በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የድኅረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፤ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት

በላይ ሰይድ

ሰኔ 1992 ዓ.ም.

# የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፣ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት
የቀረበ ጥናት

ለእንግሊዝኛ ማስተማር /TEAM/ ኤም.ኤ. ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ

በላይ ሰይድ
ጥር፣ 1992 ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት

# የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ፡ በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት

በ

በላይ ሰይድ
የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

የፈተና ቦርድ አባላት

______________________ ______________________
አማካሪ

______________________ ______________________
ፈታኝ

______________________ ______________________
ፈታኝ

# ምስጋና

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ጊዜያቸውን ሰውተው ፅሁፌን በማንበብ፣ የማሻሻያ ሀሳብ በመስጠትና በማረም የቅርብ ክትትላቸው ሳልተለየኝ አማካሪዬና መምህሬ ለዶ/ር አረጋ ኀይለሚካኤል ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

እንዲሁም ልምዳቸውን በማካፈል ጠቃሚ ምክሮችንና አስተያየቶችን በመስጠትና በማበረታታት፣ ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መጻሕፍቶችን በማዋስ የሙያ ድጋፋቸው ሳልተለየኝ ለአቶ ዘሪሁን አስፋው፣ ለዶ/ር ሀብታሙ ወንድሙ፣ ለዶ/ር ደጀኔ ለታና ለአቶ ሰለሞን ተሰማ ያለኝ አክብሮትና ምስጋና የላቀ ነው፡፡

ለጥናቱ መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኘው የመድኃኔ አለም አጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህራንና፣ በ1991 ዓ.ም. የትምህርት ቤቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን እንዲሁም የ11ኛ 21፣23 እና 30 ምድብ ተማሪዎች በተጠኚነት በመሳተፍ ለጥናቱ መሳካት ላደረጉልኝ ትብብር ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡

በጥናቱ ሂደት ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ የምክርና የማተሪያል እገዛው ሳልተለየኝ ለባለቤቴ ለአቶ ሰውመሆን እንግዳየሁ፣ እንዲሁም ለአቶ እንተነህ ወርቁና ለአቶ ይትባረክ ወርቁ፣ እስቸጋሪውን ልጅ የመንከባከብ ተግባር በትዕግስት በመወጣት፣ ለጥናቱ መሳካት እገዛዋ ሳልተለየኝ ለእህቴ ለሀዋ ሰይድ ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የጥናቴን ረቂቅ በማንበብና አስተያየት በመስጠት በቪዲዮ የተቀረፀውን መረጃ በመሰነድ ለተባበሩኝ ጓደኞቼ ለአቶ እንግዳ ዘውዱ፣ ለአቶ ታደሰ ሲባሞ፣ ለአቶ በፍቃዱ ዘለቀና ለአቶ ጌታሁን ሞላ፣ በቀተታ ተጠኚ ክፍሎችን በቪዲዮ ካሜራ በመቅረፅ ለተባበሩኝ ለአቶ በቀለ አስፋው ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በመጨረሻም ለጥናቱ የሚረዱ የተለያዩ ፅሁፎችንና ዋናውን ጥናት በኮምፒውተር በመፃፍ ቀና ትብብራቸው ሳልተለየኝ ለወ/ሮ ዘነበች ሽፈራውና ለወ/ሮ ዕላት አድነው ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

በክፍል ውስጥ የመማሀር ተማሪ ተራክቦ ላይ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች አብረው በሚማሩባቸው ክፍሎች የወንዶች ተማሪዎች ተሳትፎ ከሴቶች የበለጠ መሆኑንና መምህራንም ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ ከሴቶች የበለጠ መሆኑን ለማሳየት ሞክረዋል።

የዚህ ጥናት ዋንኛ ትኩረትም ሴቶች ተማሪዎች በሚበዙበት፣ ከወንዶች ጋር እኩል በሚሆኑበትና ወንዶች በሚበዙበት ምድብ የሴቶችንና የወንዶችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎና መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ልዩነት መኖር አለመኖሩን መመርመር ነው። ጥናቱ የተካሄደው አዲስ አበባ ውስጥ በመድሃኔ አለም አጠቃላይ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ሲሆን ተጠኝዎቹ 79 ወንዶችና 68 ሴቶች ተማሪዎችና ስድስት የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ናቸው።

የተማሪዎችን ተሳትፎ መጠንና የመምህሩን ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ ለመመርመር የተመረጡት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የቪዲዮ ቀረፃ፣ በመምህራን በተማሪዎች የተሞላ የፅሁፍ መጠይቅና ምልከታ ናቸው።

ከላይ በተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው መረጃም የወንዶችና የሴቶችን ተሳትፎ መጠን በሚመለከት በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ እንዳላቸውና መምህራንም የበለጠ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት ለወንዶች መሆኑን አሳይቷል። የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ የሆነበት ምክንያት መምህራኑና ተማሪዎች በሰጡት አስተያየት፣ ሴቶች ተማሪዎች "ብሳሳት ይስቁብኛል" በሚል ለመሳተፍ ስለማይፈልጉ፣ ለመሳተፍ ቢፈልጉም እድሉን፣ የበለጠ የሚያገኙት ወንዶች በመሆናቸው፣ መምህራን ከሴቶች ይልቅ ወንዶችን የበለጠ ስለሚያቀርቡ፣ ሴቶች በባህል ተፅዕኖ ከወንዶች እኩል መከራከርና ማውራት ስለማይፈቀድላቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ለዚህም የተሰጠው አስተያየት መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ወንዶችና ሴቶችን እኩል ቢይዙ ወይም እኩል ትኩረት ቢሰጡ፣ በትምህርት ቤቶች ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎችን እኩል የሚያሳትፍ የውይይት መድረክ በማዘጋጀት የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ይቻላል የሚል ነው።

## ማውጫ


ገፅ

ምዕራፍ አንድ፡- መግቢያ

1.1. የጥናቱ ዳራ.................................................... 1

1.2. የጥናቱ አላማ.................................................... 3

1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ.................................................... 4

1.4. የጥናቱ ወሰን....................................................5

ምዕራፍ ሁለት፡ የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

2.1. የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦ/ተሳትፎ/ ምንነት........................ 6

2.2. የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያለው ሚና....................................................7

2.3. በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የጾታ ልዩነት....................................................8

2.4. መምህራን ለሴቶችና ለወንዶች የሚሰጡት ትኩረት (Teacher treatment)እና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ (Verbal feed-back) ከተማሪዎች ተሳትፎ ጋር ያለው ግንኙነት....................................16

2.5. በየምድቦቹ የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎች ቁጥር የተለያየ መጠን ንፃሬ(Ratio) ከተሳትፎአቸው ጋር ያለው ግንኙነት........................20

2.6. ለራስ የሚሰጥ ግምት (self-esteem) ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎና ከጾታ ጋር ያለው ግንኙነት....................................22

ምዕራፍ ሶስት፡ የአጠናን ዘዴ

3.1. የናሙና ትምህርት ቤት መረጣ....................................24

3.2. የተሳታፊዎች አወሳሰድ....................................24

3.3. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ....................................25

3.3.1. የፅሁፍ መጠይቆች....................................25

3.3.2. የቪዲዮ ቀረፃ....................................27

3.3.3. የክፍል ውስጥ ምልከታ....................................27

3.4. የመረጃ አተናተን ሂደት....................................29

ምዕራፍ አራት፡ የመረጃዎች ውጤትና ትንተና

4.1. የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠን በሚመለከት ከቪዲዮ ምዝገባ (Video Transcription) እና ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና..31

4.2. የወንዶችና የሴቶችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከተማሪዎችና ከመምህራን የጽሁፍ መጠይቆች የተገኘ መረጃ ትንተና..42

4.2.1. ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት............42
4.2.2. ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት............49
4.3. መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት (Teacher treatment) እና ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ (Verbal feedback)..........52
4.3.1. መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከቪዲዮ ምዝግቡ የተገኘ መረጃትንተና..........53
4.3.2. መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና..........60
ምዕራፍ አምስት፡ ማጠቃለያና አስተያየት
5.1. ማጠቃለያ..........78
5.2. አስተያየት..........80
ዋቢ ምንጮች..........82

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ ገፅ


ሀ. በየምድቦቹ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛትና የጾታ ስርጭት.................... 25

1. የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎችን ንግግር /utterance/ በአማካይ (Mean)እና በመቶኛ ስሌቶች .......................... 31
2. ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚያደርጉትን እጅ የማውጣት ድግግሞሽ በተመለከተ ከቪዲዮ ቀረጻው የተገኘ መረጃ ውጤት.......................... 32
3. በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች የተመለሱ መልሶችን ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ.................................................. 34
4. ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ያልገባቸውን ጥያቄ በመጠየቅ በኩል የሚያደርጉትን ተሳትፎ በሚመለከት ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘ መረጃ ውጤት.................................. 35
5. በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች የቀረቡ ትክክለኛ መልሶች ብዛትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ.................................. 37
6. ከተማሪዎች መልስ አሰጣጥ አንፃር በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚኖረውን የተሳትፎ ልዩነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ.... 39
7. በስድስቱም ምድቦች የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘ መረጃ ውጤት.......... 41
8. መጠይቅ በመሙላት ተሳታፊ የሆኑ ተማሪዎችን ዱሬ የሚገልፅ ሰንጠረዥ.................................................. 43
9. የወንዶችና የሴቶችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ.................................................. 44
10. ወንዶችና ሴቶች ለራሳቸው የሚሰጡትን ግምት በሚመለከት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ .......... 47
11. የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት.......... 49
12. የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ የሆነበትን ምክንያት በተመለከተ ከመምህራን የተሰጡ አስተያየቶች በምን ላይ ያተኩሩ እንደሆነ የሚያሳይ........... 51
13. መምህራን እጃቸውን ላወጡ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ያደረሱትን ጥያቄ መጠን የሚያሳይ .......................... 54
14. ለመመለስ ፈቃደኛ (እጃቸውን ላላወጡ) ወንዶችና ሴቶች መምህሩ የሰጡትን ጥያቄ መጠን የሚያሳይ...................... 54
15. ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ መምህራን ስማቸውን በተደጋጋሚ የጠሯቸው ወንዶችና ሴቶች ብዛት.................. 55
16. በምድብ አንድ (ሴቶች በሚበዙበት) የመምህሩን አዎንታዊ፣ አሉታዊና መካከለኛ (Neutral/ ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘ መረጃ ውጤት........... 58
17. የመምህሩን አዎንታዊ፣ አሉታዊና መካከለኛ (Neutral/ ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከምድብ ሁለት (ወንዶችና ሴቶች እኩል በሆኑበት) የተገኘ መረጃ............... 59
18. የመምህሩን አዎንታዊ፣ አሉታዊና መካከለኛ (Neutral/ ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከምድብ ሶስት (ወንዶች በሚበዙበት) የተገኘ መረጃ ውጤት.................................. 59
19. መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ትኩረት በሚመለከት በምድብ አንድ ከሚማሩ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት.................................. 61

20. መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ትኩረት በሚመለከት በምድብ ሁለት ከሚማሩ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት........................ 65
21. መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ትኩረት በሚመለከት በምድብ ሶስት ከሚማሩ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት.................................. 68
22. መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከምድብ አንድ ተማሪዎች የተገኘ መረጃ ውጤት................................................... 71
23. መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከምድብ ሁለት ተማሪዎች የተገኘ መረጃ ውጤት................................................... 73
24. መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከምድብ ሶስት ተማሪዎች የተገኘ መረጃ ውጤት................................................... 75

# የአባሪዎች ዝርዝር

አባሪ


ገፅ

1. የቪዲዮ ምዝግብ /Vedio-transcription/
    1.1. በምድብ አንድ ........................................................ 86
    1.2. በምድብ ሁለት ........................................................ 98
    1.3. በምድብ ሶስት ........................................................ 105

2. ለተማሪዎች የተበተነ የጽሁፍ መጠይቅ ........................................ 114

3. ለመምህራን የተበተነ የጽሁፍ መጠይቅ ........................................ 117

4. የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመመርመር የተዘጋጀ የምልከታ ቻርት.............. 123

5. የመምህሩን ትኩረት (Attention) እና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ
ለመመርመር የተዘጋጀ የምልከታ ቻርት ........................................ 124

# ምዕራፍ አንድ

## 1. መግቢያ

### 1.1. የጥናቱ ዳራ

የጾታን ልዩነት መሠረት በማድረግ በመማሪያ ክፍል (መማክ) በመማር ማስተማር ሂደት የመምህር ተማሪን ተራክቦ የመረመሩ ጥናቶች በተለያዩ ሀገሮች (ለምሳሌ፡በማላዊ፡ በታንዛኒያ፡ በሩዋንዳና በሌሎችም) ተካሂደዋል:: በእነዚህ ሀገሮች የተደረጉ የመማክ ውስጥ ምልከታ በክፍል ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ መምህራን የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት፡ በተደጋጋሚ ጥያቄ የሚጠይቁትና እንዲመልሱ እድል የሚሰጡት ከሴቶች የበለጠ ለወንዶች ተማሪዎች መሆኑንና በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ወይም ተራክቦ በልጠው የሚታዩት ወንዶች መሆናቸውን Odaga and Henveld (1995), Kilo (1994)ን በመጥቀስ ገልጸዋል::

ከዚህ በተጨማሪም John and Glendnning (1995), Golombok and Fivush(1994) Sunderland (1994) Irvine(1986) እና ሌሎቹም ባካሄዷቸው የምርምር ሥራዎች ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች አብረው በሚማሩባቸው መማክ ውስጥ ወንዶች ተማሪዎች ከሴቶች የበለጠ የክፍል ውስጥ ተራክቦ ሲኖራቸው ከወንድም ሆነ ከሴት መምህሮቻቸው ዘንድ የሚያገኙትም ትኩረት ከሴት ተማሪዎች የበለጠ እንደሆነ ገልጸዋል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ Sunderland (1994) Gass and Varonis ን በመጥቀስ እንደገለጹት መምህራን ተማሪዎቻቸውን በጾታቸው መለያየት የተነሣ እኩል አያበረታቷቸውም:: ስለተማሪዎቻቸውም ሲጠየቁ በስፋትና በዝርዝር የሚናገሩትም ሆነ ስማቸውን በተደጋጋሚ የሚጠሩት ወንዶች ተማሪዎችን ብቻ ነው::

በሀገራችንም MacCoul(1994)በሂሳብ ትምህርት ሰሎሞን አበበ(1997) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት የሴት ተማሪዎችን ቃላዊ ተራክቦ ከወንዶች ጋር በማነጻጸር ባደረጉት ጥናት ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች ያነሱ መሆናቸውንና በንግግር ጊዜም የሚወስዱት ተራ (Turn-Taking) ከወንዶች በጣም ያነሰ መሆኑን እንዲሁም በክፍል ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ ገንኖ የሚታየው የወንዶች ተማሪዎች ተራክቦ መሆኑን አመልክተዋል::

በአጠቃላይ በቋንቋ ለመናና መማር ረገድ ሴቶች ከወንዶች የተሻሉ ናቸው የሚሉ በጎኒት ተመራማሪዎች ቢኖሩም በሀገራችንም ሆነ በውጭ ሀገር የተደረጉ ጥናቶች ያስገኟቸው ውጤቶች ግን በመማክ ውስጥ ተራክቦ ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች ያነሱና የመምህራኑም ትኩረት በወንዶች ተማሪዎች ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው::

ከላይ የተለያዩ ምሁራን ጥናቶችን በመጥቀስ እንደተገለጸው በክፍል ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ የሴት ተማሪዎች ቃላዊ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ ነው::ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶችን Clerk and Tranford(1995), Lindros(1995), Lott(1987), Betz and Fetzegeraldi(1987), Coates(1986)ይጠቅሳሉ:: ከእነዚህም መካከል ሴቶች ተማሪዎች በወንዶች ጓደኞቻቸውና በመምህሮቻቸው ፊት ለመናገር አለመድፈር፡ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት

ዝቅተኛ መሆን፣ ለመናገር በሚሞክሩበት ጊዜ ንግግራቸው በወንዶች አቻዎቻቸውና በመምህሮቻቸው መቋረጡ፣ መምህራን በተደጋጋሚ ጥያቄ የሚጠይቁትም ሆነ የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ለወንዶች ተማሪዎች በመሆኑና የማህበረሰቡ ባህልም ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል ማውራትና መከራከር እንደሌለባቸው ስለሚያግድ የሚሉት ከብዙዎቹ ምክንያቶች ጥቂቶቹ ናቸው።

በተጨማሪም በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የወንዶች ተሳትፎ በልጦ መታየቱና መምህራንም የበለጠ የሚያበረታቱት፣ ማለትም በተደጋጋሚ ስማቸውን የሚጠሩት፣ ጥያቄ የሚጠይቁት ወንዶችን ብቻ በመሆኑ የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ አነስተኛ ሊሆን ችሏል ሲሉ በዚህ መስክ ላይ ጥናት ያደረጉ በርካታ ምሁራን ይገልጻሉ። በዚህም መሠረት ብቻቸውንና ከወንዶች ጋር የሚማሩ ሴቶች ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተራክቦ ልዩነት ያጠኑ ምሁራን ለምሳሌ King and Hill (1994) Lockeed and Verspoor(1991)ን በመጥቀስ፣ በጥናታቸው ያገኙት ውጤት ብቻቸውን የሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች ጋር ከሚማሩት የበለጠ ንቁ ተሳታፊዎች መሆናቸውን የሚያሳይ ሲሆን ለራሳቸው የሚሰጡት ግምትም ከፍተኛ ነው። የሚል መሆኑን ለመረዳት ተችሏል። ከዚህም ሌላ የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች በሚያንስበት በሚበልጥበትና ተመጣጣኝ በሚሆንበት ክፍል ውስጥ የሴት ተማሪዎች ተራክቦ ምን እንደሚመስል ያጠኑ ምሁራን አሉ። ከእነዚህም ለምሳሌ Webb (1984) በከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ሴቶች ተማሪዎች ላይ ባካሄዱት ጥናት የሴት ተማሪዎች መጠን ንጻሬ (ratio) የተለያየ በሆነበት ቡድን ለተማሪዎች የክፍል ውስጥ ሥራ በመስጠት እንዲወያዩ ካደረጉ በኋላ ድምፃቸውንም በቴፕሪከርደር በመቅዳትና መረጃውንም በጽሁፍ በመመዝገብ ያገኙት ውጤት ሴቶች ከወንዶች በሚበልጡበት ቡድን የሴቶች ተሳትፎ መጠን ከወንዶች የተሻለ ሲሆን ተመጣጣኝ በሆነበት ተሳትፎአቸውም እኩልና ከወንዶች በሚያንስበት ቡድን ተሳትፎአቸው በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የሚያሳይ ነው።

በሀገራችን አማኑኤል ገብሩ (1996) በቡድን ውይይት በሚደረግ ቃላዊ ተራክቦ የሚታየውን የጾታ ልዩነት በሚመለከት በአንደኛ ዓመት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ባካሄዱት ጥናት ያገኙት ውጤት ቀደም ብሎ ከተጠቀሰው ጥናት ውጤት የተለየ ነው። ይህም ሶስቱም ቡድኖች (ማለትም ወንዶች የሚበዙበት ሁለቱም ተመጣጣኝ የሆኑበትና ሴቶች የሚበዙበት) አድርጎ በመከፋፈል በአንድ ርዕስ ነገር ላይ እንዲወያዩ በማድረግና መረጃውን በመሰብሰብ ያገኙት ውጤት በቃላዊ ተራክቦ በሶስቱም ቡድኖች በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ልዩነት የለም የሚል ነው። ይሁን እንጂ የአማኑኤል ጥናት ልዩነት ያላሳየው ምናልባትም የወንዶቹና የሴቶቹ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታቸው የማይለያይ በመሆን ሊሆን ይችላል።

በአጠቃላይ በመማክ ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የጾታን ልዩነት በመመርመር ጥናት ያካሄዱ ምሁራን እንደሚያስገነዝቡት በክፍል ውስጥ በሚከናወነው ትምህርት የሴቶች

ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛና ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ መልስ ለመስጠት የሚያደርጉት ሙከራም ከወንዶች በጣም ያነሰ ነው። ይህም ሴቶችና ወንዶች ተማሪዎች አብረው በሚማሩባቸው መማክ ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት የሚኖራቸው ቃላዊ ተሳትፎ፣ ለመሳተፍ የሚያገኙት ዕድልና የሚያደርጉት ልምምድ ከትምህርት ቤት ከወጡ በኋላም ወንዶችና ሴቶች አብረው በሚሰሩባቸው ቦታዎች በሚያደርጓቸው ውይይቶች፣ የተለያዩ የቡድን ጨዋታዎች (role play) ወዘተ. ላይ ለሚኖራቸው ተሳትፎ መሰረት በመሆኑ ሴቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች እኩል እንዲሆኑና የበለጠ እንዲሳተፉ መበረታታት አለባቸው። መምህሩንም ተማሪዎቻቸውን እኩል ማበረታታትና ማሳተፍ ይኖርባቸዋል።

ሴቶች ተማሪዎች በጠቅላላው በትምህርት ረገድ ያላቸው ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ መሆኑን በጥናቶቻቸው ያረጋገጡ የውጭም ሆነ የሀገራችን ምሁራን በርካታ ናቸው። በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ፣ የተማሪ ተማሪ ቃላዊ ተራክቦን በተመለከተ በውጭው አለም በተለያዩ የክፍል ደረጃዎችና የትምህርት አይነቶች ላይ በርካታ ጥናቶች የተከናወኑ ቢሆንም በሀገራችን ግን MacCoul (1994) በሂሳብ ትምህርት፣ አማኑኤል ገብሩ (1996)፣ ሰሙንሽ አበበ(1997) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ካደረጓቸው ጥናቶች በስተቀር ሌሎች ጥናቶች አለመደረጋቸው፣ እንዲሁም የወንዶችና የሴቶች ቁጥር እኩል በሆነበት ቡድን ውስጥ የተደረጉ ጥናቶች ቢኖሩም፣ የሴቶችና የወንዶች መጠነ ንፃሬ የተለያየ በሆነበት ቡድን በሀገራችን አማኑኤል ገብሩ(1996) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ካደረጉት ጥናት ሌላ ባለመደረጉ፣ በተለይ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ ብርሃኑ ገብረማርያም (1986) ካደረጉት ጥናት በስተቀር የሴት ተማሪዎችን ቃላዊ ተራክቦ በሚመለከት የተካሄደ ጥናት ያለመኖሩ የዚህ ጥናት አነሳሽ ምክንያት ሆኗል።

## 1.2. የጥናቱ አላማ

የዚህ ጥናት አላማ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ የሴት ተማሪዎችን ቃላዊ ተራክቦ መጠን መመርመርና መምህሩን ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎቻቸው የሚኖራቸውን አመለካከት ወይም የሚሰጡትን ትኩረት መጠን ማሳየት ሲሆን በዝርዝር ሲታይም የሴቶችና የወንዶች መጠነ ንፃሬ የተለያየ በሆነበት (ማለትም ሴቶች በሚበዙበት፣ ተመጣጣኝ በሚሆኑበትና በሚያንሱበት ክፍል) ውስጥ የሚኖራቸውን ቃላዊ ተራክቦ መጠንና ሊኖር የሚችለውን ልዩነት፣ ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች ያነሰ ተራክቦ የሚኖራቸው ከሆነም ሴቶች ከወንዶች እኩል ተራክቦ እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ ምክንያቶችን ማመልከት ነው።

ጥናቱ በእነዚህ አላማዎች ላይ ተመስርቶ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ይሞክራል፣

1. ሴቶች ከወንዶች በሚበዙበት ምድብ የሴት ተማሪዎች ቃላዊ ተራክቦ መጠን ምን ያህል ነው?
2. ሴቶችና ወንዶች ተመጣጣኝ በሆኑበት ምድብ የሴት ተማሪዎች ቃላዊ ተራክቦ መጠን ምን ያህል ነው?
3. ሴቶች ከወንዶች በሚያንሱበት ምድብ የሴት ተማሪዎች ቃላዊ ተራክቦ መጠን ምን ያህል ነው?
4. በሶስቱ ምድቦች በሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች መካከል የተራክቦ መጠን ልዩነት አለን? ልዩነት ካለ የልዩነቱ መንስኤ ምንድን ነው?
5. መምህሩን፣ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር፣ ለሴት ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ ምን ያህል ነው? የመምህሩት ትኩረት ለሴት ተማሪዎች ዝቅተኛ ከሆን ከተሳትፎአቸው ጋር ግንኙነት አለውን?

## 1.3. የጥናቱ ጠቀሜታ

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሴት ተማሪዎችን የመማክ ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ መጠን፣ ንቁ ተሳትፎ የማይኖራቸው ከሆን እንዳይኖራቸው የሚያደርጉ ምክንያቶችን ማውጣትና መምህሩን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት መመርመር ሲሆን ውጤቱም የሚከተሉትን ጠቀሜታዎች ያስገኛል ተብሎ ይታሰባል፣

1. ሴቶች ብዙ ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታም ሆነ ከወንዶች ጋር በሚማሩባቸው ክፍሎች የሚኖራቸው ቃላዊ ተራክቦ ከወንዶች ያነሰ መሆኑን በርካታ ጥናቶች እንደሚያሳዩ ከላይ ለመግለፅ ተሞክሯል። በዚህም በቃላዊ ተራክቦ የሚኖራቸው ተሳትፎ፣ አነስተኛ ከሆን ቋንቋን በመግር ረገድ የሚያገኙት እድል የተገደበ ይሆናል። ከትምህርት ቤት ውጭም በሚካሄዱ ውይይቶች ተሳታፊዎች እንዳይሆኑ እንቅፋት ይሆናል። ስለዚህ ሴቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚኖራቸው ቃላዊ ተሳትፎ ተመርምሮ ንቁ ተሳትፎ ከሌላቸው እንዳይሳተፉ የሚያግዷቸው ምክንያቶች ታውቀው የበለጠ እንዲሳተፉና እንዲበረታቱ አስፈላጊው ጥረት እንዲደረግ፣ ለመምህራንም ሆነ ለመምህራን አሰልጣኞች ሀሳብ ይሰጣል።

2. በመማክ ውስጥ በሚከናወን የመማር ማስተማር ሂደት መምህሩን ለሴቶችና ለወንዶች የሚሰጡት ትኩረት የተለያየ ከሆን መምህሩት ይህን ልዩነት አስወግደው ሴቶችና ወንዶች ተማሪዎችን እኩል እንዲያሳትፉና እንዲያበረታቱ እንዲሁም እኩል ትኩረት መስጠት አስፈላጊነቱን እንዲረዱት ለማድረግ የሚያስችል ዘዴ በስልጠና ወቅት እንዲሰጣቸው አስተያየት ይሰነዝራል።

3. ይህ ጥናት ሴቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተራክቦ በተለይም በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማሪያ ክፍል ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የሚገጥሟቸውን ችግሮች ስለሚያሳይ ችግሮቹን ለማቃለል የሚያስችሉ የመፍትሄ ሀሳቦችን ይጠቁማል።

4. በመጨረሻም ተመሳሳይ ችግር ይዘው በተለያዩ የትምህርት ዓይነቶችና የክፍል ደረጃዎች ላይ ጥናት ለማካሄድ ለሚነሱ አጥኚዎች እንደመነሻ ሊያገለግል ይችላል።

## 1.4. የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ሴቶች ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሚኖራቸውን የተራክቦ መጠንና መምህራን ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ልዩነት ይመረምራል። ጥናቱ በተቅሉ የሴት ተማሪዎችን ቃላዊ ተራክቦ (ለጥያቄዎች መልስ መስጠት፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ሀሳብ መሰንዘር እና የመሳሰሉትን)፣ እንዲሁም የመምህራን ትኩረት (attention)ና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ (verbal -feedback ) (ተማሪዎች መልስ እንዲሰጡ በተደጋጋሚ መጠየቅ፣ ስማቸውን በተደጋጋሚ መጥራት፣ ማሞገስ፣ መተቸትና የመሳሰሉትን) በመከፋፈል ያቀርባል። በተጨማሪም ከላይ ከተዘረዘሩት ተላውጠዎች አንፃር የሴት ተማሪዎች መጠነ ንግሬ የተለያየ በሆነባቸው ምድቦች ሊታይ የሚችለውን ልዩነት ያመለክታል።

ጥናቱ በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ በመምህር ተማሪ ተራክቦ ስር በሚደረግ ቃላዊ ተራክቦ ላይ ብቻ የሚያተኩር ሲሆን ኢ ቃላዊ ተግባራት (Non-verbal Activities) (ለምሳሌ፡ ራስን ማወዛወዝ፣ ፈገግታ፣ የአይን እንቅስቃሴ፣ ወዘተ.) በዚህ ጥናት አልታዩም። በተጨማሪም የመምህራንን ጾታ በተመለከተ ወንዶችና ሴቶች መምህራን የማስተማር ዘዴያቸው የተለያየ ቢሆንም ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት ተመሳሳይ ነው። በሌላ አገላለፅ የመምህራን ጾታ ለተማሪዎች ከሚሰጡት ትኩረት አንፃር ተፅዕኖ አይኖረውም ሲሉ Woods and Hummersley (1993), Good et al (1975), Kelly (1988), Sunderland (1992) የገለፁትን መሰረት በማድረግ ወንዶች መምህራንን ለማየት ተችሏል። እንዲሁም በተመረጡት ክፍሎች ውስጥ የሚያስተምሩት መምህራን ወንዶች በመሆናቸው ጥናቱ ሴት መምህራንን አያሳይም።

# ምዕራፍ ሁለት

## የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

### 2.1. የመማሪያ ክፍል (መማክ) ውስጥ ተራክቦ ምንነት

Thomas(1991:8) እና Irvin(1986ን 14) የተራክቦን ምንነት ሲገልጹ፡ "ተራክቦ ባለሁለት ፈርጅ ሂደት (two way process) ሲሆን ይህም አንድ ተናጋሪና አንድ አድማጭ ወይም ለንግግሩ ምላሽ የሚሰጥ አካል ያለበት ማለት ነው ይላሉ።" ይህም በሁለትና ከዚያ በላይ ባሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች መካከል የሚደረግ ቃላዊ ምልልስ ወይም ንግግር ተራክቦ እንደሚባልም ገልጸዋል። በተራክቦ ሂደት በሁሳብ የመደጋገፍም ሆነ መጋጨት ሊኖር እንደሚችል ምሁራት ያስገነዝባሉ።

ወደ መማክ ውስጥ ስንመጣ ደግሞ በመማክ ውስጥ በሚደረግ ተራክቦ ተሳታፊዎቹ መምህሩ፣ ተማሪዎችና የመማሪያ መጸህፍቱ መሆናቸውን የተለያዩ ጥናቶች ይገልጻሉ።

በመማክ ውስጥ በሚከናወን የመምህር ተማሪ ተራክቦ ስር የሚነሱ ጉዳዮች ማለትም መምህሩና ተማሪዎች በመማክ ውስጥ የሚኖራቸው ተራክቦ የሚገለጸው በሚከተሉት ፈርጆች (Patterns) ዙሪያ ነው። እነዚህም ማስተማር (Lecturing) ፣ መጠየቅ (Questioning) ፣ ማሞገስ (Praising)፣ መተቸት (Critisizing) ናቸው። John and Glendinning (1996) ። ከዚህም በተጨማሪ Irvin (1986:14) የመምህር ተማሪ ተራክቦን በሚመለከት ባካሄዱት ጥናት እንዳመለከቱት፣ በመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የሚደረጉ ጥናቶች የሚያነሷቸው የምርምር ጥያቄዎች የተማሪውን ፈር ቀዳጅ ባህርይ (student initiation Behaviour) ፣ የመምህሩን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ (Teacher Verbal-Feedback) እና ተማሪው ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት የሚያገኘውን ዕድል (Student Response Opportunity) የተመለከቱ ናቸው።

ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ Sunderland (1994:137) ደግሞ በመማክ ውስጥ የሚደረግ ግንኙነትም ከንቁ በተራክቦ ስር እንደሚጠቃለል ከገለፁ በኋላ የመማክ ውስጥ ተራክቦ ከቀላል የመማር ባህርይ እስከ ሙሉ ወይም አጠቃላይ የሆነ የመማር ማስተማር ሂደት የሚደርስ መሆኑንም አስረድተዋል። በዚህም መሰረት በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የሚደረግ የመምህርና የግለሰብ ተማሪ፣ የመምህርና የቡድን ወይም የክፍሉ አጠቃላይ ተማሪዎች፣ የተማሪዎች የርስበርስ ንግግር በተራክቦ ስር እንደሚጠቃለል አመልክተዋል። በተጨማሪም Allwright and Bailey (1991:3) የመማክ ውስጥ ተራክቦ ተማሪዎች በመማር ማስተማሩ ሂደት የሚወስዱት ተራ ስርጭት (turn-distribution) መሆኑን አስረድተዋል።

ከላይ የተለያዩ ምሁራንን በመጥቀስ እንደተገለጸው፣ ተራክቦ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ ቡድኖች መካከል የሚደረግ የእርስ በርስ ግንኙነት ሲሆን የመማክ ውስጥ ተራክቦም

በመማር ማስተማሩ ሂደት መምህሩንና ተማሪዎችን፣ መማሪያ መፃህፍቱን እንዲሁም እነዚህ የሚያደርጉትን የእርስ በርስ ግንኙነት የሚመለከት ነው፡፡ ንግግርን በተመለከተ ደግሞ በመማክ ውስጥ የሚከናወነን የመምህር ተማሪ ቃላዊ ተሳትፎ የሚመለከት ይሆናል፡፡ ይህም መምህሩ ያስተምራል፣ ተማሪው ምላሽ ይሰጣል፡፡ በዚህም ጥያቄ ይጠይቃል፣ ይመልሳል፣ አስተያየት ይሰጣል፣ መምህሩም ለተማሪው ንግግር ምላሽ ይሰጣል፡፡ እነዚህም ማስተካከያ (እርማት፣ ማበረታቻ፣ ትችትና የመሳሰሉት) ናቸው፡፡ ስለዚህ በዚህ ሁኔታ በመምህሩና በተማሪዎች መካከል የሚደረገው ንግግር ቃላዊ ተራክቦ እንደሚባል ከላይ ከተጠቀሱት ሀሳቦች መረዳት ይቻላል፡፡

በመሆኑም በመማክ ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ ጥናት ለማድረግ የሚነሳ ተመራማሪ ለምርምሩ የሚያነሳቸው ጥያቄዎች በመምህሩ የማስተማር ስልት፣ በሚጠየቁት ጥያቄዎች አይነትና ብዛት፣ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ተማሪዎቹ ከመምህሩ በሚያገኙት ዕድል፣ በተማሪዎች ፈር ቀደድ ባህርይ፣ መምህሩ ለተማሪዎቹ በሚሰጠው ምጋቤ ምላሽ (ሙገሳ፣ትችት፣ወዘተ) አይነትና መጠን ዙሪያ እንደሚሆን የምሁራኑ የምርምር ውጤት ያሳያል፡፡

## 2.2. የመማክ ውስጥ ተራክቦ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ያለው ሚና

በመማክ ውስጥ የሚደረግ የመምህር ተማሪ እና የተማሪ ተማሪ ተራክቦ ለመማር-ማስተማሩ ሂደት የላቀ አስተዋጽኦ እንዳለው በርካታ ምሁራን ይገልፃሉ፡፡ ከእነዚህም ለምሳሌ Allwright(1991:8)፣ "የመማክ ውስጥ ተራክቦ ለትምህርቱ መሳካትም ሆነ በመምህሩና በተማሪው መካከል ለሚኖረው ማህበራዊ ግንኙነት የሚበጅ በመሆኑ አስፈላጊነቱ የጎላ ነው፡፡" ሲሉ ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም ብርሃኑ ገብረማርያም (1986:4)Thomas and Allwright (1991)ን በመጥቀስ እንደገለፁት ቀደም ሲል የተለማዱትን አይነት የአቀራረብ ስልት ብንከተል መማርና ማስተማርን የሚያማክለው የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦ፣ በተራክቦው ላይ ለተሳታፊዎች የሚሰጥ ድርሻና ተሳታፊዎቹ የሚጫወቷቸው ሚናዎች አይነት በመሆኑም ተራክቦ መማር ማስተማርን የሚያግዝ ድልድይ ነው፡፡

በመሆኑም የመማክ ውስጥ ተራክቦ ተማሪው በመማር ማስተማሩ ሂደት ምን ያህል የመማር ዕድል አገኘ? የሚለውን ጥያቄ መልስ ስለሚነግረን የጎላ ጠቀሜታ አለው፡ ምክንያቱም ተራክቦ መምህሩ ጠቃሚ መሰረተ ሀሳቦችን (information) ለተማሪው የሚያቀርብበትና የተማሪውን የመማር ባህርይ የሚገመግምበት አይነተኛ መንገድ በመሆኑም ነው፡፡ ይህን በሚመለከት Sunderland (1994) በተለይም በቋንቋ ትምህርት መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚደረግ የመምህር የአንድ ተማሪ (individual student)፣ የመምህር የቡድን ተማሪዎች፣ የመምህር አጠቃላይ የክፍሉ ተማሪዎችና የተማሪ ተማሪ ተራክቦ ተማሪዎች ለትምህርት

የቀረበውን ቋንቋ በተግባር እንዲጠቀሙበትና ሀሳባቸውን በትክክል ለመግለፅ እንዲችሉ የሚያደርግ በመሆኑ አስፈላጊነቱ የላቀ ነው በማለት ይገልፃሉ።

እንዲሁም በመማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ ተማሪዎች ቃላዊ ተሳትፎ ከሌላቸው የሚከተሉት ችግሮች እንደሚያጋጥሟቸው Lyle (1997:39) Boxdell (1988)ን እና Bennet (1976)ን በመጥቀስ ይገልፃሉ፤

1. ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተራክቦ ቃላዊ ተሳትፎ (ንግግር) ከሌላቸው ያላቸውን እውቀት መጠቀም አይችሉም፤
2. ተማሪዎች ለመናገር ዕድሉን ካላገኙ ሀሳብ ለማመንጨት አይችሉም፤
3. ተማሪዎች ስለተለያዩ ነገሮች ንግግር ሳያደርጉ ግንዛቤያቸውን ለመግለፅ አይችሉም።

ስለዚህ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን እንደሚሉት በመማር ማስተማሩ ሂደት ብዙውን ጊዜ በመናገርና በማዳመጥ ላይ ማተኮር የተማሪዎችን የመፃፍና የማንበብ ክሂል ስለሚያዳብር ወሳኝነት አለው። በዚህም በርካታ መምህራን፤ ንግግር ተማሪዎች የበለጠ እንዲማሩ የሚያግዝ መሆኑን ያምናሉ።

ከዚህ በተጨማሪም መምህሩ ከተማሪዎች ንግግር መጠንና አይነት ተነስቶ ተማሪዎቹ ምን ያህል ያውቃሉ? ወይም በትምህርቱ ሂደት ለመሳተፍ እድል ያገኙት ምን ያህሉና እነማን ናቸው? ለሚለውና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኝበትና ለዚህም ምላሽ ለመስጠት እንዲችል የሚረዳው በመሆኑ ተራክቦ መማር ማስተማርን የሚያገናኝ መሆኑን ከምሁራኑ ገለፃ ለመረዳት ተችሏል።

ስለሆነም በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ፤ በተራክቦውም በሚደረግ ንግግር ሀሳብን ለመግለፅ፤ ለመረዳትና እውቀትን በተግባር ላይ ለማዋል እንዲሁም ከትምህርት ቤት ውጭ በሚደረጉ ውይይቶች ለመሳተፍ የሚያስችል መሰረት ለማስያዝ የሚረዳና ለመማር-ማስተማሩም ሂደት አስፈላጊ መሆኑን ከተለያዩ ምሁራን ለመገንዘብ ችለናል። ይህ ከሆነ በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ተማሪዎች ምን ያህል ቃላዊ ተሳትፎ (ንግግር) ይኖራቸዋል? ለዚህስ ከመምህሮቻቸው የሚያገኙት ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ ምን ያህል ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች መመርመር ተማሪዎቹ በትምህርቱ ሂደት ምን ያህል እውቀት አግኝተዋል? ወይም ለመናገር ምን ያህል እድል አገኙ? ለሚለው የምርምር መሰረታዊ ጥያቄ መነሻ ሀሳብ ይሰጣል።

2.3. በመማክ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የጾታ ልዩነት

ቃላዊ ተራክቦ ከጾታ ጋር ያለውን ግንኙነት ከመግለፃችን በፊት በአጠቃላይ በትምህርት ላይ የጾታን ልዩነት በቅድሚያ ማየት የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል።በመሆኑም የጾታ ልዩነትና ትምህርትን በሚመለከት በሀገራችንም ሆነ በውጭው አለም በርካታ ጥናቶች መከናወናቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ። በሀገራችን ከተካሄዱ ጥናቶች መካከል ለምሳሌ Tsige Haile (1991)፥ Genet Zewdie (1991)፥ Seyoum Teffera (1991)፥ Almaz Eshete (1991) እና ሌሎችም በትምህርት ላይ

ከሚኖር ተሳትፎ አንጻር የጾታን ልዩነት ባጠኑበት ወቅት ያገኙት ውጤት ከዝቅተኛ ክፍል ጀምሮ በየደረጃው ከሚገኙ የትምህርት ተቋማት በየክፍሉ ከሚደግሙትና ከነጭራሹ ትምህርታቸውን ለመተው (ለማቋረጥ) ከሚገደዱት ተማሪዎች ውስጥ የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች በጣም የሚበልጥ መሆኑን ያሳያል:: ወደ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚገቡም ሴቶች ከወንዶች በጣም ያነሱ መሆናቸውን ይኸው የጥናት ውጤት ያረጋግጣል::

በውጭው አለም ከተከናወኑ ጥናቶች ውስጥ ደግሞ፣ ለምሳሌ Maccoby and Jacquline (1974) , Betz and Fetzegerald (1987), Golombok and Fivush (1994) እና Johns and Smart (1995) በጥናቶቻቸው እንዳረጋገጡት ከትምህርት ጋር ከተያያዙ ተግባራት አኳያ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ልዩነት መኖሩን ገልፀዋል:: ከዚህም የተነሳ በተለያዩ የትምህርት አይነቶች የሚያስመዘግቡት ውጤት፣ ለየትምህርት አይነቱ ባላቸው ዝንባሌና አመለካከት፣ ከዚህም አልፎ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ ከመምህሮቻቸውና ከክፍል ጓደኞቻቸው ጋር በሚኖራቸው ቃላዊ ተራክቦ (Verbal Interaction) ፣ እንዲሁም ለራሳቸው ችሎታ ከሚኖራቸው ግምት (Self-esteem) ፣በተጨማሪም ለውጤታቸው ከሚኖራቸው ፍረሃትና ስጋት አንፃር በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ልዩነት መኖሩን አረጋግጠዋል::

በሌላ በኩል በተለያዩ አእምሮአዊ ተግባራት (Cognitive skills) ፣ ለምሳሌ በቃላዊ ተግባራት (Verbal skills) ፣ በቋንቋ ጥበብ (Language art) ፣ በሒሳብና በሳይንስ፣ በሙያና በቴክኒካዊ ችሎታዎች (Spatial skills) አንፃር በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚኖረውን ልዩነት በሚመለከት Maccoby and Jacquline (1974), Golombok and Fivush (1995), Marsh (1989) እንደገለፁት፣ በቃላዊ ተግባራትና በቋንቋ ጥበብ ሴቶች፣ በሒሳብና በሳይንስን ትምህርቶች ደግሞ ወንዶች የበለጠ ውጤት ያስመዘግቡ ቢሆንም በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚታየው ልዩነት ግን ከግምት የማይገባ መሆኑን አክለው ገልፀዋል::

ከዚህ በተጨማሪም Golombok and Fivush (1994), Hyde, Fennema and Lamon (1990)ን በመጥቀስ እንደሚያስረዱት፣ ከሒሳብ ችሎታ አንፃር የጾታን ልዩነት የመረመሩ ከ100 በላይ ጥናቶችን በመተንተን እንዳጠቃለሉት በሒሳብ ችሎታ ወንዶች ከሴቶች የተሻሉ ናቸው የሚል እምነት ቢኖርም፣ በጥናት የተደረሰበት ግን በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚታየው ልዩነት በጣም ያነሰ መሆኑን የሚሳይ ነው:: ይህንን ችሎታ ከተማሪዎች እድሜ አንፃር በመረመሩበት ወቅት ደግሞ በዘማንነት የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች የበለጠ ችሎታ እንደነበራቸው ተመልክተዋል:: ስለዚህም ከሒሳብ ችሎታ አንፃር የሚታየው የጾታ ልዩነት ከማህበረሰቡ እምነትና ባህል፣ እንዲሁም ለወንዶችና ለሴቶች ከሚሰጡት የስራ ድርሻ የተነሳ እንጂ በተፈጥሮአዊ ልዩነት የተነሳ አለመሆኑን አረጋግጠዋል:: ነገር ግን በቴክኒካዊ ችሎታ (Spatial skills) አኳያ የሚታየው የጾታ ልዩነት ተፈጥሮአዊ ተፅዕኖ (Biological effect) እንዳለው ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ገልፀዋል::

የቴክኒክ ወይም የሙያ ችሎታ ከአካላዊ ብቃት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ይህ ችሎታ ከወንዶች ተግባር የሚመደብ መሆኑንም አክለው ገልፀዋል:: ምክንያቱም ወንዶች ከህፃንነታቸው ጀምሮ ለሙያና ለቴክኒክ ስራዎች የተጋለጡ በመሆናቸው ከሴቶች ይልቅ በሙያና በቴክኒክ ችሎታዎች የተሻሉ ናቸው:: በዚህም የሚታየው ልዩነት ውጤቱ አስተማማኝ መሆኑን Golombok and Fivush (1994), Baenaenger and New Combe (1989) እና Halpern (1992) ን በመጥቀስ፣ Betz and Fetzegerald (1987) አሳይተዋል::

ከዚህ በተጨማሪም ቴክኒካዊ ችሎታን ለማዳበር የሚያስችል በጉርምስና ጊዜ የሚዳብር ሆርሞን በወንዶች ውስጥ በመኖሩ ቴክኒካዊ ችሎታ የወንዶች ተግባር ነው ሲሉ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ያስረዳሉ:: ስለዚህም የልዩነቱ መንስዔ አንዱ ተፈጥሮአዊ ተጽእኖ መሆኑን ከገለጻው ለመረዳት ይቻላል፤ ነገር ግን ይህ ተፈጥሮአዊ ተጽእኖ ብቻውን በወንዶችና በሴቶች መካከል ለሚኖረው የቴክኒክ ችሎታ ልዩነት መንስዔ ሊሆን እንደማይችልና ማህበራዊና ባህላዊን ሁኔታዎችም አጋዥ ምክንያቶች መሆናቸውን ምሁራኑ አክለው አስረድተዋል::

ለዚህም ምሳሌ Golombok and Fivush (1994) የጠቀሱትን ስናይ፣ በማህበረሰቡ ባህልና እምነት መሠረት ወንዶች ከሴቶች በተለየ ሁኔታ ውስብስብ በሆኑ ቦታዎችና ሁኔታዎች ያድጋሉ:: እንዲሁም ከቤት ውጭ ይወጣሉ፣ ይጫወታሉ:: የተለያዩ አስቸጋሪና ሰፊ ቦታዎችን የመጎብኘት ነጻነት ይሰጣቸዋል:: በህጻንነታቸውም ቴክኒካዊ ውስብስብነት ባላቸው መጫወቻዎች ለምሳሌ ከመገንባት ከማንጸ ጋር በተያያዙ መጫወቻዎች ይጫወታሉ:: በዚህ መልክ የሚዳብር የቴክኒክ ልምምድ ከአደጉ በኋላ ለሚኖራቸው ቴክኒካዊ ችሎታ መሠረት እንደሚሆን ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ይገልጻሉ::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ Warrick and Jack(1993) የጾታን ልዩነት ከትምህርት ችሎታ አንጻር ለማየት ባደረጉት ጥናት ያገኙት ውጤት ሴቶች በማድመጥ፣ በማንበብና በማየት፣ ወንዶች በመናገርና በመጻፍ ችሎታዎች የተሻለ ውጤት ማስመዝገባቸውን የሚያሳይ ነው:: ነገር ግን በሀገራችን በተደረጉ ጥናቶች ለምሳሌ ፋንቱ ደምሴ(1989) በቋንቋ መማር ረገድ የጾታን ልዩነት በመረመሩበት ወቅት ያገኙት ውጤት ከላይ ከተገለፀው የተለየ ነበር:: ይህም በቋንቋ መማር ረገድ በሴቶችና በወንዶች መካከል ልዩነት የለም የሚል ነው::

ከላይ የተለያዩ ጥናቶችንና አተኗዎችን በመጥቀስ ለማሳየት እንደተሞከረው በተለይ ቢቃላዊ ችሎታ አንጻር የሚታይ የጾታ ልዩነትን በተመለከተ የተደረጉ ጥናቶች ሁለት ተቃራኒ ሁሳቦችን እንዳስገኙ መገንዘብ ይቻላል:: ይህም ለምሳሌ Maccoby and Jacquline (1974) በቃላዊ ተግባራት ሴቶች ከወንዶች የተሻለ ውጤት ማስገንዘባቸውን ሲገልጹ ሌሎች ደግሞ ለምሳሌ Warrick and Jack(1993) በመናገርና በመጻፍ ክሂል ወንዶች፣ በማየትና በማንበብ ክሂሎች ደግሞ ሴቶች የተሻሉ መሆናቸውን ገልጸዋል:: ስለዚህ በመጀመሪያ የተጠቀሱት ምሁራን ቃላዊ ተግባራት ሲሉ ንግግርን የሚያዘ በመሆኑ ቀጥለው ከተጠቀሱት ምሁራን የጥናት ግኝት ጋር የሚቃረን ውጤት ማግኘታቸውን መረዳት ይቻላል:: ሆኖም በእነዚህ የቋንቋ ክሂሎች የሚታየው

የጾታ ልዩነት ከጉርምስና/ከሩርድና የዕድሜ ክልል በፊት የማይታይ መሆኑን በተለያዩ አካባቢዎችና ማህበራዊ ሁኔታዎች ውስጥ ከተደረጉ ጥናቶች የተገኙ መረጃዎች ያሳያሉ። ልኘተተ (1987), Maccoby and Jacquline (1974)።

ይህን በሚመለከት Betz and Fetzegerald (1987) ሲገልጹ ለተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች በሚኖር አመለካከት ዝንባሌና ውጤት ረገድ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል የሚታይ ልዩነት ልጆቹ ማህበረሰቡ በባህሉ መሠረት ከወንዶችና ከሴቶች ምን እንደሚጠብቅና ለሁለቱም ጾታዎች ተገቢ ነው ተብሎ የተወሰነላቸው ተግባር ምን እንደሆነ ሊረዱ እስከሚችሉበት የጉርምስናና የኩርድና የዕድሜ ክልል ድረስ ሊታይ እንደማይችል ያረጋግጣሉ።

በአጠቃላይ በትምህርት ችሎታ ረገድ የጾታን ልዩነት በተመለከተ የተለያዩ ጥናቶች የሚጠቁሙት ከላይ ለመግለጽ የተሞከረውን ሲመስል በቋንቋ ትምህርትም የጾታን ልዩነት የመረመሩ ጥናቶች በአእምሮአዊ ተግባራት (cognitive skills) ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚኖርን ልዩነት በሚመለከት ስፊ ጥናት ያደረጉ መሆናቸውን የሚጠቁም ሀሳብ ቀደም ብሎ ተገልጿል። በዚህም በቃላዊና ሥነልሳናዊ ችሎታዎች ሴቶች ከወንዶች እንደሚበልጡ Maccoby and Jacquine (1974) ገልጸዋል። ቢሆንም ቃላዊ ችሎታ ለሚለው እሳቤ ግልጽ ያለ ብያኔ ባለመስጠታቸው ጥናታቸው ተቀባይነት የለውም ሲሉ Warrick and Jack (1993) Witting and Pettersen (1979)ን በመጥቀስ ትችት ሰንዝረዋል።

በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የመምህር ተማሪ ተራክቦን በሚመለከት ደግሞ የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠን የመረመሩ አጥኚዎች እንዳመለከቱት ጥያቄ በመጠየቅ፣ ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት፣ ሀሳባቸውን ዘርዝርና ስፋ አድርገው በመግለጽ ረገድ ሴቶች ከወንዶች ያነሱ ናቸው። Golobok and Fivush (1994), Sunderland (1992፣1994), Lott (1987), Coates(1986), Irvine (1986), Potter (1978) እና ሌሎችም ከላይ የተገለጸውን ሀሳብ የሚያጠናክሩ ናቸው።

ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶችን Tsge Haile (1991)፣ Clerk and Tranford (1995) Lott (1987) Betz and Fetzegerald (1987) Lindros (1995) እና ሌሎቹም እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

ሴቶች ተማሪዎች በወንዶች ጓደኞቻቸውና በመምህሮቻቸው ፊት ለመናገር አለመድፈር፣ መምህሮቻቸው ሲመልሱም ሆነ ሲጠይቁ ከወንዶች እኩል ስለማያበረታቷቸው ለዚህ በምሳሌነት Golombok and Fivush (1994), Good and Brophy (1987:596-597) ከአንድ መማሪያ ክፍል ውስጥ ያደረጉትን ጥናት በመጥቀስና ለአብነት በመውሰድ እንደሚከተለው አቅርበዋል። ይህም የጥናቱ ተመራማሪ ምልከታውን ባካሄዱበት ወቅት መምህሩ አራቱን የአመቱ ወራት በትምህርትነት ይሰጡ ነበር። በዚህም ትምህርት ሂደት መምህሩ ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ምጋቢ ምላሽ የተለያየ መሆኑን የሚያሳይ እንደነበር ምሳሌው ያስረዳል፣

መምህር፡-  "ካሮል! በአመት ውስጥ ስንት ወራት አሉ?"

ካሮል፡-  "ሶስት"

መምህር፡-  "አይደለም። ባለፈው የፃፋችሁት ከሶስት የሚበልጥ ነው፡ "ትንሽ አስብ።"

ካሮል፡-  "አራት"

መምህር፡-  "ጥሩ! ስማቸውን ልትጠራልኝ ትችላለህ?"

ካሮል፡  ( ሶስቱን መለሰ)

መምህር፡-  "አራቱን አልጻፍከም?"

ካሮል፡  "አላስታውስም"

መምህር፡-  "እንደገና አራቱንም እንድትጽፍ፤ አራቱን የሚያውቅ ማነው?
ጆን "ትመልሳለህ?"

ጆን፡  (አራቱን መለሰ)

መምህር፡  ጥሩ "አስታውስሃል"

ከዚህ በላይ ከተጠቀሰው የመምህር ተማሪ ተራክቦ ዘርፍ በመጀመሪያ የተጠየቀው ተማሪ መልሱን ባለማወቁ እንደገና እንዲሞክር እድል በመስጠት መምህሩ እንዲበረታታ ማድረጋቸውን ተገንዝበናል። ከዚህ ቀጥሎ የቀረበው የመምህር ተማሪ ተራክቦ ደግሞ በመምህርና በሴት ተማሪ መካከል የተደረገ ንግግር ሲሆን የመምህሩ ምላሽ ከላይ ከቀረበው ለየት ያለ ነው። ትምህርቱ ስለ አመቱ ወራትና የበአል ቀን ስሞች ነበር፤

መምህር፡  የ "ፎል ሲዝን" ሌላ መጠሪያው ምን ይባላል? ሊኒ!

ሊኒ፡  " "ሀሎዊን"

መምህር፡  የበአል ስም አልጠየቅኩሽም! ሌላ መጠሪያ ቃሉን እንጂ?

ሊኒ፡  (መልሱን እንደማታውቀው ገለፀች)

መምህር፡  "ጥቁር ሰሌዳው ላይ እጽፈዋለሁ፤ ሮቢ ያነበዋል ተመልከቱ!"

ሮቢ፡  (መልስ አልሰጠም።)

መምህር፡  "የሚታወስ ቃል ነው ሮቤ! እረዳሀለሁ!"

ከላይ ከተጠቀሱት ምሳሌዎች የምንገነዘበው መምህሩ ለወንድና ሴት ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ያላቸው አመለካከት የተለያየ ከመሆኑ ባሻገር መምህሩ ከሴት ተማሪዎች ይልቅ ለወንዱ ተማሪ የበለጠ ማበረታቻና ምጋቢ ምላሽ የሚሰጡ መሆኑን ነው፤ ምክንያቱም በመጀመሪያው የመምህር ተማሪ ተራክቦ የተጠቀሰው ተማሪ "ካሮል" ለተጠየቀው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ አልሰጠም። በሁለተኛውም የተጠቀሰችው ተማሪ "ሊኒ" ትክክለኛ መልስ አልሰጠችም። ለሁለቱ ተማሪዎች የመምህሩ ምላሽ ግን የተለያየ እንደነበር ከምሳሌው አይተናል። ይህም ተማሪ ካሮል፤ ጥያቄውን እንደገና እንዲሞክር ሌላ እድል ተሰጠው። ተማሪ ሊኒ ግን ሌላ እድል አልተሰጣትም። በተጨማሪም ተማሪ "ሮቢ" መልስ ሳይሰጥ ሲቀር እንዲመልስ አበረታቱት። ስለዚህ ከዚህ ሁኔታ በመነሳት ምሁራኑ ለሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተራክቦ አነስተኛ መሆን ዋናው ምክንያት መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች

የሚሰጡት ትኩረትና የሚኖራቸው አመለካከት የተለያየ በመሆኑ ነው ሲሉ ገልፀዋል።

ሌላው ምክንያት ሴቶች ተማሪዎች ለመናገር በሚሞክሩበት ጊዜ መምህሮቻቸውና ወንዶች ጓደኞቻቸው በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ስለሚያቋርጧቸው ሲሆን ለዚህም ምሳሌ Lindros (1995:153) በእንግሊዝኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ የተማሪዎችን ንግግር መቋረጥ በሚመለከት ባደረጉት ጥናት በክፍል ውስጥ ያስተዋሉትን እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡

> መምህሩ በሚያስተምሩበት ክፍል ውስጥ ወንዶች ተማሪዎች በሚናገሩበት ወቅት በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት አያቋርጧቸውም። እንዲያውም ለሀሳባቸው ድጋፍ በመስጠት ሁኔታው የውይይት መልክ እንዲይዝ ያደርጋሉ። ሴቶች ተማሪዎች በሚናገሩበት ወቅት ግን መምህሩ ብቻ ሳይሆኑ ወንዶች ተማሪዎችም በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግራቸው በተደጋጋሚ እንዲቋረጥ ያደርጋሉ።

ከላይ ከተቀሰ እንደምንረዳው፣ ሴቶች ተማሪዎች በሚናገሩበት ጊዜ መምህራኑም ሆኑ ወንዶች አቻዎቻቸው ንግግራቸውን ስለሚያቋርጡባቸው ለመናገር አይደፋፈሩም።

ከእነዚህ ሌላ ደግሞ በሴት ተማሪዎች ትምህርት አቀባበል ላይ ማህበረሰቡ ያለው አሉታዊ አመለካከት፣ የማህበረሰቡ ባህል የሚያሳድርባቸው ተፅዕኖ፣ መምህራን ብዙ ትኩረት የሚሰጡትና በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ሁኔታ ብዙ ግንኙነት የሚኖራቸው ከወንዶች ተማሪዎች ጋር በመሆኑ (Good and Brophy 1973:75) ና በዚህም በመማክ ውስጥ በሚደረገው የመምህር ተማሪ ቃላዊ ተራክቦ በወንዶች ተማሪዎችና በመምህራን መካከል ብቻ ተወስኖ የሚቀር በመሆኑ፣ ሴቶች ተማሪዎች ከመማር ማስተማሩ ሂደት የተገለሉ ናቸው። ለዚህም ምክንያቱ መምህራን የማህበረሰቡ አካል በመሆናቸውና ማህበረሰቡ ለሴት ተማሪዎች ትምህርት አቀባበል ያለውን አሉታዊ አመለካከት ስለሚያንፀባርቁ፣ ወንዶችን ከሴቶች የተሻለ ግንዛቤ ያላቸው አድርገው ስለሚገነዘቡ ብዙውን ጊዜ እንዲሳተፉ እድል የሚሰጡት ለወንዶች ተማሪዎች ብቻ በመሆን ነው። Potter (1978), Sunderland (1994)።

ይህን በተመለከተ Spender (1982) በሴት ተማሪዎች የመማሪያ ክፍል ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ ከወንዶች በጣም ያነሰ መሆኑን ሲገልፁ፣ ሴቶች ተማሪዎች፣ ምናልባትም ወንዶች በመማክ ውስጥ የሚያደርጉትን ንግግር ግማሽ ያህል ቢናገሩ በወንዶች ተማሪዎች ዘንድ የሚኖረው ግምት የንግግሩን የበላይነት የወሰዱት ሴቶች ናቸው የሚል ነው። ከዚህ ሀሳብ የምንረዳው ሴቶችና ወንዶች ተማሪዎች በመማክ ውስጥ በሚያደርጉት ቃላዊ ተራክቦ በመካከላቸው የጎላ ልዩነት ያለ መሆኑን ነው። ለዚህ ምሳሌ Spender (1982) በአንድ "ወርክሾፕ" ውስጥ 32 ሴቶችና 5 ወንዶች በሚያደርጉት ንግግር የወንዶችና የሴቶችን ተራ አወሳሰድ (Turn-takings) በሚመለከት ባካሄዱት ጥናት አስደናቂ ውጤት ማግኘታቸውን ይገልፃሉ። በዚህም በጠቅላላው ከተደረገው የ58 ደቂቃ ንግግር፣ 32 ደቂቃውን የወሰዱት ወንዶች

መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል። ስለዚህ ከዚህ ምሳሌ የምንረዳው በመማክ ውስጥም ሆነ ውጭ ወንዶችና ሴቶች በሚያካሂዷቸው ውይይቶች የንግግሩን የበላይነት የሚወስዱት ወንዶች ተማሪዎች መሆናቸውን ነው።

ከዚህ አንፃር በተለይም ቋንቋን በመማር ሂደት ላይ ትኩረት ለመስጠት በሚታሰብበት ጊዜ ሊታይ የሚችለው ጉዳይ በክፍል ውስጥ ተራክቦ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል የቃላዊ ተሳትፎ ልዩነት እንዳይኖር መምህራን ተማሪዎችን እኩል ማሳተፍ እንደሚኖርባቸውና በሚሰጡትም ምዘና ምላሽ የጾታ ልዩነት (ጾታዊ አድሎ) እንዳይኖር መጠንቀቅ እንዳለባቸው የሚያሳስብ ነው። ምክንያቱም እንደ በርካታ ምሁራን አገላለፅ ሴቶች ተማሪዎች በመማክ ውስጥ የመናገር ልምምድ ስለሌላቸው፣ መምህራንም ትኩረት ስለማይሰጧቸውና በዚህም ለራሳቸው የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ Sunderland (1994:150) ከትምህርት ቤት ውጭም በሚያጋጥሟቸው የውይይት ተግባራት የመሳተፍ እድላቸው ዝቅተኛ ይሆናል። ስለዚህ የመማክ ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ ለመማር ሂደትም አስፈላጊ በመሆኑ መምህራን ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎችን እኩል ማሳተፍ እንደሚኖርባቸው Spender (1982) ያስገነዝባሉ።

አንዳንድ መምህራንም ስለሴቶች ተማሪዎች የመማክ ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በክፍል ውስጥ እርስ በርስ ከሚያደርጉት ወሬ በስተቀር በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚካሄደው የመምህር ተማሪ ተራክቦ ተሳታፊ አለመሆናቸውን የሚያሳይ ነው። ሲሉ ከላይ የተጠቀሱት ምሁራን ያስረዳሉ። እንደዚሁም ሴቶች ተማሪዎች ራሳቸው ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሴቶች ከወንዶች እኩል ከተናገሩ ወይም ንግግር ካደረጉ የሴትነት ባህሪያቸውን የተው ስለሚመስላቸው ከመናገር እንደሚታቀቡ አስረድተዋል። Spender (1982)

እንዲሁም በለንደን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ልጃገረዶች የመማክ ውስጥ ቃላዊ ተራክቦን በሚመለከት ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ሴቶች ከወንዶች እኩል ማውራት የአ. ሴትነት ባህርይ ነው የሚል ነው። ስለዚህም ከተለያዩ ምሳሌዎችና የጥናት ግኝቶች የተገኙት ውጤቶች እንደሚያሳዩት፣ ወንዶች ተማሪዎች ከሴቶች የበለጠ ለተጠየቁ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ምላሽ ይሰጣሉ፣ ጥያቄ ይጠይቃሉ፣ መምህሩን ይቃወማሉ፣ ሴቶች በተቃራኒው ከዚህ ሁሉ ተግባር የተገለሉ ወይም የራቁ ናቸው።

Sunderland (1994), Julia Batters (1987)ን በመጥቀስ እንደገለፁት ደግሞ በብሪቲይን የዘመናዊ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በተደረገ ጥናት የተገኘው ውጤት ሴት ተማሪዎች ብዙውን ጊዜ የሚሳተፉት በአትኩሮት ክንዋኔዎች (Attentive activities) ሲሆን እነዚህም፡- መመልከት፣ ማዳመጥ፣ ማንበብ ናቸው። ወንዶች ደግሞ በተሳትፎአዊ ተግባራት (Participative activities) እና በቃላዊ ተግባራት (Verbal skills) የበለጡ ናቸው የሚል ነው።

በተጨማሪም Kelly (1988) በመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የተደረጉ 81 ጥናቶችን በመገምገምና ሰፋ ያለ ትንታኔ በመስጠት ያጠቃለሉትን ስንመለከት፣ በሁሉም የእድሜ ክልል

ውስጥ የሚገኙ ሴቶች ተማሪዎች በብዙ ሀገሮች፣ የተለያየ ማህበረ-ኢኮኖሚያዊ ዳራ ባላቸው ቡድኖች መካከል በሁሉም የትምህርት አይነቶችና ወንዶችና ሴቶች በሚያስተምሩባቸው መማሪያ ክፍሎች ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ቃላዊ ተራክቦ ሴቶች የሚወስዱት ተራ (Turn-Takings) ከወንዶች በጣም ያነሰ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው:: የመምህራኑንም ትኩረትና ምጋቢ ምላሽ በሚመለከት መምህራን ለሴት ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ምጋቢ ምላሽ በጣም ያነሰ ነው:: እንዲሁም ሴቶች ተማሪዎች ጥሩ ፀባይ በማሳየታቸው ሲመሰገኑ፣ ወንዶች ለጥያቄዎች መልስ በመስጠታቸው ይሞገሳሉ:: ሌላው ደግሞ ወንዶች በመጥፎ ባህርይ ሲወቀሱ ሴቶች ትክክለኛ መልስ ባለመስጠታቸው ይወቀሳሉ:: ከዚህ ሀሳብ የምንገነዘበው መምህራን ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ምጋቢ ምላሽ በመጠን ብቻ ሳይሆን በአይነትም የተለያየ መሆኑን ነው Golobok and Fivush (1994)::

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተለያዩ ጥናቶችን በመጥቀስ ለማሳየት የተሞከረው በመማሪያ ክፍል ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ የጾታ ልዩነት መኖሩንና በዚህም የሴት ተማሪዎች ቃላዊ ተራክቦ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ነው:: ይህም በክፍል ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ ላይ የወንዶች የበላይነት ከመታየቱም በተጨማሪ መምህራንም የበለጠ ትኩረትና የተሻለ ምጋቢ ምላሽ የሚሰጡት ለወንዶች ተማሪዎች ብቻ መሆኑን በተለያዩ ሀገሮች የተደረጉ ጥናቶች ያስገኟቸው ውጤቶች ያሳያሉ:: በዚህም የማስተማሩን አጠቃላይ ሂደት፣ ጠለቅና ደረጃቸው ከፍ ያለ ጥያቄዎችን፣ ትምህርት ነክ ትችቶችን (Academic criticism) ፣ የበለጠ ሙገሳና ባህሪያዊ ትችት (Behavioral criticism) የሚያገኙት ወንዶች ተማሪዎች መሆናቸውን ምሁራኑ ይገልፃሉ::

በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የጾታን ልዩነት በሚመለከት ሌላው ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ ለተጠየቁ ጥያቄዎች በሚሰጧቸው መልሶች ምክንያት በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት የመኖሩ ጉዳይ ነው:: ለዚህም በመስኩ ላይ ምርምር ያካሄዱ በርካታ አጥኚዎች እንደሚጠቁሙት ሴቶች በተደጋጋሚ የሚመልሷቸው ጥያቄዎች አጭር፣ ማስብና ማስላሰል የማይጠይቁና በአንድ ቃል ብቻ የሚመለሱትን ሲሆን ወንዶች ግን በተቃራኒው ዝርዝርና ረዘም ያለ፣ ምክንያትን የሚፈልጉ ጥያቄዎችን በመመለስ እንደሚሳተፉ የሚያሳይ ነው:: በዚህ ምክንያት ወንዶች ተማሪዎች በመማክ ውስጥ ተራክቦ ብዙውን ጊዜ የሚወስዱት ከሚመልሱት መልስ መርዘምና ዝርዝር ማለት ሁኔታ እንፃር መሆኑን እንረዳለን::

ከዚህ በተጨማሪም ሴቶችና ወንዶች በመማክ ውስጥ በሚካሄድ የመምህር-ተማሪ ተራክቦ በሚያደርጉት ተሳትፎ ከሚለያዩባቸው ነገሮች ሌላው ሴቶች ብዙውን ጊዜ ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ በመስጠት ብቻ የሚሳተፉ ሲሆን ወንዶች ግን መልስ በመስጠት ብቻ ሳይሆን ያልገባቸው ጥያቄ በመጠየቅም ከሴቶች የበለጠ ተሳታፊዎች መሆናቸውን John and Glendinning(1996) በዚህ መስክ ሰፊ ጥናት ያካሄዱትንና የመስኩ መስራች የተባሉትን Good and Brophy (1970)ን በመጥቀስ አመልክተዋል::

ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች በሚማሩት የትምህርት አይነት ምክንያትም በተራክቦ የተለያዩ መሆናቸውን Woods and Hammerssely (1993) ገልፀዋል:: ይህም ሴቶች በንባብ ትምህርት፣ ወንዶች በሂሳብ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ከመምህሩ ጋር በሚያደርጉት የመምህር ተማሪ ተራክቦ የተሻሉ መሆናቸውን ያስገነዝባሉ::

## 2.4. መምህሩን ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት /Teacher treatment/ እና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ /Verbal fedback/ መለያየት ከተሳትፎአቸው ጋር ያለው ግንኙነት

ጾታንና የመማክ ውስጥ ተራክቦን በሚመለከት ከመምህሩ አያያዝ ወይም ትኩረት /Teacher treatment/ አንፃር ምርምር ያካሄዱ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ በወንዶችና በሴቶች መካከል የጎላ ልዩነት እንጂ ተመሳሳይነት የለም:: ለዚህም ለምሳሌ በኬንያ ትምህርት ቤቶች የክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ የጾታን ልዩነት የዳሰሱ ጥናቶች ግኝት አትጣጫ እንደሚጠቁመው መምህሩን አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ጾታዊ አድሎ ያደርጋሉ:: Kabira's and Masinjilay (1997), King and Hill (1993)::

በዚህም መምህሩን በመማር ማስተማሩ ሂደት ከተማሪዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የመማሪያ ክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ ለተማሪዎቹ ከሚሰጡት ትኩረት መጠን (ለምሳሌ ተማሪዎቹ ጥያቄ እንዲመልሱም ሆነ እንዲጠይቁ በተደጋጋሚ እድል መስጠት፣ ማበረታታት፣ ማሞገስ፣ መተቸት ወዘተ.) እና የትኩረቱ አይነት (ለምሳሌ ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚጠይቋቸው ጥያቄዎች መለያየት ይህም ሴቶችን አጭርና ሂደትን የማያሳዩ ጥያቄዎችን (Product questions) ወንዶችን ደግሞ ዘርዘርና ሂደትን ማሳየት የሚያስፈልጋቸው ጥያቄዎችን (Process questions) የሚጠይቁ መሆኑን በማሳየት አንፃር የጾታን ልዩነት የመረመሩ በርካታ ጥናቶች በመማክ ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ ላይ ለሚታየው የጾታ ልዩነት ዋናው መንስኤ መምህሩን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ትኩረት የተለያየ መሆኑ ነው በማለት ያስረዳሉ::

Sunderland (1994) በቋንቋ መማክ ውስጥ በሚደረግ ቃላዊ ተራክቦ የወንዶች ተሳትፎ በልጦ መታየት፣ መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች በሚሰጡት እኩል ያልሆነ ትኩረት ወይም አያያዝ (Unfair treatment) መሆኑን አክለው ይገልፃሉ:: ይህን የጥናት ውጤት የሚቃረን ግኝት Ehrlich(1997) Sunderland (1995)ን እንደጠቀሱት፣ በቋንቋ መማክ ውስጥ የተማሪዎችን ቃላዊ ተሳትፎና የመምህሩን አያያዝ በሚመለከት የሚከተለውን ገልፀዋል፣ "ወንዶችና ሴቶች አብረው የሚማሩበት የቋንቋ መማሪያ ክፍል "ዲስኮርስ" ባህርይ የሚታይበት ነው:: ስለሆነም ከሌሎች ትምህርቶች መማክ በተሻለ ሁኔታ ሴቶች ተማሪዎች ንግግር ያደርጋሉ፣ የበለጠና የተሻለ አይነት የመምህሩን ትኩረት ይወስዳሉ::" ይህን በሚመለከት Sunderland (1995) የጥናታቸውን ውጤት ከጾታዊ አመለካከት አንፃር ሲገልፁም በቋንቋ ክፍል

ውስጥ ቢቃላዊ ተራክቦም ሆነ በመምህሩ አያያዝ ወይም ትኩረት የሴቶች የበላይነት መኖሩን መምህራን ይመለከታሉ በማለት ነው:: በተለይም በጣም የቅርብ ጊዜ ጥናታቸው በሆነው በውጭ ቋንቋ መማክ ውስጥ የተማሪዎቹ አፍ መፍቻ ቋንቋ ጀርመንኛ በሆነበት ክፍል በ1998 ባካሄዱት ጥናት በሁሉም መማሪያ ክፍሎች ውስጥ በሚደረግ የመምህር-ተማሪ ተራክቦ የወንዶች የበላይነት አይታይም:: ሴቶችም በተለያየ አይነት ጥሩ ተሳትፎ ያደርጋሉ ሲሉ ሪፖርት አድርገዋል:: Sunderland (1998)

ሌሎች ምሁራን ደግሞ ለምሳሌ John and Gledning (1996), Sunderand(1994), Spender (1982) ን በመጥቀስ Kelly (1988) በመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የጾታን ልዩነት ከመምህሩ ሙገሳና ተችት፣ እንዲሁም ትኩረት አንፃር ባደረጉት ምርምር መምህራን ለሴቶች ተማሪዎች የሚያደርጉት አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ትኩረት በጣም ያነሰ መሆኑን አመልክተዋል:: በዚህም ሴቶች ተማሪዎች በትምህርታቸው ጎበዝ፣ ወይም ጠንካራ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ለመሳተፍ የሚተጉ፣ ፍላጎቱም ያላቸው ቢሆንም ከመምህሮቻቸው የሚያገኙት ምጋቤ ምላሽ ግን ከወንዶች ያነሰ እና ተቀራኒ በሆነ መልክ ነው:: ይህም ሴቶች ተማሪዎችን ተስፋ የሚያስቆርጥና ከመማር ማስተማሩ ሂደት የተገለሉ እንዲሆኑ የሚያደርግ ሲሆን ለወንዶች ግን የሚያበረታታ መሆኑን ምሁራኑ ያስረዳሉ::

በተጨማሪም Irvin (1986), Simpson and Erikson (1983)ን በመጥቀስ የመምህሩን ቃላዊናኢ-ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከተማሪዎቹ ዘር፣ ጾታና ከመምህሩ ጾታ አንፃር ተመልክተው በተለይ ከተማሪዎች ጾታ አንፃር የታየውን ልዩነት በተመለከተ መምህራን ቃላዊም ሆነ ኢ-ቃላዊ ሙገሳ፣ ትችት ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች እንደሚያደርሱ ገልፀዋል:: መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን የተለያየ ትኩረት በሚመለከት የተጠናቀሩ መረጃዎች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረት እንደሚያገኙ ያሳያሉ ሲሉ Potter (1978) የገለፁትንም እናገኛለን:: በዚህ ላይ ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች ያነሰ ተሳትፎ የሚኖራቸው መምህራን ትኩረት ስለማይሰጧቸው ሳይሆን ሴቶች ከወንዶች የበለጠ የሚሰጡት መልስ የተሳሳተ ስለሚሆን ነው በማለትም የመምህሩ ትኩረት ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተራክቦ ጋር ግንኙነት የለውም ወደሚል ድምዳሜ ላይ ይደርሳሉ:: ነገር ግን የበርካታ ጥናቶች ግኝት የሚያሳየው በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ ለሚታየው የጾታ ልዩነት ዋናው ምክንያት የመምህሩ ትኩረት ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የተለያየ በመሆኑ ነው የሚል ነው::

በአጠቃላይ መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት የትኩረት መጠን ተደምሮና በመቶኛ ተሰልቶ ሲታይ የወንዶች 51%፣ የሴቶች 49% መሆኑን Sunderland (1994) ሌሎች ጥናቶችን በመጥቀስ ገልፀዋል:: ቢሆንም የሚታየው ልዩነት የጎላ አይደለም ሲሉ አስተያየታቸውን ሰንዝረዋል:: Kelly (1988) ይህን በመቃወም በመማር ማስተማሩ ሂደት የመምህራን ትኩረት ሙሉ በሙሉ በወንዶች ተማሪዎች ላይ ብቻ መሆኑን ባካሄዱት የብዙ ጥናቶች ግምገማ ገልፀዋል:: ይህም ሁኔታ መምህራን ሳያውቁ ማለትም ለወንዶች ተማሪዎች የበለጠ ትኩረት ለመስጠት አስበው ሳይሆን በአጋጣሚም የሚፈጠር መሆኑን አክለው አመልክተዋል::

ስለዚህም Kelly (1988) እና Holmes (1994) በ Ehrlich (1997) እንደተጠቀሱት፣ Golombok and Fivush (1999) ፣ እና ሌሎችም እንደገለፁት ሴቶች ተማሪዎች በመማክ ውስጥ ለሚኖራቸው ተሳትፎ ከመምህሩ የሚያገኙት ምላሽ በሚናገሩበት ጊዜም ንግግራቸው እንዲቀጥል የሚያገኙት ማበረታቻ ከወንዶች በጣም ያነሰ ነው:: በዚህም ሴቶች ከመምህሩ የሚያገኙት ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ በክፍል ውስጥ በሚደረግ ውይይት ተሳትፎአቸው በጣም ዝቅተኛ ይሆናል:: ከዚህ አንፃር በመምህሩና በተማሪዎች መካከል በሚደረግ ተራክቦ ተደጋጋሚ ተራ የሚወስዱት ወንዶች ብቻ ናቸው የሚለው የ Potter(1987) ሀሳብ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ Bank and Hall (1997:139-149) "ሴቶች ተማሪዎቸ በመማክ ውስጥ የማይታዩ የክፍሉ አባላት (Invisible Members of the Class Room ) ናቸው::" ሲሉ የገለፁትን እናገኛለን:: በተጨማሪም መምህራን የተሻለ ጥያቄ የሚጠይቁት በተደጋጋሚ ስማቸውን የሚጠሩት፣ አጭርና ገንቢ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት ለወንዶች ተማሪዎች ብቻ መሆኑንም ከላይ የተጠቀሱት ምሁር ያስረዳሉ:: በዚህም ሴቶች በክፍል ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ የተገለሉ፣ ለሚኖራቸውም ተሳትፎ ትኩረት የማይሰጠውና ዋጋ የማይኖረው (Under Valued) ነው በማለትም ይገልፃሉ::

በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ የጾታን ልዩነት በሚመለከት የተደረጉ ሌሎች ጥናቶች ደግሞ ከላይ ከተገለፀው ሀሳብ የተለየ ውጤት ማግኘታቸውን መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ለምሳሌም John and Glendinning (1996) የገለፁት የመምህሩ ትኩረት ከተማሪዎች ጾታ ጋር ሳይሆን ከተማሪዎቹ ችሎታ መለያየት ጋር ግንኙነት ያለው መሆኑን የሚያሳይ ነው:: በዚህም ንቁ ተሳትፎ ያላቸውና ጎበዝ ተማሪዎች ከደካማዎቹ የበለጠ የመምህራንን ትኩረት ይስባሉ:: ስለዚህም ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ መለያየት ካላቸው የችሎታ መለያየት ምክንያት እንጂ በጾታቸው ምክንያት አለመሆኑን ገልፀዋል::

ይህን ሀሳብ በሚመለከት ለዚህ ጥናት መረጃ ለማግኘት በተደረገው ምልከታና ከአንዳንድ መምህራን በተገኘው ጥቆማ መሰረት ተማሪዎች ከመምህሩ ጋር ለሚኖራቸው ቅርበት

ዋናው የተማሪዎቹ የትምህርት አቀባበልና በውጤታቸው የተሻሉ ሆኖ መገኘት መሆኑን ለመገንዘብም ተችሏል:: ይህም ከላይ የተጠቀሱትን ምሁራን ሀሳብ የሚደግፍ ሆኗል::

Maccby (1990) በአሜሪካን ሀገር በአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ላይ ያደረጉት ጥናት ደግሞ ሴቶች ተማሪዎች በውጤታቸውም ሆነ በመማክ ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች የተሻሉ በመሆናቸው የመምህራኑንም ትኩረት ከወንዶች የበለጠ የሚወስዱት ሴቶች ተማሪዎች እንደነበሩ ጥናታቸውን ባካሄዱበት ክፍል ውስጥ ያስተዋሉትን ገልፀዋል:: ነገር ግን ይህ ሀሳብ ከላይ የተገለፀውን የሚደግፍ ቢሆንም ይህን የመሰለ ውጤት በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች ላይ ተጠንቶ ተመሳሳይ ውጤት ያልታየ በመሆኑ ለአብነት መውሰድ ያስቸግራል የሚል አስተያየትም ሰንዘረዋል::

ከዚህ በተጨማሪም Irvin (1986) Brophy and Evers ton (1981) ን በመጥቀስ የተማሪዎች ፊርተ ቀደድ ባህርይ፣ የመምህሩን ምጋቤ ምላሽና ተማሪዎች መልስ ለመስጠት የሚያገኙትን እድል በሚመለከት ከጾታና ከዘር ጉንቅር አንፃር ባደረጉት ጥናት ጾታን በተመለከተ ወንዶች ተማሪዎች ከሴቶች ተማሪዎች የበለጠ ፊርተ ቀደድ ባህርይ ሲኖራቸው ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠትም ተደጋጋሚ እድል የሚያገኙት እነሱ መሆናቸውን ገልፀዋል:: ለዚህም የሰጡት አስተያየት ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች በመማክ ውስጥ በሚኖራቸው ተራክቦ መጠን ሊለያዩ የሚችሉት ባላቸው የመማር ባህርይ መንስኤንት ነው የሚል ሲሆን ንቁ ተሳትፎ ያላቸውና ነበዝ ተማሪዎች ከመምህሩ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት ንቁ ተሳትፎ ከሌላቸውና ከደካማዎቹ የበለጠ መሆኑንም አክለው ገልፀዋል:: ምክንያቱም በተሳትፎ ዝቅተኛ የሆኑና ደካማ ተማሪዎች ከመምህሩ ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት እልፎ እልፎ ወይም ምንም ግንኙነት የሌላቸው በመሆን ስለነዚህ ተማሪዎች መምህሩ ጠለቅ ብለው ስለማያውቁ በተራክቦም አነስተኛ የሆኑና የመምህሩንም አነስተኛ ትኩረት የሚወስዱ መሆናቸውን ምሁሩ ያስረዳሉ::

በአጠቃላይ የተማሪዎቹ የመማር ባህርይ፣ ማለትም የትምህርት ችሎታ ከፍተኛና ዝቅተኛ መሆን በተራክቦአቸው ላይ ተፅዕኖ እንዳለው የሚገልፁ አንዳንድ ምሁራን ቢኖሩም እንደአብዛኛዎቹ ተመራማሪዎች አገላለፅ ግን የመምህሩ ትኩረት በተማሪዎቹ የመማር ፍላጎትና ዝንባሌ እንዲሁም በክፍል ውስጥ በሚኖራቸው ተራክቦ ላይ ተፅዕኖ አለው:: ለምሳሌ:- ተማሪዎቹ መምህሮቻቸው ስማቸውን ቢያውቁና በተደጋጋሚ ቢጠሩ በመምህሩና በትምህርቱ ላይ የሚኖራቸው ስሜት ጥሩ ይሆናል:: ምክንያቱም መምህሩ ስማቸውን በማወቃቸው ሊረዷቸው እንደሚችሉ ይሰማቸዋል:: በመሆኑም መምህራን የሚያስተምሩባቸውን ክፍሎች ተማሪዎች በሙሉ ስማቸውን ማወቅ አለባቸው ባይባልም የወንዶችና የሴቶችን ስም እኩል ወይም ተመጣጣኝ በሆነ መልኩ ለማወቅ መሞከር አለባቸው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል:: ምክንያቱም የተማሪዎችን ስም ማወቅና በተደጋጋሚ መጥራት መምህሩ ለተማሪዎች ከሚሰጡት ትኩረት አንዱ በመሆን ነው::

## 2.5. በየምድቦቹ የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎች ቁጥር መጠን ንፃሬ /ratio/ መለያየት ከተሳትፎአቸው ጋር ያለው ግንኙነት

ከላይ በተለያዩ ንዑስ ርዕሶች ስር ለማገለፅ እንደተሞከረው በመማክ ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የጾታን ልዩነት በሚመለከት በውጭም ሆነ በሀገራችን የተከናወኑ ጥናቶች የሴቶችና ወንዶች ተማሪዎች ቁጥር እኩል በሆኑበት ቡድን ውስጥ የተደረጉ ናቸው:: የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሆነውና ብዙ ጥናት ያልተደረገበት ደግሞ የወንዶችና የሴቶች ቁጥር የተለያየ በሆነበት ቡድን ወይም ምድብ የሴት ተማሪዎችን የመማክ ውስጥ ተራክቦ በሚመለከት የሚደረግ ጥናት ነው:: በዚህም መሰረት በውጭው አለም ከተደረጉ ጥናቶች Webb (1984) የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች በሚበልጥበት፣ እኩል በሚሆንበትና ከወንዶች በሚያንስበት ቡድን ውስጥ የሚኖራቸውን ቃላዊ ተራክቦ መጠን መርምረዋል:: ያገኙት ውጤትም ይዘውት የተነሱትን መላምት የሚደግፍ ሆኖአል:: ይህም ሴቶች ከወንዶች በሚበዙበት ቡድን ውስጥ የሴቶች ቃላዊ ተራክቦ መጠን ወይም የሚወስዱት ተራ ከወንዶች የሚበልጥ ሲሆን እኩል በሆኑበት ቡድን ውስጥ የወንዶችና የሴቶች ቃላዊ ተሳትፎ እኩል ይሆናል፣ እንዲሁም የሴቶች ቁጥር ከወንዶች በሚያንስበት ቡድን የወንዶች ቃላዊ ተሳትፎ በልጦ ይታያል የሚል ነው:: ከላይ የተጠቀሱት ምሁርም በጥናታቸው ሪፖርት ያደረጉት ይህንኑ የሚያመለክት ነው::

በሀገራችን አማኑኤል ገዛኸኝ (1996) ተመሳሳይ ጥናት አድርገው የተለየ ውጤት አግኝተዋል:: ይህም በሶስቱም ቡድኖች ማለትም (ሴቶች ከወንዶች በሚበልጡበት፣ እኩል በሆኑበትና በሚያንሱበት) ቡድኖች በተደረገ ውይይት ወንዶችና ሴቶች ባደረጉት ቃላዊ ተሳትፎና በወሰዱት ተራ ስርጭት (Turn-distribution) በመካከላቸው ልዩነት አለመኖሩን አረጋግጠዋል::

በሌላ መልኩ ደግሞ ሴቶች ተማሪዎች ብቻቸውን በሚማሩባቸው ክፍሎች ውስጥ ከመምህሮቻቸውም ሆነ ከጓደኞቻቸው ጋር የሚኖራቸው ቃላዊ ተሳትፎ ምን ይመስላል? በማለት ጥናት ያካሄዱ ምሁራንም አሉ:: ከእነዚህም ለምሳሌ King and Hill (1996) Lockeed and Jemenez (1988) ን በመጥቀስ የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዳራዎችና ሌሎች ተዕዕኖ የሚያደርጉ ነገሮችን በመቆጣጠር በታይላንድ ሀገር ሴት ተማሪዎች መማክ ውስጥ ተራክቦ ላይ ጥናት ያካሄዱ ሲሆን በጥናታቸው ውጤትም ከወንዶች ጋር ከሚማሩት ሴቶች ተማሪዎች ይልቅ ብቻቸውን የሚማሩት ንቁ ተሳትፎና የበለጠ ተራክቦ ያላቸው መሆኑን አሳይተዋል::

በተጨማሪም Odaga and Henveld (1995) Kilo (1994) ን በመጥቀስ በክፍል ውስጥ የሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦን ከጾታ አንፃር ለመመርመር በኬንያ፣ ማላዊ ታንዛኒያና ሩዋንዳ የተደረጉ የክፍል ውስጥ ምልከታዎችንና የተገኘውን ውጤት መሰረት በማድረግ እንደገለፁት ወንዶች ጋር ለሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች መምህራን የሚሰጡት ትኩረት ከወንዶች በጣም ያነሰ መሆኑንና የሚያደርጉትም ቃላዊ ተራክቦ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ገልፀው በዚህም

ምክንያት ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች ጋር አብረው በሚማሩባቸው ት/ቤቶች (Coeductional schools) ለመማር ያላቸው ፍላጎት ወይም ፈቃደኝነት በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለመረዳት ችለዋል::

ሌሎች ምሁራንም ለምሳሌ፡- Lee and Bryk (1986), Potter (1978), Kim Thomas (1990) Scheneider and Coutts (1982 )የመምህር ተማሪን የክፍል ውስጥ ተራክቦ ከጾታ ልዩነት አንፃርና የአንድ ጾታ ብቻ ትምህርት ቤት (Single-sex school) በሴቶች ተማሪዎች ላይ ያለውን ውጤት (Effect) በማጥናት ያገኙት ውጤት በሁለቱም ጾታዎች መማሪያ ትምህርት ቤት (Coeducational school) ከሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች ይበልጥ ብቻቸውን ወይም በአንድ ጾታ ት/ቤት (Single-sex school) የሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች የበለጠ ተሳታፊና ውጤታማ መሆናቸውን አመልክተዋል::

በአጠቃላይ ወንዶችና ሴቶች አብረው በሚማሩባቸው ክፍሎች ውስጥ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ወይም የተማሪ ተማሪ ተራክቦ ላይ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ሁለት መልስ ያላገኙ ጥያቄዎችን አንስተዋል:: እነዚህም፡-

1. በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ መጠን ላይ የሚታየው ልዩነት ወንዶችና ሴቶች አብረው በሚማሩበት ክፍል ውስጥ (Cross-sex) በሚደረግ ተራክቦ ላይ ብቻ ወይስ?
2. በተመሳሳይ ጾታዎችም (Same-sex) ሴቶች እርስ በርስ በሚያደርጉት ተራክቦም ልዩነት አለ? የሚሉ ናቸው::

ከዚህ በተጨማሪም ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎች ቁጥር ማለትም በቡድን ወይም በክፍል ውስጥ የሚኖራቸው መጠነ ንፃሬ (Ratio) መለያየት በክፍል ውስጥ በሚያደርጉት ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ አለውን? የሚለውን ጥያቄ የጥናታቸው መነሻ ያደረጉት ምሁራን እንዳሉም ተገልጿል:: ስለዚህ ሴቶች ለብቻቸውና ከወንዶች ጋር ሲማሩ የሚኖራቸውን የክፍል ውስጥ ቃላዊ ተራክቦ ወይም ሴቶች በሚበዙበት፣ እኩል በሚሆኑበትና ከወንዶች በሚያንሱበት ቡድን ወይም መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚኖራቸውን ቃላዊ ተራክቦ መጠን ልዩነት መመርመር ልዩነቱ ጎልቶ የሚታየው በተለይም ሴቶች ተማሪዎች በመማሪያ ክፍል ውስጥ ቃላዊ ተሳትፎ የተሻሉ ሆነው የሚታዩት በየትኛው ቡድን ወይም ክፍል ውስጥ ነው? ለምን? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይጠቅማል:::

በዚህም Webb (1984) ከሚከተሉት ምክንያቶች አንዱ ሴቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚኖራቸው ዝቅተኛ ተሳትፎ ምክንያት ሊሆን ይችላል በማለት ይገልፃሉ::

1. ሴቶች በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ በሚደረገው የመማር ማስተማር ሂደት የሚያደርጉት ቃላዊ ተሳትፎ ዝቅተኛ በመሆኑ፣
2. ሴቶች ከወንዶች ጋር በሚማሩበት ጊዜ ተሳትፏቸው የሚቀንስ በመሆኑ

እነዚህ ሁለት ነጥቦች በዚህ ጥናትም የሚተኮርባቸው ናቸው፣ ማለትም በሶስቱም ምድቦች የሴቶች ተማሪዎች ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ሆኖ ከተገኘ በተራ ቁጥር አንድ ላይ የተገለፀው ነጥብ ምክንያት ይሆናል፡፡ ማለትም ሴቶች በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ የሚያደርጉት ቃላዊ ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው የሚለው ምክንያት ይሆናል፣ ነገር ግን ሴቶች በሚበዙበት ምድብ የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች የተሻለ ከሆነና ወንዶችና ሴቶች እኩል በሆኑበትና ወንዶች በሚበዙበት ምድብ የሴቶች ተሳትፎ ዝቅተኛ ከሆነ በተራ ቁጥር ሁለት ስር የተጠቀሰው ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህም ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ ተሳትፎአቸው ይቀንሳል የሚለው ምክንያት ይሆናል፡፡

## 2.6. ለራስ የሚሰጥ ግምት /Self-esteem/ ከክፍል ውስጥ ተሳትፎና ከጾታ ጋር ያለው ግንኙነት

በትምህርትም ሆነ በሌሎች ተግባራት ረገድ በራስ የመተማመን ችሎታ ወይም ለራስ ከሚሰጥ ግምት አንፃር በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት መኖሩን ያረጋገጡ ምሁራን በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህ ምሁራንም በጥናቶቻቸው ያረጋገጡት ከዝቅተኛ ክፍሎች እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች ለራሳቸው ችሎታና ተሳትፎ የሚሰጡት ግምትና ዋጋ ከተግባራቸው የሚጠብቁት ውጤት ከወንዶች ያነሰ መሆኑን የሚያስረዳ ነው Maccoby and Jucquline (1974) ፡፡ ይህም በትምህርታቸው የተሻለ ውጤት በሚያስመዘግቡትና በተሳትፎም የተሻሉ ናቸው በሚባሉት ተማሪዎችም ጭምር የሚታይ መሆኑን ጥናቶች ይጠቁማሉ Marsh (1989)፡፡

ለራስ የሚሰጥ ግምት አነስተኛና ከፍተኛ መሆኑን ከሚያደርጓቸውና ከሚታይባቸው አንዳንድ ባህሪያት በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት መኖሩን ለማወቅ ይቻላል፡፡ ለምሳሌ፡- ተማሪዎች ፈተና ከተፈተኑ በኋላ ወንዶች ፈተናው ቀላል ነበር በማለት ለጓደኞቻቸው ይናገራሉ፡፡ ሴቶች በተቃራኒው ፈተናው የከበዳቸውና እወድቃለሁ የሚል ስጋት እንዳላቸው ይናገራሉ፡፡ እንዲሁም በክፍል ውስጥ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች ግልፅና ዘርዘር ያለ መልስ ለመስጠት የሚሞክሩት ወንዶች ሲሆኑ ሴቶች ግን አጭር የሆነ መልስ በማይሰማ ድምፅ የሚመልሱ በመሆን ወንዶች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከሴቶች የሚበልጥ መሆኑን ምሁራት ያስረዳሉ፡፡

ስለዚህ ሴቶች ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከወንዶች ያነሰ በመሆኑ በክፍል ውስጥ በሚደረግ የመማሀር ተማሪ ተራክቦ ላይ ለመሳተፍ "እሳሳታለሁ" የሚል ፍርሃት ስለሚያድርባቸው ለንግግር አይነሳሱም፡፡ በዚህ መልኩ ሴቶችና ወንዶች በክፍል ውስጥ ለሚኖራቸው ቃላዊ ተራክቦ ልዩነት ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት አንዱ. መንስኤ ሊሆን እንደሚችል መገመት ይቻላል፡፡ ይህን ሁኔታ በሚመለከት ብዙ መምህራንም ሴቶች ተማሪዎች

"ስናገር እሳሳታለሁ" በሚል ፍርሃት ለመሳተፍ አይነሳሱም የሚል አስተያየት የሰጡትን እናገኛለን።

ለራስ የሚሰጥ ግምትን ከጾታ አንፃር የመረመሩ አጥኚዎች ባካሄዱት ምርምር እንደገለፁት፣ ሴቶች ተማሪዎች በማንኛውም የትምህርት አይነት ለሚያስመዘግቡት ውጤት የሚኖራቸው ግምት ከወንዶች ያነሰና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን አረጋግጠዋል። ከዚህም ሌላ ለሚያከናውኗቸው ተግባራት መሳካት ወይም መደናቀፍ ወንዶችና ሴቶች የሚኖራቸው አመለካከት የተለያየ ነው። ለምሳሌ ሴቶች በፈፀሙት ተግባር ስኬታማ ካልሆኑ ለውድቀታቸው መንስኤ የችሎታቸው ማነስ መሆኑን ሲገልፁ ወንዶች ግን በቂ ጥረት ባለማድረጋቸው መሆኑን እንደሚያምኑበት Johns and Smart (1995), Victoria and Diana (1997) ይገልፃሉ።

ሴቶች በአጠቃላይ ለራሳቸው የሚሰጡት አነስተኛ ግምት በትምህርትና በክፍል ውስጥ ለሚኖራቸው ተሳትፎ ማነስ ዋና ምክንያት ከመሆኑም ባሻገር በወደፊት ህይወታቸውም ከፍተኛ እንቅፋት እንደሚፈጥርባቸው Betz and Fetzegerald (1987) ይገልፃሉ።

# ምዕራፍ ሶስት

## የአጠናኑ ዘዴ

### 3.1. የናሙና ትምህርት ቤት መረጣ

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች በሚበልጥበት፣ እኩል በሚሆንበትና ከወንዶች በሚያንስበት መማሪያ ክፍል ውስጥ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ (የመምህር ተማሪ ተራክቦ) መጠንና መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት መመርመር ነው:: በተጨማሪም በሶስቱ ምድቦች በሚገኙ ሴቶች ተማሪዎች መካከል የተራክቦ ልዩነት ካለ ልዩነቱንና የልዩነቱን መንስኤ ማሳየት ነው::

ለዚህ አላማም ተግባራዊነት በይሁንኝ የናሙና አመራረጥ ስልት(Purposive sampling) የተመረጠው ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኘው የመድሃኔ አለም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሲሆን ይህም የተመረጠበትም ምክንያት:-

1. አጥኚዋ ጥናቱን ለማካሄድ በምትጠይቅበት ጊዜ የትምህርት ቤቱ አስተዳደርም ሆነ ተጠኝ መምህራን ባሳዩት መልካም ፈቃደኝነት፣
2. ከላይ የተጠቀሱት ምድቦች ማለትም የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች የሚበልጥበት፣ እኩል የሚሆንበትና ከወንዶች የሚያንስበት ሁኔታ በቀላሉ ሊገኝበት በመቻሉ እና
3. ትምህርት ቤቱ በቀደምት የተለያዩ አጥኚዎች ያልተሰላቸ በመሆኑ ጥሩ መረጃ ይገኝበታል የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

### 3.2. የተሳታፊዎች አወሳሰድ

ለዚህ ጥናት በቀጥታ የተወሰደው የክፍል ደረጃ የ11ኛ ክፍል ነው:: የተመረጠበት ምክንያትም ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች በጾታቸው መለያየት የተነሳ በክፍል ውስጥ ተሳትፎም ሆነ በአጠቃለአይ ትምህርት ረገድ ልዩነት የሚኖራቸው በጉርምስና ወይም በኩርድና የእድሜ ክልል ሲደርሱ Betz and Fetzegerald (1987), Lindors (1995) ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሚማሩበት ወቅት መሆኑን Woods and Hammersely (1991) Warrick and Jack (1993) Merrett and Wheldall (1992)ን በመጥቀስ፣ Hilton and Verlunged(1979) የገለፁትን መሰረት በማድረግ ነው:: ስለዚህም ከአሉት የሁለተኛ ደረጃ ክፍሎች (ማለትም ከ9ኛ፣10ኛ 11ኛ ክፍሎች) የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች በእድሜም ሆነ በእስተሳሰብ ከሌሎቹ የተሻሉ ከመሆናቸውም በላይ ልዩነቱ ጎልቶ ሊታይ የሚችለው በዚህ ክፍል ደረጃ በሚማሩ ሴቶችና ወንዶች ተማሪዎች ላይ ይሆናል:: የአስራ ሁለተኛ ክፍል ተማሪዎች በመረጃ ስበሰባው ወቅት በት/ቤቱ ስለማይገኙ ከምርጫው እንዲገለሉ ተደርገዋል::

በመድሃኒ አለም አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ በጠቅላላው 15 የ11ኛ ክፍል ምድቦች /Sections/ ለዚህ ጥናት በቀጥታ አስፈላጊ የሆኑት ሶስት ምድቦች በይሁንኝ የናሙና አመራረጥ /Purposive sampling/ ስልት መሰረት ተመርጠዋል። እነዚህም ክፍሎች የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች የሚበልጥበት፣ እኩል የሆነበትና ከወንዶች የሚያንስበት ሲሆን ከእነዚህ ምድቦች ከእያንዳንዳቸው ሁለት፣ሁለት ምድቦችን ለመውሰድ ታስቦ ነበር። ነገር ግን የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች የሚበልጥበት ከአንድ በላይ ማግኘት ባለመቻሉና ከአሉትም ምድቦች መካከል ጥቂቶቹ በችሎታ "ልዩ" (Special) የሆኑ ተማሪዎች የተመደቡባቸው በመሆናቸው ከእነዚህ ምድቦች ናሙና ለመውሰድ አልተቻለም፣ ምክንያቱም እነዚህን ልዩ ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎች ከመካከለኞቹና ከዝቅተኞቹ ጋር ለማወዳደር የማይቻል በመሆኑ በስሱ በአብዛኛው ተመሳሳይ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በሚገኙባቸው ምድቦች ላይ ብቻ ለመወሰን ተችሏል።

በአጠቃላይ 147 ተማሪዎች በዚህ ጥናት ተሳታፊ ሆነዋል። አጠቃላይ ዝርዝሩን ከሚከተለው ሰንጠረዥ ይመልከቱ፤

ሰንጠረዥ ሀ፡ <u>በየምድቦቹ የሚገኙ ተማሪዎች ብዛትና የጾታ ስርጭት</u>

| ተ.ቁ | ምድቦች | የተሳታፊዎች ብዛት | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወ | % | ሴ | % | ድምር |
| 1 | ሴቶች የሚበዙበት | 17 | 37 | 29 | 63 | 46 |
| 2 | ሴቶችና ወንዶች እኩል የሆኑበት | 24 | 52.2 | 22 | 49.8 | 46 |
| 3 | ወንዶች የሚበዙበት | 38 | 69.1 | 17 | 30.9 | 55 |
| | ጠቅላላ ድምር | 79 | 53.7 | 68 | 46.3 | 147 |

## 3.3. የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት በዋናነት የተሰራባቸው በመምህራንና በተማሪዎች የተሞሉ የፅሁፍ መጠይቆች፣ ያቪዲዮ ቀረፃና ምልከታ ናቸው።

### 3.3.1. የፅሁፍ መጠይቆች

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት በዋናነት የተሰራባቸው የፅሁፍ መጠይቆች በተማሪዎችና በመምህራን የተሞሉ ሲሆን እያንዳንዳቸውን ቀጥሎ እንመለከታለን።

#### 3.3.1.1. የተማሪዎች መጠይቅ

የተማሪዎች መጠይት የተዘጋጀው ተማሪዎቹ የክፍል ውስጥ ተሳትፎአቸው በእነሱ አይን ምን መልክ እንዳለው ለማወቅ ነው። እንዲሁም መምህራን የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ለወንዶቹ ነው ለሴቶቹ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ነው። በዚህ መልክ የቀረበው

መጠይቅ ይዘቱ በጾታና በክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ የተመሰረተ ሲሆን ይህም በመምህር ተማሪ ተራክቦ ረገድ የበለጠ ተሳታፊዎቹ ወንዶቹ ወይስ ሴቶቹ መሆናቸውንና በሁለቱ መካከል ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለመገምገም የሚያስችል ነው፡፡

መጠይቁ በሁለት ክፍሎች የቀረበ ሲሆን የመጀመሪያው በምርጫ መልክና ለሚመርጧቸው መልሶች ምክንያቶችን እንዲያክሉበት በሚጠይቅ መልክ የቀረበ ነው፡፡ ሁለተኛው በክፍል ውስጥ ተራክቦና በጾታ ዙሪያ ከተደረጉ ጥናቶች በመነሳት ለተዘጋጁት ጥያቄዎች ደረጃ (Scale) እንዲሰጡ የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚህ መልክ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች በሁለት መልክ ተተንትነዋል፡፡ እነዚህም በምርጫና በደረጃ ለቀረቡት ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች ወደ አሀዝ ተለውጠው (ለምሳሌ በጣም ከፍተኛ=5፣ ከፍተኛ=4፣ መካከለኛ=3፣ ዝቅተኛ=2 እና በጣም ዝቅተኛ=1) የእያንዳንዱ ምድብ ውጤቶች ለየብቻ ተሰልተዋል፡፡ ደረጃን የሚለኩትን "በጣም ከፍተኛ" እና "ከፍተኛ" (5+4) በአንድ ላይ "መካከለኛ" ለብቻውና "ዝቅተኛ"ና "በጣም ዝቅተኛ" (2+1) በአንድ ላይ ተደምረው ተወስደዋል፡፡ የተማሪዎችንስሜትና ፍላጎት እንዲሁም አስተያየት ለማወቅ ምክንያት እንዲሰጡባቸው ለማድረግ ለቀረቡት ክፍት ጨራሽ (Open-ended) ጥያቄዎች በአብዛኛዎቹ መላሾች የተጠቀሱት ነጥቦች ትኩረት ከሚሰጥባቸው ጉዳዮች አንፃር ተለይተው ቀርበዋል፡፡

### 3.3.1.2. የመምህራን መጠይቅ

ከተማሪዎች መጠይቅ ለሚገኘው መልስ ማጠናከሪያነት ይረዳ ዘንድ የመምህራን መጠይቅ ይዘቱ ከተማሪዎች መጠይቅ ጋር እንዲመሳሰል ተደርጓል፡፡ አቀራረቡን በሚመለከት ግን ለየት ይላል፡፡ ይህም በመጀመሪያው ክፍል በወንዶችና በሴቶች መካከል የክፍል ውስጥ ተራክቦ ልዩነት መኖር አለመኖሩን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ጥያቄዎች በምርጫ መልክና እንዲሁም የመምህራኑን አስተያየትና አመለካከት ለማየት እንዲያስችሉ በክፍት ጨራሽ ጥያቄዎች መልክ ቀርበዋል፡፡

በሁለተኛ ክፍል የቀረቡ ጥያቄዎች ከተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት የተገኙ ሀሳቦች ሲሆኑ ይህም በክፍል ውስጥ በመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የጾታን ልዩነት ያጠኑ ምሁራን ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ተሳትፎ እንዳላቸው በመግለፅ ሴቶች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ የሆነባቸውን ምክንያቶች ዘርዝረዋል፡፡ ከእነዚህ ምክንያቶች የተወሰኑትን በናሙናነት በመውሰድ በዚህ ጥናትም የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ ነው በማለት መልስ የሰጡ መምህራን እነዚህን ነጥቦች በየግል አስተያየታቸው እንዲመርጧቸው የሚጠይቅ ነው፡፡ ለዚህ ጥያቄ ከቀረቡት ምርጫዎች አብዛኛዎቹ መምህራን የመረጧቸው ሀሳቦች ትኩረት ከሚሰጥባቸው ነጥቦች አንፃር ተመርጠው ተወስደዋል፡፡

መጠይቁን የሞሉት መምህራን የ11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሙሉ ሲሆኑ ብዛታቸውም ስድስት እና ሁሉም ወንዶች ናቸው።

### 3.3.2. የቪዲዮ ቀረፃ

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት የተሰራበት ሌላው መሳሪያ በክፍል ውስጥ በመምህር-ተማሪ ተራክቦ ላይ የሚታዩ ክንዋኔዎችን በቪዲዮ ካሜራ መቅረፅ ነው። የቪዲዮ ቀረፃው ቃላዊ ክንዋኔዎችን ደጋግሞ ለማየት ከማስቻሉም በተጨማሪ አህዛዊ መረጃን ለመትከል፣ በምልከታ የታለፉ ቃላዊ ክንዋኔዎችን ደጋግሞ በማየት መረጃውን የተሟላ ለማድረግና በመማር ማስተማሩ ሂደት በሚደረገው የመምህር ተማሪ ተራክቦ በሚኖር ንግግር ተሳታፊው (ተናጋሪው) ወንድ ወይም ሴት መሆኑን ለመለየት የሚረዳ በመሆኑ ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ተሰርቶበታል።

ቀደም ባሉት ጊዜያት ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ባላቸው ጥናቶች ላይ ምርምር ያደረጉ አጥኚዎች እንዳደረጉት የቪዲዮ ቀረፃው በሁለት ንዑሳን ክፍሎች ተከፍሎ ተከናውኗል። ከእነዚህም አንዱ ምስለ ቀረፃ (Simulation) የሚባለው ሲሆን ተማሪዎቹም ሆኑ መምህራን የካሜራ ባለሙያው በክፍል ውስጥ በመገኙ ምክንያት ከተለምዶው ተግባራቸው የተለየ ክንዋኔ እንዳያሳዩ ለማድረግ ለመጀመሪያዎቹ ሁለት ቀናት ምስለ ቀረፃ ተደርጓል። በሚቀጥለው ቀንም እውነተኛው ቀረፃ ተከናውኗል። በዚህ ጊዜ መምህራኑም ሆኑ ተማሪዎች በተደጋጋሚ ስለተቀረፁ በየትኛው ጊዜ እውነተኛ ቀረፃው እንደተደረገ ስለማያውቁ መረጃውን አስተማማኝ ለማድረግ ተሞክሯል። በዚህ ሁኔታ እያንዳንዱ ተጠኝ ምድብ ለ40 ደቂቃ ተቀርጿል። የተቀረፀውን ፊልምም ሁለት ዳኞች ማለትም አንድ ወንድና አንድ ሴት ከአጥኚዋ ጋር በመሆን እያዩና እያዳመጡ የሚፈለጉትን ተላውጦዎች (Variable) እና ድግግሞሻቸውን በማውጣት መረጃውን ወደ ፅሁፍ ሰነድነት ለመለወጥ ችለዋል። በመጨረሻም በስስቱም ምድቦች የወንዶችና የሴቶች ንግግር፣ የመምህሩ ምላሽ አይነትና መጠን ለየብቻ በመቶኛ ተሰልቷል።

### 3.3.3. የክፍል ውስጥ ምልከታ

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለሚደረግ ምርምር መረጃ መሰብሰቢያነት የሚያገለግል ምልከታ በሁለት መንገድ እንደሚከናወን Seliger and Shohamy (1989:175). ያረጋግጣሉ። እነዚህም በተሳታፊነትና በኢ-ተሳታፊነት (Participant . and Non-Participant Observers) ናቸው። በተሳታፊነት የሚደረግ ምልከታ አጥኚው በክፍል ውስጥ በሚከናወነው ተግባር ተሳታፊ በመሆን የሚከናወን ሲሆን በኢ-ተሳታፊነት ደግሞ አጥኚው በድርጊቱ ተሳታፊ

ሳይሆን መረጃውን ለመሰብሰብ ብቻ በክፍል ውስጥ ተገኝቶ የሚያካሄደው የምልከታ ሂደት ነው። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናት ተግባራዊ የሆነው የኢ-ተሳታፊነት ምልከታ ነው።

በሌላ መልኩ የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በተለይም በቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ የሚደረግ ምልከታ፣ በሁለት እንደሚከፈል Richards and Nunan(1990) ገልጸዋል። እነዚህም አይነታዊና መጠናዊ (Qualitative and quantitative observations) በመባል ይታወቃሉ።

አይነታዊ ምልከታ ከሚባለው አንዱ ኢትኖግራፊያዊ ምልከታ (Ethnographic observation) የሚባለው ሲሆን አጥኚው በክፍል ውስጥ ተቀምጦ የትምህርቱን ክንዋኔ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ ተከታትሎና በፅሁፍ መዝግቦ የሚይዝበትና የወሰደውንም ማስታወሻ ዘርዝርና ጠለቅ አድርጎ የሚያቀርብበት ነው።

መጠናዊ ምልከታ፣ ደግሞ በክፍል ውስጥ በሚደረግ በመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ ከሚታዩ ክንዋኔዎች ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑትን አስቀድሞ በመምረጥና የምልከታ "ቻርት" (Observation cheklist) በማዘጋጀት በዚህም ላይ የክንዋኔዎቹን ድግግሞሾች (Frequencies) ቁረት (Tally) አድርጎ ወይም የድግግሞሾቹን መጠን ደረጃ በሚለኩ (ማለትም በጣም ከፍተኛ፣ ከፍተኛ፣ መካከለኛ፣ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ) በማለት በእነዚህ የደረጃ መለኪያዎች በመጠቀም የሚሰራበት ነው።

ለዚህ ጥናት ሁለቱም የምልከታ አይነቶች ተግባራዊ ሆነዋል። በመጀመሪያ በአይነታዊ ምልከታ የመማሪያ ክፍሎቹን ድባብ፣ የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል ሁኔታ፣ የትምህርቱን ሂደት፣ በአጠቃላይ በተማሪዎችና በመምህራን መካከል የሚካሄደውን ትምህርታዊ ክንዋኔ በመመልከት ለመጠናዊ ምልከታ የሚረዱ ተላውጦዎችን (Variables) ለማውጣት ተችሏል። በሌላ አገላለፅ በመምህሩና በተማሪዎች መካከል በሚኖረው የክፍል ውስጥ ተራክቦ የሚነሱ ጉዳዮችን ለማውጣት አይነታዊ ምልከታ አስፈላጊ በመሆኑ ከመደበኛው ምልከታ ቀደም ብሎ በቃኚ ጥናት (Pilot study) ወቅት ተግባራዊ ሆኗል።

ከላይ በተገለፁት የምልከታ ስልቶች በመጠቀም ለጥናቱ የተመረጡት ምድቦች እያንዳንዳቸው ሰስት፣ ሰስት ጊዜ ምልከታ ተደርጎባቸዋል።

ምልከታው የተደረገበት የምልከታ ቻርት (Cheklist) ሁለት ይዘቶች አሉት። ከእነዚህም አንዱ የተማሪዎችን ተሳትፎ (ተራክቦ) መጠን ለመገምገም የሚያስችል ሲሆን ሌላው መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት (Atention) እና ምጋቤ ምላሽ (Feedback) ለማወዳደር የሚቻልበት ነው። የተማሪዎችን ተራክቦ መጠን ለመገምገም የተመረጡ ይዘቶች ለምሳሌ፦ ተማሪዎቹ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚያደርጉትን ሙከራ (እጅ ማውጣት)፣ በመምህሩ ሳይጠየቁ መልስ የመስጠት ሁኔታ፣ ጥያቄ መጠየቅ፣ ትክክለኛ መልስ መስጠት፣ ወዘተ. በምሳሌነት ሊጠቀሱ ይችላሉ። የመምህሩን ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ በሚመለከት ደግሞ ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ

መምህራን የሚሰጧቸው እድል፣ ሙገሳ፣ ትችት፣ ወዘተ. በዋናነት የተነሱ ናቸው።

እነዚህ ይዘቶች የተመረጡት ቀደም ብሎ እንደተገለፀው በቃኚ ጥናት ወቅት በተደረገ አይነታዊ ምልከታ የታዩና በመግሪያ ክፍል ውስጥ በመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ ምርምር ያደረጉ ቀደምት ምሁራን ከጠቀሷቸው ተላውጦዎች ለዚህ ጥናት በቀጥታ አስፈላጊ የሆኑት ናቸው። በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት ሁለቱ ይዘቶች በክፍል ውስጥ ተራክቦ ወንዶች ናቸው ወይስ ሴቶች የበለጠ ተሳታፊዎች? የሚለውንና መምህራን የበለጠ ትኩረት የሚሰጡት ለወንዶች ወይስ ለሴቶች? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ይረዳሉ።

## 3.4. የመረጃ አተናተን ሂደት

በዚህ ጥናት ተግባራዊ የተደረጉ የመረጃ አተናተን ስልቶች አይነታዊና መጠናዊ (Qualitative and quantitative) ናቸው። በአይነታዊ የመረጃ አተናተን ስልት የይዘት ትንተና (Content analysis) ተግባራዊ ሆኖአል። በዚህም ተሳታፊ ተማሪዎችና መምህራን ለክፍት ጫፍ (Open-ended) ጥያቄዎች የሰጧቸው አስተያየቶች በጥናቱ ከተነሱት ጥያቄዎች አንፃር በማዋሀድ ገለፃ ለማድረግ ተሞክሯል።

በመጠናዊ የመረጃ አተናተን ስልት ደግሞ አሀዛዊ የሆኑ መረጃዎች ተተንትነዋል። በዚህም ከቪዲዮ ቀረፃው የተገኘው መረጃ በመጀመሪያ ተመዝግቧል። ማለትም በመማር-ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችንና የመምህሩን ንግግር እያዩና እያዳመጡ ለመፃፍ ተሞክሯል። በመቀጠልም ለጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የንግግር ፈርጆችንና ድግግሞሻቸውን በመቁጠር የሰስቱንም ምድቦች ለየብቻ የወንዶችንና የሴቶችን በመቶኛና በአማካይ (Mean) በማስላት ልዩነታቸውን በቲ ስሌት ለማሳየት ተችሏል። የመምህራኑንም ንግግር በሚመለከት ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በሚመለከት የሚታየውን ልዩነት እንደዚሁ በአማካይና በመቶኛ በማስላት ልዩነቱን በቲ ስሌት ለማሳየት ተሞክሯል።

# ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ውጤትና ትንተናው

በመጀመሪያው ምዕራፍ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ ሴቶች ከወንዶች በሚበልጡበት፣ እኩል በሆኑበትና ከወንዶች በሚያንሱበት ምድብ ውስጥ የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠንና መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ (Verbal feedback) መመርመር ነው፡፡ በተጨማሪም የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በተመለከተ ከሶስቱ ምድቦች በየትኛው ምድብ የሚማሩ ሴቶች የተሻለ ተሳትፎ አላቸው? የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ ነው፡፡ ጠቅለል ባለመልኩ ደግሞ የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ ሆኖ ከተገኘ፣ ተሳትፎአቸው ዝቅተኛ እንዲሆን የሚያደርጉ ምክንያቶችን ማሳየት የዚህ ጥናት ሌላው አላማ ነው፡፡

ለዚህም የተሰራባቸው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ የቪዲዮ ቀረፃ፣ በተማሪዎችና በመምህራን የተሞሉ የፅሁፍ መጠይቆችና ምልከታ ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍም ከላይ በተዘረዘሩት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካኝነት የተገኙትን መረጃዎች በመተንተን ቀደም ሲል የተጠቀሱትን የጥናቱን አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

ለመረጃ አተናተን እንዲያመች መረጃው በሁለት ክፍሎች ተከፍሏል፡፡ የመጀመሪያው የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠን በሚመለከት ሲሆን በሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኙ መረጃዎች እርስ በርስ እየተመሳከሩ ይቀርባሉ፡፡ በመቀጠልም መምህራት ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በሚመለከት የተገኙ መረጃዎች ውጤት ይገለፃል፡፡ በመጨረሻም የመምህሩ ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመመርመር በሁለቱ ይዘቶች ስር የተገኙ ውጤቶች ይገናዘባሉ፡፡

ጥናቱ ከላይ የተጠቀሱትን አላማዎች ተግባራዊ ለማድረግ ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል፤

1. የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር፡-
    1.1. ሴቶች በሚበዙበት ምድብ /Section/ ምን ያህል ነው?
    1.2. ሴቶችና ወንዶች እኩል በሆኑበት ምድብ ምን ያህል ነው?
    1.3. ወንዶች በሚበዙበት ምድብ ምን ያህል ነው?
2. ከሶስቱ ምድቦች የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በልጦ የሚታየው በየትኛው ምድብ ነው?
3. መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ይለያያልን?

4. የመምህሩ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ከተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ጋር ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል?

### 4.1. የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠን በሚመለከት ከቪዲዮ ምዝገባ (Video Transcription) እና ከምልከታ የተገኘ መረጃ ውጤት

የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለመመርመር የክፍል ውስጥ ክንውኑን በቪዲዮ ካሜራ መቅረፅ የዚህ ጥናት አንዱ ተግባር ነበር:: ይህም በምዕራፍ ሶስት እንደተገለፀው በምልከታ የተገኘውን መረጃ አስተማማኝ ለማድረግ፣ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳታፊዎችን ግንኙነት ለይቶ ለማወቅና የተማሪዎችንም ሆነ የመምህሩን ንግግር ወደ ጽሁፍ ሰነድነት ለመለወጥ በማስቻሉ በዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ መጠቀም የግድ ሆኗል::

በሶስቱም ምድቦች /ሴቶች በሚበዙበት፣ ሴቶችና ወንዶች እኩል በሚሆኑበትና ወንዶች በሚበዙበት /የተቀረፀውን መረጃ እያዩና እያዳመጡ ወደ ፅሁፍ ሰነድነት ለመለወጥ ተችሏል:: ከዚህም የሴቶችና የወንዶችን፣ እንዲሁም የመምህሩን ንግግር /Utterance/ መጠንና አይነት በመቁጠር አማካዩን (Mean) እና መቶኛውን በማስላት በሶስቱም ምድቦች በሚማሩ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ከተሳትፎም ሆነ ከመምህሩ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አንፃር ያለውን ልዩነት ለማሳየት ተሞክሯል:: በቅድሚያ የተማሪዎችን ተሳትፎ መጠን በሚመለከት የመረጃው ውጤት ቀርቧል:: በመቀጠልም የመምህሩን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ የተገኘው መረጃ ተተንትኗል::

ሰንጠረዥ 1፡ የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎችን ንግግር (Utterance) በአማካይ (Mean) እና በመቶኛ ስሌቶች

| ምድብ | ተመንዎች | ብዛት | የንግግር መጠን | አማካይ (Mean) | % | ቲ ስሌት | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ወንድ | 17 | 60 | 3.5 | 52.6 | 1.1. | የለውም |
| | ሴት | 29 | 54 | 1.9 | 47.4 | | |
| 2 | ወንድ | 24 | 50 | 2.0 | 74.6 | 1.8 | የለውም |
| | ሴት | 22 | 17 | 0.8 | 25.4 | | |
| 3 | ወንድ | 38 | 72 | 1.9 | 64.5 | 0.5 | የለውም |
| | ሴት | 17 | 24 | 1.4 | 35.5 | | |
| ጠቅላላ | ወንድ | 79 | 182 | 2.3 | 65.7 | 1.4 | የለውም |
| | ሴት | 68 | 95 | 1.4 | 34.3 | | |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በሶስቱም ምድቦች በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል የጎላ የተሳትፎ ልዩነት የለም ለማለት ይቻላል:: ሆኖም ልዩነቱ በስታቲስቲካዊ ስሌት የጎላ ባይሆንም ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ እንዳላቸው ውጤቱ ያሳያል:: ምክንያቱም ከጠቅላላው 277 የተማሪዎች ንግግር 182ቱ ወይም 65.7% የወንዶች የንግግር ድርሻ ሲሆን ቀሪው 95ቱ ወይም 34.3% የሴቶች ንግግር ድርሻ ነው::

የየምድቦችን ለየብቻ ስንመለከትም በምድብ አንድ ስታቲስቲካዊ ስሌቱም ሆነ መቶኛው የጎላ ልዩነት አለመኖሩን ያሳያሉ፤ በምድብ ሁለት ልዩነቱ የጎላ ባይሆንም ወንዶች የተሻለ ተሳትፎ እንዳላቸው የመቶኛ ስሌቱ ያሳያል ይህም ከጠቅላላው የተማሪዎች የንግግር መጠን 74.6% ያህሉ የወንዶች የንግግር ድርሻ ሲሆን 25.4% ያህሉ የሴቶች የንግግር ድርሻ ነው:: ስለዚህ ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ንግግር አድርገዋል:: በምድብ ሶስትም እንደዚሁ በወንዶችና በሴቶች መካከል የጎላ ልዩነት ባይኖርም ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ እንዳላቸው ለመመልከት ይቻላል:: ከጠቅላላው የተማሪዎች የንግግር መጠን 64.5% የወንዶች ድርሻ ሲሆን ቀሪው 35.5% የሴቶች ድርሻ ነው:: ስለዚህ ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ንግግር አድርገዋል ለማለት ይቻላል::

ከፍ ሲል ለማሳየት የተሞከረው የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በመማር-ማስተማሩ ሂደት ከሚያደርጉት ንግግር አንፃር ሲሆን ቀጥሎ ደግሞ የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሚገለፅባቸው ጉዳዮች (ማለትም ተማሪዎቹ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጃቸውን በተደጋጋሚ ማውጣታቸውን፣ ለጥያቄዎች በተደጋጋሚ መልስ መስጠታቸውን፣ ያልገባቸውን ጥያቄ በተደጋጋሚ መጠየቃቸውን፣ ወዘተ. በተመለከተ በሶስቱም ምድቦች በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ሊኖር የሚችለውን የተሳትፎ ልዩነት እንመለከታለን::

ሰንጠረዥ 2፡- ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የሚያደርጉትን እጅ የማውጣት ድግግሞሽ በተመለከተ ከቪዲዮ ቀረፃው የተገኘ መረጃ ውጤት

| | | የወንዶች | | የሴቶች | |
|---|---|---|---|---|---|
| ምድብ | እጅ የማውጣት ድግግሞሽ | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | 940 | 620 | 65.9 | 320 | 34.1 |
| 2 | 470 | 290 | 61.7 | 180 | 38.3 |
| 3 | 1030 | 640 | 62.1 | 390 | 37.9 |
| ጠቅላላ | 2440 | 1410 | 57.8 | 1030 | 42.2 |

ከላይ በሰንጠረዡ ለማሳየት የተሞከረው በመምህሩ ለተጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ወንዶችና ሴቶች እጃቸውን የማውጣታቸውን ድግግሞሽ ሲሆን ይህንንም አሀዝ ለማግኘት ሶስት ረዳት ተመልካቾች ወይም ዳኞች በቪዲዮ የተቀረፀውን የመማር ማስተማር ሂደት በመመልከትና በዚህም የተማሪዎችን እጅ የማውጣት ድግግሞሽ በመቁጥር ያገኙትን ውጤት በመደመርና ለሶስት በማካፈል አማካዩን (Average) በመውሰድ ነው:: የተገኘው ውጤት እንደሚያሳየውም በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ እጃቸውን በተደጋጋሚ ማውጣታቸውን ውጤቱ ያሳያል::

ይህንኑ ሀሳብ በተመለከተ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው ውጤትም ከላይ የተገኘውን መረጃ የሚደግፍ ነው::ይህም በክፍል ውስጥ ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጃቸውን በተደጋጋሚ የሚያወጡት ወንዶች ወይስ ሴቶች?" በሚል ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 6 የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አራቱ ወንዶች መሆናቸውን ገልጸዋል:: ስለዚህ ከቪዲዮ ተረጻውና ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው መረጃ ውጤት የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል::

ከምልከታው የተገኘው ውጤትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው:: ምክንያቱም በሶስቱም ምድቦች ለሶስት ቀናት በተደረገው ተከታታይ ምልከታ የተገኘው ውጤት በመቶኛ ተሰልቶ በምድብ አንድ 60% ወንዶችና 40% ሴቶች፣ በምድብ ሁለት 68.8%ወንዶችና 31.2% ሴቶች በምድብ ሶስት 63.5% ወንዶችና 36.5% ሴቶች ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጃቸውን በተደጋጋሚ ማውጣታቸውን ለመመልከት ተችሏል:: እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ አሀዞች የሚያመለክቱት እጃቸውን በተደጋጋሚ ያወጡ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎችን ብዛት ሳይሆን እጅ የማውጣት ድግግሞሹን መሆኑን ነው:: ምክንያቱም ለተለያዩ ጥያቄዎች እጃቸውን በተደጋጋሚ የሚያወጡት የተወሰኑ ወንዶች ወይም የተወሰኑ ሴቶች ብቻ ሊሆኑ ይችላሉ:: ስለዚህ የተማሪዎቹን ቁጥር ሳይሆን እጃቸውን ለምን ያህል ጊዜ በተደጋጋሚ አወጡ የሚለውን ነው ለመውሰድ የተቻለው::

ስለሆነም ከላይ እንደተገለጸው ከምልከታው የተገኘ መረጃ ውጤት እንደሚያሳየው በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ እጃቸውን በተደጋጋሚ ማውጣታቸውን ለመገንዘብ ተችሏል:: በተጨማሪም ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ወንዶችና ሴቶች የሚያደርጉትን እጅ የማውጣት ድግግሞሽ በተመለከተ ለተማሪዎች ከተረበው መጠይቅ በጥያቄ 3 ቁጥርም ላይ ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ይህንኑ የሚያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል:: ይህም "መምህሩ ጥያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ መልስ ለመስጠት ስትፈልግ/ጊ ምን ታደርጋለህ/ታደርጊያለሽ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ከተሰጡት ሶስት አማራጮች (እጄን አወጣለሁ፣ እጄን ማውጣት ስለምፈራ አልመልስም፣ መምህሩ ሲጠይቁኝ ብቻ እመልሳለሁ ከሚሉት አማራጮች በሶስቱም ምድቦች በአብዛኞዎቹ ሴቶች የተመረጠው " እጄን ማውጣት ስለምፈራ አልመልስም::" የሚለው ነው:: በዚህም በምድብ አንድ (ሴቶች በሚበዙበት) መጠይቁን ከሞሉት 29 ሴቶች 18ቱ ወይም 62.1% በምድብ ሁለት (ወንዶችና ሴቶች እኩል በሆኑበት) መጠይቁን ከሞሉት 22 ሴቶች

ተማሪዎች 15ቱ ወይም 68.1% እና በምድብ ሶስት (ወንዶች በሚበዙበት) መጠይቁን ከሞሉት 17 ሴቶች ተማሪዎች 13ቱ ወይም 76.4% የሰጡት ምላሽ " እጄን ማውጣት ስለምፈራ አልመልስም።" የሚለውን ነው። ስለዚህ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘው ውጤት ከቪዲዮ ተረጻው፣ ከምልከታውና ከመምህራኑ መጠይቅ የተገኘውን ውጤት የሚደግፍ ነው።

የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ለመመርመር ሌላው ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ በክፍል ውስጥ ለተጠየቁ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ መልስ መስጠት የሚለው ነው። ይህንን በሚመለከትም ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 3፡- በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች የተመለሱ መልሶችን ብዛት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ምድብ | በተማሪዎች የተመለሱ ጠቅላላ መልሶች | | በወንዶች ተማሪዎች የተመለሱ | | በሴቶች ተማሪዎች የተመለሱ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | 115 | 42.4 | 70 | 60.8 | 45 | 39.2 |
| 2 | 65 | 24.0 | 48 | 73.8 | 17 | 26.2 |
| 3 | 91 | 33.6 | 56 | 61.5 | 35 | 38.5 |
| ጠቅላላ | 271 | 100 | 164 | 60.5 | 107 | 39.5 |

ከላይ በሰንጠረዡ ለማሳየት የተሞከረው በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተጠየቁ ጥያቄዎች በተማሪዎች ከተሰጡት ጠቅላላ መልሶች "በወንዶች ምን ያህል? በሴቶችስ ምን ያህል ተመለሱ" የሚለውን ወይም በተደጋጋሚ መልስ የሰጡት ወንዶቹ? ወይስ ሴቶቹ? ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት የተቻለበትን መረጃ ነው።

በሰንጠረዥ 3 እንደተገለጸው፣ በሁሉም ምድቦች የሚማሩ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ለጥያቄዎች በተደጋጋሚ መልስ በመስጠት የላቀ ተሳትፎ አድርገዋል። ይህም በጠቅላላ ከተሰጡት 271 ምላሾች 164 ወይም 60.5% በወንዶች ተማሪዎች የቀረቡ ሲሆኑ ቀሪዎቹ 107 ወይም 39.5% በሴቶች የቀረቡ መልሶች ናቸው። በየምድቦቹ በሚማሩ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ ደግሞ በምድብ አንድ ከቀረቡት ጠቅላላ 115 ምላሾች 70 ወይም 60.8% በወንዶች የተመለሱ ሲሆን ቀሪዎቹ 45 ወይም 39.2% በሴቶች የተሰጡ ናቸው።

በምድብ ሁለት በጠቅላላው በተማሪዎች ከቀረቡት 65 ምላሾች 48 ወይም 73.8% በወንዶች ቀሪዎቹ 17 ወይም 26.2% በሴቶች የቀረቡ ናቸው። በምድብ ሶስት ደግሞ

በጠቅላላው በተማሪዎች ከተሰጡት 91 መልሶች 56 ወይም 61.5% በወንዶች፣ ቀሪዎቹ 35 ወይም 38.5% በሴቶች የተሰጡ ናቸው:: ስለዚህም በሶስቱም ምድቦች ለማሳየት እንደተሞከረው ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ተሳትፎ አድርገዋል::

ከምልከታ የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚደግፍ ነው:: በየምድቦቹ በተደረገው ተከታታይ ምልከታ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ በተደጋጋሚ ለጥያቄዎች መልስ በመስጠት የላቀ ተሳትፎ አሳይተዋል:: በዚህም በምድብ አንድ በተማሪዎች ከተሰጡ ጠቅላላ 59 መልሶች 39 ወይም 68% በወንዶች፣ ቀሪዎቹ 20 ወይም 32% በሴቶች የቀረቡ ሲሆኑ፣ በምድብ ሁለት በጠቅላላ በተማሪዎች ከቀረቡት 48 መልሶች 30 ወይም 62.5% በወንዶች፣ ቀሪዎቹ 18 ወይም 37.5% በሴቶች የቀረቡ ናቸው:: በምድብ ሶስትም በጠቅላላ በተማሪዎች ከተሰጡት 72 ምላሾች 51 ወይም 70.8% በወንዶች ቀሪዎቹ 21 ወይም 29.2% በሴቶች የቀረቡ መልሶች ናቸው:: በጠቅላላው በሶስቱም ምድቦች ከተመለሱት ጠቅላላ 179 ምላሾች 113 ወይም 63.1% በወንዶች፣ ቀሪዎቹ 66 ወይም 36.9% በሴቶች የቀረቡ ናቸው:: ስለዚህ የምልከታው ውጤት ከቪዲዮ ምዝገባ ውጤት ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል::

የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከሚነሱ ጉዳዮች ሌላው ተማሪዎቹ ያልገባቸውን ጥያቄ በመጠየቅ የሚያደርጉት ተሳትፎ ነው:: ይህንንም በተመለከተ ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

ሰንጠረዥ 4፦ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ያልገባቸውን ጥያቄ በመጠየቅ በኩል የሚያደርጉትን ተሳትፎ በሚመለከት ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘ መረጃ ውጤት

| ምድብ | በተማሪዎች የተጠየቁ ጠቅላላ ጥያቄዎች | | በወንዶች ተማሪዎች የተጠየቁ ጥያቄዎች | | በሴቶች ተማሪዎች የተጠየቁ ጥያቄዎች | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | 7 | 38.9 | 5 | 71.4 | 2 | 28.6 |
| 2 | 5 | 27.8 | 4 | 80 | 1 | 20 |
| 3 | 6 | 33.3 | 6 | 100 | - | - |
| ጠቅላላ | 18 | 100 | 15 | 83.3 | 3 | 16.7 |

ከሰንጠረዥ 4 እንደምንመለከተው ያልገባቸውን ጥያቄ ከመጠየቅ አንጻር ተማሪዎቹ በሚያደርጉት ተሳትፎ በሶስቱም ምድቦች በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ልዩነት አለ:: በዚህም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ያልገባቸውን ጥያቄ በመጠየቅ የሚያደርጉት ተሳትፎ ከፍተኛ መሆኑን ከውጤቱ መመልከት ይቻላል:: ይህም በሶስቱም ምድቦች በጠቅላላው በተማሪዎች

ከተጠየቁት 18 ጥያቄዎች 15 ወይም 83.3% በወንዶች ተማሪዎች የተጠየቁ ናቸው፡፡ በየምድቦቹም ስንመለከት በምድብ አንድ ከጠቅላላው 7 ጥያቄዎች 5 ወይም 71.4% በምድብ 2 ከተጠየቁት 5 ጥያቄዎች 4 ወይም 80% በምድብ ሶስት ከጠቅላላው 6 ጥያቄዎች 6ቱም በወንዶች የተጠየቁ ሲሆን ቀሪዎቹ በሴቶች የተጠየቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ ከዚህ ውጤት በመነሳት ሴቶች ተማሪዎች ጥያቄ በመጠየቅ በኩል የሚያደርጉት ተሳትፎ ከወንዶች በጣም ያነሰ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ይህም John and Glendinning (1996) ሴቶች ተማሪዎች ያልገባቸውን ጥያቄ ከመጠየቅ አንፃር የሚያደርጉት ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ ነው በማለት የገለፁትን የጥናት ግኝት የሚደግፍ ነው፡፡

ይህንኑ በተመለከተ ከምልከታ የተገኘው መረጃ ውጤትም ከላይ ከቀረበው ውጤት ጋር የሚጣጣም ነው፡፡ ይህም በተከታታይ በተደረገው ምልከታ የተመዘገበውን የወንዶችና የሴቶችን ጥያቄ የመጠየቅ ድግግሞሽ ውጤት ምልከታው ለተካሄደበት ጊዜ በማካፈል አማካዩን በመውሰድ የተገኘው አሀዝ በምድብ አንድ ጠቅላላ ከተጠየቁ 12 ጥያቄዎች 8 ወይም 66.7% በወንዶች የተጠየቁ ሲሆን ቀሪዎቹ 4ቱ ወይም 33.3፣ በሴቶች የተጠየቁ ናቸው፡፡ በምድብ ሁለትም በጠቅላላ በወንዶችና በሴቶች ከተጠየቁት 8 ጥያቄዎች 6 ወይም 75፣ በወንዶችና ቀሪዎቹ 2ቱ ወይም 25% በሴቶች የተጠየቁ ሲሆን በምድብ ሶስት በጠቅላላ ከተጠየቁት 13 ጥያቄዎች 11 ወይም 84.6% በወንዶች የተጠየቁ ሲሆን ቀሪዎቹ 2ቱ ወይም 15.4% በሴቶቸ የተጠየቁ መሆናቸውን ከመረጃው ውጤት ለመረዳት ተችሏል፡፡ የሶስቱንም ምድቦች በአጠቃላይ ስንመለከትም በጠቅላላው ከተጠየቁት 33 ጥያቄዎች 25ቱ ወይም 80.6% በወንዶች ተማሪዎች የተጠየቁ ናቸው፡፡ ስለዚህ በሁለቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው መረጃ ውጤት እንደሚያሳየው ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ጥያቄ በመጠየቅ የሚያደርጉት ተሳትፎ ከፍተኛ ሲሆን ሴቶች በተቃራኒው ተሳትፎአቸው በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ለመምህራን በቀረበው መጠይቅ፡ "በክፍል ውስጥ ያልገባቸውን ጥያቄ በተደጋጋሚ የሚጠይቁት ወንዶቹ? ወይስ ሴቶቹ? በሚል ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 6 መምህራን 5ቱ ወንዶች መሆናቸውን ገልፀዋል፡፡ እንዲሁም ለተማሪዎች በተሰጠው መጠይቅ፣ "ያልገባህ/ሽን ጥያቄ በመጠየቅ የምታደርገው/ጊው ተሳትፎ ሁኔታ? በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ በምድብ አንድ መጠይቁን ከሞሉት 17 ወንዶች 14ቱ ወይም 82.3% እና ከ29 ሴቶች 10 ወይም 34.5% ሴቶች ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል፡፡ በተመሳሳይ በምድብ ሁለት መጠይቁን ከሞሉት 24 ወንዶች 18 ወይም 75% ወንዶችና 25% ሴቶች በምድብ ሶስት ደግሞ፣ መጠይቁን ከሞሉት 38 ወንዶች፣ 33ቱ ወይም 86.8% ወንዶችና ቀሪዎቹ 13.2% ሴቶች "ከፍተኛና" "በጣም ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል፡፡ ስለዚህም በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ያልገባቸውን ጥያቄ የመጠየቅ ችሎታቸው ከፍተኛ መሆኑንን ከመልሶቻቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡

የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል የሚኖረውን ልዩነት ለመመርመር እንዲያስችል ሊነሳ የሚገባው ጉዳይ ተማሪዎቹ የሚሰጡት መልስ ትክክል መሆን አለመሆኑን ማየት ነው:: ምክንያቱም በምዕራፍ ሁለት ስር እንደተገለፀው Potter (1987:7) ሴቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሱ መሆናቸውን ሲገልፁ ለዚህ ምክንያቱ ሴቶች ተማሪዎች በአብዛኛው የሚሰጡት መልስ ትክክል ባለመሆኑ ነው በማለት የጥናታቸውን ውጤት ገልፀዋል:: ከዚህ አንፃርም በዚህ ጥናት ትክክለኛ መልስ በተደጋጋሚ የሰጡ ወንዶችና ሴቶችን በማወዳደር በክፍል ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ መጠን ለመመርመር ተሞክሯል:: ስለዚህም በጠቅላላ በተማሪዎች ከቀረቡት ትክክለኛ መልሶች በወንዶችና በሴቶች የተሰጡትን በማወዳደር በክፍል ውስጥ ተሳትፎ የተሻለ ውጤት ያስመዘገቡት ወንዶቹ? ወይስ ሴቶቹ? የሚለውን በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመላክቷል፡

ሰንጠረዥ 5፡ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች የቀረቡ ትክክለኛ መልሶች ብዛትን በመቶኛ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ምድብ | በተማሪዎች የተሰጡ ትክክለኛ መልሶች በጠቅላላ | | በወንዶች ተማሪዎች የተመለሱ | | በሴቶች ተማሪዎች የተመለሱ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | 92 | 43 | 61 | 66.3 | 31 | 33.7 |
| 2 | 49 | 23 | 36 | 73.5 | 13 | 26.5 |
| 3 | 73 | 34 | 45 | 61.6 | 28 | 38.4 |
| ጠቅላላ | 214 | 100 | 132 | 61.7 | 82 | 38.3 |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደቀረበው በሶስቱም ምድቦች ሴቶች የሰጧቸው ትክክለኛ መልሶች ብዛት ከወንዶች ያነሰ ነው:: ይህም በሁሉም ምድቦች በጠቅላላ በተማሪዎች ከተሰጡት 214 ትክክለኛ መልሶች 132 ወይም 61.7% በወንዶች የተሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 82 ወይም 38.3% በሴቶች የተመለሱ ናቸው:: የእያንዳንዱን ምድብም ብንመለከት በሴቶች ተማሪዎች የተሰጡ ትክክለኛ መልሶች ከወንዶች በጣም ያነሱ ከመሆናቸውም በተጨማሪ በምድብ ሁለትና ሶስት ዝቅተኛ ነው ለማለት ይቻላል:: ስለዚህ ትክክለኛ መልስ ከመስጠት አንፃር ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ተሳትፎ አላቸው ለማለትም ያስደፍራል::

በምልከታ የተገኘው ውጤትም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው:: በየምድቦቹ ከተደረገው ተከታታይ ምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየው በምድብ አንድ በጠቅላላ በተማሪዎች የተሰጡ ትክክለኛ መልሶች በሁሉም የምልከታ ቀናት ተመዝግቦ አማካዩ ተወስዶ በተገኘው ውጤት መሰረት 120 ሲሆን ከነዚህ መሀል 70ዎቹ ወይም 58.3% በወንዶች የተመለሱ ሲሆኑ

ቀሪዎቹ 50ዎች ወይም 41.6% በሴቶች የተመለሱ ናቸው፡፡ በምድብ ሁለትና ሶስትም በተማሪዎች የተሰጡ ትክክለኛ መልሶች 58 እና 84 በቅደም ተከተል ሲሆኑ በምድብ ሁለት ከ58 መልሶች 42ቱ ወይም 72.4% በወንዶች የተሰጡ ትክክለኛ መልሶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 16ቱ ወይም 27.6% በሴቶች የተሰጡ ናቸው፡፡

በምድብ ሶስት ደግሞ በጠቅላላ በተማሪዎች ከተሰጡት 84 ትክክለኛ መልሶች 58ቱ ወይም 69% በወንዶች የተሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 26ቱ ወይም 31% በሴቶች የተመለሱ መሆናቸውን መረጃው አሳይቷል፡፡ በየምድቦቹ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ በሶስቱም ምድቦች ሴቶች ትክክለኛ መልስ ከመስጠት አንፃር የሚያደርጉት ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ያነሰ ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ቀደም ሲል ከቀረበው ማብራሪያ በተጨማሪ ተማሪዎቹ የሚሰጧቸውን መልሶች በሁለት ወገን በመክፈል የወንዶችንና የሴቶችን ተሳትፎ መጠን ለመመርመር ይቻላል፡፡ ይህም የሰጧቸውን መልሶች በተማሪዎች ፈቃደኝነት (እጅ በማውጣት) የተመለሱና በመምህሩ አነሳሽነት (እጅ ሳያወጡ) ወይም ፈቃደኛ ባልሆኑ ተማሪዎች የተመለሱ በማለት በመለየት ሲሆን በሁለቱም የመልስ አሰጣጥ መንገዶች የወንዶችና የሴቶችን ተሳትፎ መጠን እንደሚከተለው ለማቅረብ ተሞክሯል፡፡

ሰንጠረዥ 6፡ ከተማሪዎች መልስ አሰጣጥ አንፃር በወንዶችና በሴቶች መካከል የሚኖረውን የተሳትፎ ልዩነት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| መልስ የተሰጠበት መንገድ | ምድብ አንድ | | | | | | ምድብ ሁለት | | | | | | ምድብ ሶስት | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | በተማሪዎች የተሰጡ ጠቅላላ መልሶች | | በወንዶች የተመለሱ | | በሴቶች የተመለሱ | | በተማሪዎች የተሰጡ ጠቅላላ መልሶች | | በወንዶች የተመለሱ | | በሴቶች የተመለሱ | | በተማሪዎች የተመለሱ ጠቅላላ መልሶች | | በወንዶች የተመለሱ | | በሴቶች የተመለሱ | |
| | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| በተማሪዎች ፈቃደኝነት | 80 | 87 | 50 | 62.5 | 30 | 37.5 | 38 | 77.6 | 28 | 73.7 | 10 | 26.3 | 56 | 76.7 | 35 | 62.5 | 21 | 37.5 |
| በመምህሩ አነሳሽነት | 12 | 13 | 10 | 83.3 | 2 | 16.7 | 11 | 22.4 | 8 | 72.7 | 3 | 27.3 | 17 | 23.3 | 13 | 76.5 | 4 | 23.5 |
| ጠቅላላ | 92 | 100 | 60 | 65.2 | 32 | 34.8 | 49 | 100 | 36 | 73.5 | 13 | 26.5 | 73 | 100 | 48 | 65.7 | 25 | 34.3 |

በሰንጠረዡ እንደተመለከተው በሶስቱም ምድቦች በጠቅላላው በተማሪዎች ከተሰጡት መልሶች አብዛኞቹ በተማሪዎች ፈቃደኝነት የተመለሱ ናቸው:: ከዚህ አንፃርም በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት በተመለከተ በሶስቱም ምድቦች በተማሪዎች ፈቃደኝነት ከተሰጡት ጠቅላላ መልሶች በወንዶች ተማሪዎች የተሰጡት ከፍተኛውን ቁጥር ይዘዋል::

የየምድቦቹን ለየብቻ ስንመለከት ደግሞ በምድብ አንድ በጠቅላላው በተማሪዎች ፈቃደኝነት ከተሰጡት 80 መልሶች 50 ወይም 62.5% በወንዶች፣ ቀሪዎቹ 30 ወይም 37.5% በሴቶች፣ የተመለሱ ናቸው:: በምድብ ሁለት ከጠቅላላው 38 መልሶች 28ቱ ወይም 73.7% በወንዶች፣ ቀሪዎቹ 10 ወይም 26.3% በሴቶች የተሰጡ ናቸው:: በምድብ ሶስትም ከጠቅላላው 56 መልሶች 35ቱ ወይም 62.5% በወንዶች ቀሪዎቹ 21 ወይም 37.5% በሴቶች የቀረቡ ናቸው::

በመምህሩ አነሳሽነት ከተሰጡት የተማሪዎች መልሶችም በወንዶች የተሰጡት የበለጠውን አሀዝ ይዘዋል:: በምድብ አንድ በመምህሩ አነሳሽነት ተማሪዎች ከሰጧቸው ጠቅላላ 12 መልሶች 10 ወይም 83.3% በወንዶች የተሰጡ ሲሆን፥ በምድብ ሁለት ከጠቅላላው 11 መለሶች 8ቱ ወይም 72.7% በምድብ ሶስት ከ17 መልሶች 13ቱ ወይም 76.5% በወንዶች የተሰጡ ናቸው:: ስለዚህ በሶስቱም ምድቦች በወንዶች የተሰጡ መልሶች በርካታ ናቸው::

በፈቃደኝነትም ሆነ በመምህሩ አነሳሽነት ተማሪዎቹ ከሚሰጡት መልስ አንፃር ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ተሳትፎ እንዳደረጉ ከሶስቱም ምድቦች የተገኘው ውጤት ያሳያል:: ይህን በሚመለከት ከምልከታውና ከተማሪዎቹ መጠይቅም የተገኘው ውጤት ከላይ የቀረበውን ውጤት የሚደግፍ ሆኗል::

በተማሪዎቹ በፈቃደኝነትና በመምህሩ አነሳሽነት የሚሰጡት መልስ መጠን" በሚል ለቀረበ ንጥብ በሁሉም የምልከታ ቀናት በየምድቦቹ የተመዘገበው ውጤት አማካዩ እንደሚያሳየው በሶስቱም ምድቦች በሁለቱም የመልስ አሰጣጥ መንገዶች በወንዶች የተሰጡ መልሶች ይበልጣሉ:: ስለዚህም በምድብ አንድ በተማሪዎች ፈቃደኝነት የተሰጡ ጠቅላላ መልሶች 95 ሲሆን ከዚህ ውስጥ 59 ወይም 62% በወንዶች ቀሪዎቹ 36ቱ ወይም 38% በሴቶች የቀረቡ ናቸው:: በምድብ ሁለት ከጠቅላላው 62 መልሶች 48ቱ ወይም 77.4% በወንዶች ቀሪዎቹ 14 ወይም 22.6% በሴቶች የተሰጡ ሲሆን በምድብ ሶስት ደግሞ ከጠቅላላው 89 መልሶች 60 ወይም 67.4% በወንዶችና ቀሪዎቹ 29 ወይም 32.6% በሴቶች የተሰጡ መልሶች ናቸው::

በመምህሩ አነሳሽነት የተሰጡ መልሶችን በሚመለከት ደግሞ በምድብ አንድ በመምህር አነሳሽነት ጠቅላላ በተማሪዎች ከተሰጡ 32 መልሶች 24ቱ ወይም 75% በወንዶች፥ ቀሪዎቹ 8ቱ ወይም 25% በሴቶች የተሰጡ ሲሆን፣ በምድብ ሁለት ከጠቅላላው 29 መልሶች 18ቱ

ወይም 63% በወንዶች ቀሪዎቹ 11 ወይም 37% በሴቶች የተሰጡ ናቸው:: በምድብ ሶስት ደግሞ ከጠቅላላው 42 መልሶች 28ቱ ወይም 65% በወንዶች ቀሪዎቹ 14ቱ ወይም 35% በሴቶች የቀረቡ ናቸው:: ስለዚህ በሶስቱም ምድቦች በተማሪዎች ፈቃደኝነትም ሆነ በመምህሩ አነሳሽነት ከተሰጡት መልሶች በወንዶች ተማሪዎች የተሰጡት በርካታ ናቸው:: ከዚህ አንፃርም ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ለመገንዘብ ይቻላል::

ለተማሪዎች በቀረበው የፅሁፍ መጠይቅም "ለጥያቄዎች በራስህ/ሽ ፍላጎት መልስ የመስጠት ብቃትህ/ሽ" በሚል ለቀረበ ጥያቄ በምድብ አንድ መጠይቁን ከሞሉት 17 ወንዶች 11 ወይም 64.7% እና ከ29 ሴቶች 10 ወይም 34.5% በምድብ ሁለት መጠይቁን ከሞሉት 24 ወንዶች 17ቱ ወይም 70.8% ና ከ22 ሴቶች 9 ወይም 40.9% በምድብ ሶስት መጠይቁን ከሞሉት 38 ወንዶች 28 ወይም 73.7% እና ከ17 ሴቶች 7 ወይም 41.2% "በጣም ከፍተኛ" ና "ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል:: የተማሪዎቹ ምላሽም የሚያሳየው ወንዶች በራሳቸው ፈቃደኝነት መልስ ከመስጠት አንፃር ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ነው::

በሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች በተገኘው መረጃ ውጤት ተማሪዎቹ በራሳቸው ፈቃደኝነትም ሆነ በመምህሩ አነሳሽነት ከሰጡት መልስ መጠን አንፃር ያላቸውን ተሳትፎ በተመለከተ ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ለማረጋገጥ ተችሏል::

ከላይ ለማሳየት የተሞከረው የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከሚነሱ ጉዳዮች አንፃር በየምድቦቹ በሚማሩ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች መካከል የሚታየውን የተሳትፎ ልዩነት ሲሆን በሶስቱም ምድቦች የወንዶች ተሳትፎ ከሴቶች የተሻለ ሆኖአል:: ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ቀደም ብሎ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠን ለመመርመር ከተነሱት ጉዳዮች አንፃር በሶስቱ ምድቦች ከሚማሩት ሴቶች በየትኛው ምድብ የሚማሩት የተሻለ ተሳትፎ አድርገዋል የሚለውን እንመለከታለን::

ሰንጠረዥ 7፡- በሶስቱም ምድቦች የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከቪዲዮ ምዝግቡ የተገኘ መረጃ ውጤት

| [illegible] | ምድብ አንድ | | ምድብ ሁለት | | ምድብ ሶስት | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሰዓት | አማካይ | ሰዓት | አማካይ | ሰዓት | አማካይ |
| [illegible] | 680 | 18.8 | 180 | 8.2 | 230 | 13.5 |
| [illegible] | 31 | 1.2 | 17 | 0.8 | 35 | 2.1 |
| [illegible] | 2 | 0.07 | 1 | 0.05 | - | - |
| [illegible] | 41 | 1.4 | 13 | 0.6 | 28 | 1.6 |
| [illegible] | 39 | 1.34 | 10 | 0.45 | 21 | 1.2 |
| [illegible] | 2 | 0.07 | 3 | 0.14 | 7 | 0.4 |
| [illegible] | 813 | 21.2 | 224 | 18.2 | 321 | 18.9 |

ሰንጠረዥ 9፡ የወንዶችና የሴቶችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ምድብ | ተራ ቁ | ይዘት | 5 | | | | 4 | | | | 3 | | | | 2 | | | | 1 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | 1 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለዉ/ሽ ተሳትፎ | 7 | 41.2 | 5 | 17.2 | 6 | 35.3 | 9 | 31 | 2 | 11.8 | 4 | 13.8 | 2 | 11.8 | 5 | 17.2 | - | - | 6 | 20.7 |
| | 2 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተያቄዎች መልስ ለመስጠት የምታደርገው/ጊው ሙከራ | 5 | 29.4 | 8 | 27.6 | 7 | 41.2 | 5 | 17.2 | 4 | 23.5 | 5 | 17.2 | 1 | 5.9 | 6 | 20.7 | - | - | 5 | 23.5 |
| 2 | 1 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለዉ/ሽ ተሳትፎ | 7 | 29.2 | 7 | 31.8 | 10 | 41.7 | 2 | 9.1 | 5 | 20.8 | 7 | 31.8 | - | - | 5 | 22.7 | - | - | 1 | 4.5 |
| | 2 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተያቄዎች መልስ ለመስጠት የምታደርገው/ጊው ሙከራ | 9 | 37.5 | 6 | 27.3 | 5 | 20.8 | 4 | 16.7 | 4 | 18.2 | 5 | 22.7 | 2 | 8.3 | 3 | 13.6 | 4 | 16.7 | 4 | 18.2 |
| 3 | 1 | በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለዉ/ሽ ተሳትፎ | 14 | 36.8 | 4 | 23.5 | 15 | 39.5 | 4 | 23.5 | 5 | 13.2 | 3 | 17.6 | 2 | 5.3 | 3 | 17.6 | 2 | 5.3 | 1 | 5.9 |
| | 2 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማሩ ሂደት ለተያቄዎች መልስ ለመስጠት የምታደርገው/ጊው ሙከራ | 12 | 31.6 | 8 | 47.1 | 15 | 39.5 | 2 | 11.8 | 4 | 10.5 | 4 | 23.5 | 3 | 7.9 | 2 | 11.8 | 4 | 10.5 | 1 | 5.9 |

በአማራጭነት የቀረቡት ቁጥሮች 5 "በጣም ከፍተኛ"፣ 4 "ከፍተኛ" 3 "መካከለኛ" 2 "ዝቅተኛ" 1 "በጣም ዝቅተኛ" የሚሉትን የሊከርት መለከኪያዎችን (Likert Scale) የሚወክሉ ናቸው።

በሰንጠረዡ እንደተገለፀው፣ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያላቸውን ተሳትፎ በሚመለከት ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ከሴቶች የላቀ ተሳትፎ እንዳላቸው ገልፀዋል። ይህም በምድብ አንድ መጠይቁን ከሞሉት 17 ወንዶች መካከል 13 ወይም 76.5% እና በ29 ሴቶች 14 ወይም 48.3% ፣ በምድብ ሁለት መጠይቁን ከሞሉት 24 ወንዶች መካከል 17ቱ ወይም 70.8% እና ከ22 ሴቶች 9 ወይም 40.9%፣ በምድብ ሶስት መላሾቹ 29 ወይም 76.3% ወንዶችና 8 ወይም 47.1% ሴቶች "በጣም ከፍተኛ" እና "ከፍተኛ" የሚል መልስ ሰጥተዋል።

በተራ ቁጥር 2 "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማሩ ሂደት ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የምታደርገው/ጊው ሙከራ? " በሚል ለቀረበው ጥያቄም በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ለጥያቄዎች መልስ በመስጠት የሚያደርጉት ተሳትፎ ከሴቶች የበለጠ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ገልፀዋል። ይህም በምድብ አንድ ከመላሾቹ 12 ወይም 70.6% ወንዶችና 13 ወይም 46.6% ሴቶች "ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ" በማለት መልስ ሰጥተዋል፤ በምድብ ሁለትም ከመላሾቹ 14 ወይም 58.3% ወንዶችና 10 ወይም 44% ሴቶች፣ በምድብ ሶስት ከመላሾቹ 27 ወይም 71.3% ወንዶችና 10 ወይም 58.9% ሴቶች "ከፍተኛና "በጣም ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል። ከዚህ አንፃር በሶስቱም ምድቦች በወንዶችና በሴቶች መካከል ልዩነት መኖሩን መገንዘብ ይቻላል። ሆኖም የሴቶችም ተሳትፎ የተሻለ መሆኑን ከሰጧቸው አዎንታዊ ምላሾች ለማየት ተችሏል።

በአጠቃላይ ከላይ ለማሳየት የተሞከረው በሶስቱም ምድቦች (ማለትም ሴቶች በሚበዙበት፣ ከወንዶች ጋር እኩል በሚሆኑበትና ወንዶች በሚበዙበት) የወንዶችና የሴቶችን ተሳትፎ በተመለከተ ተማሪዎቹ ለቀረበላቸው የፅሁፍ መጠይቅ ከሰጧቸው መልሶች የተገኘውን ውጤት ነው። በዚህም በሁሉም ምድቦች በወንዶችና በሴቶች መካከል የተሳትፎ ልዩነት መኖሩንና ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ ማድረጋቸውን ከመረጃው ውጤት ለመገንዘብ ይቻላል። ከዚህ በተጨማሪም ከላይ ከተነሱት ጥያቄዎች አንፃር በሶስቱ ምድቦች በሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች መካከል የሚታየውን የተሳትፎ ልዩነት ስንመረምር የጎላ ልዩነት አለመታየቱን ለማረጋገጥ ተችሏል።

ይህም በተራ ቁጥር አንድ "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ያለሽ ተሳትፎ መጠን" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ በምድብ አንድ መጠይቁን ከሞሉት 29 ሴቶች 14ቱ ወይም 48.3%

በምድብ ሁለት ከ22 ሴቶች 9 ወይም 40.9% እና በምድብ ሶስት ከ17 ሴቶች 8ቱ ወይም 47.1% "በጣም ከፍተኛ" እና "ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል:: በተራ ቁጥር ሁለትም "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በመማር ማስተማሩ ሂደት ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የምታደርጊው ሙከራ" በሚል ለቀረበው ጥያቄ ደግሞ በምድብ አንድ ከመላሾቹ 13ቱ ወይም 44.8% በምድብ ሁለት 10 ወይም 45.5% በምድብ ሶስት 8 ወይም 47% "በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ" በማለት መልስ ሰጥተዋል:: ስለዚህ ለሁለቱም ጥያቄዎች በሶስቱም ምድቦች የሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች ከሰጧቸው አዎንታዊ መልሶች አንፃር በመካከላቸው የተሳትፎ ልዩነት የለም ለማለት ይቻላል::

በአጠቃላይ ከላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በተመለከተ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ፣ ከቪዲዮ ምዝገባና ፣ ከምልከታ በተገኘው መረጃ ወንዶች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሴቶች የበለጡ መሆናቸውንና በሶስቱም ምድቦች በሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች መካከል የተሳትፎ ልዩነት አለመኖሩን ለማረጋገጥ ተሞክሯል::

ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ከሚያደርጉ ምክንያቶች አንዱ ሴቶች ወንዶች ጓደኞቻቸውና መምህሮቻቸው ፊት ለመናገር አለመድፈር (ሀሳባት ይስቁብኛል በሚል ፍርሃት) በዚህም ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ዝቅተኛ በመሆኑ ነው በማለት Tsige Haile(1991),Clerk and Tranford (1995) ገልፀዋል:: ከዚህ ሀሳብ በመነሳትም በዚህ ጥናት በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል የሚኖረውን ልዩነት ለመመርመር ለተማሪዎች ጥያቄዎች ቀርበው የሚከተለው መልስ ተገኝቷል::

ሰንጠረዥ 10፡ ወንዶችና ሴቶች ለራሳቸው የሚሰጡትን ግምት በሚመለከት ለቀረቡላቸው ተያቂዎች የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ምድብ | የጥ ቁ | ጥያቄ | 5 | | | | 4 | | | | 3 | | | | 2 | | | | 1 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | 3 | በምትማሩበት ጊዜ ሌሎች ሊመለከቱዋችሁ የሚፈልጉት ሁኔታዎች | 6 | [illegible] | 8 | 27.6 | 2 | 10.8 | 4 | 13.8 | 2 | 10.8 | 3 | 10.3 | 4 | 10.7 | 6 | 27.6 | 3 | 17.3 | 6 | 20.7 |
| | 4 | ለተያቂዎች መልስ ለመስጠት በምትፈልጉበት ጊዜ ብዙሃኑ ይሰሙላችሁ ዘንድ የሚያደርጉዋቸው ጥረቶች | 5 | 17.6 | 7 | 24 | 2 | 10.8 | 9 | 31 | 3 | 17.6 | 3 | 10.3 | 7 | 41.2 | 9 | 31 | 2 | 11.8 | 1 | 3.4 |
| 2 | 3 | በምትማሩበት ጊዜ ሌሎች ሊመለከቱዋችሁ የሚፈልጉት ሁኔታዎች | 3 | 12.5 | 5 | 20.8 | 2 | 8.3 | 6 | 27.3 | 3 | 12.5 | 4 | 18.2 | 10 | 41.7 | 2 | 9.1 | 6 | 25 | 3 | 13.6 |
| | 4 | ለተያቂዎች መልስ ለመስጠት በምትፈልጉበት ጊዜ ብዙሃኑ ይሰሙላችሁ ዘንድ የሚያደርጉዋቸው ጥረቶች | 4 | 16.7 | 4 | 18.2 | 2 | 8.3 | 8 | 36.4 | 4 | 16.7 | 4 | 18.2 | 5 | 20.8 | 3 | 13.6 | 9 | 37.5 | 3 | 13.6 |
| 3 | 3 | በምትማሩበት ጊዜ ሌሎች ሊመለከቱዋችሁ የሚፈልጉት ሁኔታዎች | 2 | 5.3 | 7 | 41.2 | 6 | 15.8 | 6 | 35.3 | 4 | 10.5 | 1 | 5.9 | 17 | 44.7 | 2 | 11.8 | 9 | 23.7 | 1 | 5.9 |
| | 4 | ለተያቂዎች መልስ ለመስጠት በምትፈልጉበት ጊዜ ብዙሃኑ ይሰሙላችሁ ዘንድ የሚያደርጉዋቸው ጥረቶች | 5 | 13.2 | 8 | 47.1 | 4 | 10.5 | 4 | 23.5 | 6 | 15.8 | 2 | 11.8 | 13 | 34.2 | 3 | 17.6 | 10 | 26.3 | ---- | ---- |

ከላይ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው ተማሪዎቹ ለራሳቸው የሚሰጡትን ግምት /Self-esteem/ በሚመለከት ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ከፍተኛ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል:: ለዚህም ለምሳሌ በተራ ቁጥር 3 "በምትናገር/ሪበት ጊዜ ሌሎች ሲመለከቱህ/ሽ የመፍራት ሁኔታህ/ሽ" በሚል ለቀረበ ጥያቄ በምድብ አንድ 9 ወይም 53% ወንዶች "ዝቅተኛ" ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት ሲመልሱ በተቃራኒው 12 ወይም 58.6% ሴቶች "ከፍተኛና" "በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል:: በምድብ ሁለት 16 ወይም 66.7% ወንዶች "ዝቅተኛ" ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት ሲመልሱ በተቃራኒው 13 ወይም 59% ሴቶች "ከፍተኛና" በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል:: በምድብ ሶስትም 26 ወይም 68.4% ወንዶች "ዝቅተኛ" ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት ሲመልሱ 13 ወይም 76.5% ሴቶች ከፍተኛና "በጣም ከፍተኛ" በማለት መልስ ሰጥተዋል:: ከዚህ አንፃር በሶስቱም ምድቦች ሴቶች ተማሪዎች በሚናገሩበት ጊዜ ሌሎች ሲመለከቷቸው የመፍራት ሁኔታቸው ከፍተኛ መሆኑን ለመገንዘብ ይቻላል::

በጥያቄ ቁጥር 4 "ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በምትፈልግ/ጊበት ጊዜ ብሳሳት ይስቁብኛል በሚል የሚኖርህ/ሽ ፍርሃት" በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄ በምድብ አንድ ከመላሾቹ 9 ወይም 53% ወንዶች "ዝቅተኛና" በጣም ዝቅተኛ ሲሉ፣ በተቃራኒው 16 ወይም 55% ሴቶች "ከፍተኛና" በጣም ከፍተኛ" በማለት መልስ ሰጥተዋል:: በምድብ ሁለት 14 ወይም 58.3% ወንዶች "ዝቅተኛ" ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት ሲመልሱ በተቃራኒው 12 ወይም 54.6% ሴቶች ከፍተኛና በጣም ከፍተኛ በማለት መልሰዋል:: በምድብ ሶስትም 23 ወይም 60.5% ወንዶች "ዝቅተኛ" ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት ሲመልሱ በተቃራኒው 12 ወይም 70.6% ሴቶች "ከፍተኛ" ና "በጣም ከፍተኛ" በማለት መልስ ሰጥተዋል:: ስለዚህም በሶስቱም ምድቦች ሴቶች መልስ ለመስጠት ቢፈልጉም ብሳሳት ይሳቅብኛል በሚል የሚኖራቸው ፍርሃት ከወንዶች የበለጠና ከፍተኛም መሆኑን ከመልሶቻቸው ለመመልከት ይቻላል::

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ለተማሪዎች በቀረበው መጠይቅ በመማር ማስተማሩ ሂደት ያላቸውን ተሳትፎ መጠን ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ተሳትፎ እንዳላቸው ገልፀዋል:: ለዚህ ምክንያቱን እንዲገልፁ ተጠይቀውም ከሰጡት አስተያየት መካከል በሶስቱም ምድቦች "ስለምፈራና፣ "ብሳሳት ይስቁብኛል" በማለት ለመናገር ስለማልደፍር አልሳተፍም::" በማለት በርካታ ሴቶች ተማሪዎች የሰጡት አስተያየት ይገኝበታል:: በዚህም ሴቶች ሲናገሩ ሌሎች ሲመለከቷቸው ስለሚፈሩና "ብሳሳት ይሳቅብኛል" በሚል ዝምታን ስለሚመርጡ በተሳትፎም ዝቅተኛ ሆነዋል::

ለመምህራን በቀረበው መጠይቅም የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ያነስ

መሆን በተናቶቻቸው ያረጋገጡ ምሁራን ለተሳትፎአቸው ማነስ ምክንያት ያሏቸውን በመውሰድ በዚህ ጥናትም የሴቶች ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ መሆኑን የሚገልፁ መምህራን በመጨረሻ ለተረበው ጥያቄ በአማራጭነት ከቀረቡት ምክያቶች በራሳቸው ግምት እንዲመርጧቸው በተጠየቁበት ጊዜ አብዛኛው መምህራን "ሴቶች አይነአፋር በመሆናቸውና 'ብሳሳት ይስቁብኛል' በሚል ስለሚፈሩ ለመሳተፍ አይነሳሱም" የሚለውን በከፍተኛ ደረጃ መርጠውታል:: በዚህም ከተማሪዎችም ሆነ ከመምህራን መጠይቅ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ሴቶች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ ውጤት ያስመዘገቡት ለመሳተፍ ቢፈልጉም ስለሚፈሩና 'ብሳሳት ይስቁብኛል' በሚል ስሜት ያላቸው ፍርሃት ከፍተኛ በመሆኑ ነው::

### 4.2.2. ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከቪዲዮ ምዝገባ፣ ከምልከታውና ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ቀደም ብሎ ቀርቧል:: ከዚህ በመቀጠል ደግሞ ለማቅረብ የተሞከረው ከላይ በሶስቱም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተነሱ ጉዳዮች ጋር የሚዛመድ ነው:: በዚህም መጠይቁን የሞሉት ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲሆኑ ሁሉም ወንዶች ናቸው:: የተገኘው ውጤትም የሚከተለውን ይመስላል

ሰንጠረዥ 11፡ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ከመምህራን የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | አማራጮች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንዶች | | ሴቶች | | ሁለቱም እኩል | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጃቸውን በተደጋጋሚ የሚያወጡት | 4 | 66.7 | - | - | 2 | 33.3 |
| 2 | ያልገባቸውን ጥያቄ በተደጋጋሚ የሚጠይቁት | 4 | 66.7 | - | - | 2 | 33.3 |
| 3 | ሲጠየቁም ትክክለኛ መልስ የሚሰጡት | 5 | 83.3 | 1 | 16.66 | | |
| 4 | እጃቸውን ሳያወጡ በመምህሩ አነሳሽነት ለጥያቄዎች መልስ የሚሰጡት | 3 | 50 | 2 | 33.3 | 1 | 16.66 |
| 5 | ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ብዙ ጊዜ እድል የሚያገኙት | 4 | 66.7 | 1 | 16.66 | 1 | 16.66 |
| 6 | በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተሻለ ተሳትፎ ያላቸው | 6 | 100 | - | - | - | - |

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ በሚመለከት ለቀረቡላቸው ጠቅላላ ጥያቄዎች መምህራን የሰጧቸው መልሶች በተሳትፎ ወንዶች ከሴቶች የሚበልጡ መሆኑን የሚያስገነዝቡ ናቸው። በተለይ "በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ የተሻለ ተሳትፎ ያላቸው ከወንዶችና ከሴቶች የትኞቹ ናቸው" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ መጠይቁን የሞሉት ስድስት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን በሙሉ ወንዶች መሆናቸውን ገልፀዋል። በሌሎቹም ተሳትፎን በሚመለከት በቀረቡት ጉዳዮች ስር የሰጧቸው መልሶች ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ እንዳላቸው የሚያሳዩ ናቸው። ይህም ቀደም ብሎ ከቪዲዮ ምዝገባና ከምልከታው እንዲሁም ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ ውጤት ጋር የሚጣጣም ነው።

ከዚህ ሌላ በአጠቃላይ "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ በሚደረግ የመምህር ተማሪ ተራክቦ የጾታ ልዩነት አለን?" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ 5ቱ ወይም 83.3% "አዎ" በማለት መልስ ሰጥተዋል።

በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል የተሳትፎ ልዩነት አለ ወይም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ተሳታፊዎች ናቸው በማለት መልስ የሰጡት መምህራን የሰጡት አስተያየትም የሚከተለውን ይመስላል፤

<u>ሴቶች ተማሪዎችን በሚመለከት፤</u>

ሴቶች የቤት ስራ ሰርተው ስለማይመጡ

ባለባቸው የባህል ተፅዕኖ ከሰዎች ፊት ለመናገር ስለሚፈሩ

ለውበትና ለፍቅር ትኩረት ስለሚሰጡ በክፍል ውስጥ የሚኖራቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ ነው።

<u>ወንዶች ተማሪዎችን በሚመለከት</u>

ለመሳተፍ ፍላጎታቸው ከፍተኛ በመሆኑ

መልስ ለመስጠት "እሳሳታለሁ" ብለው ስለማይጨነቁ

የቤት ስራ ሰርተው ስለሚመጡና ድፍረት፣ ልበሙሉነት ስለሚሰማቸው በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሴቶች የበለጡ ናቸው በማለት አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በመሆኑም እነዚህ በመምህራን የተሰጡ አስተያየቶች በምዕራፍ ሁለት ስር ለሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማነስ ዋና ዋና ምክንያቶች ብለው የተለያዩ ምሁራን ከገለጿቸው ጋር የሚቀመዱ ናቸው። እነዚህም ሴቶች አይናፋር በመሆናቸው፣ በባህል ተፅዕኖ ሴቶች ከወንዶች እኩል ማውራትና መከራከር ስለማይችሉ፣ በወንዶች ጓደኞቻቸውና በመምህሮቻቸው ፊት ለመናገር ስለሚፈሩ፣ እንዲሁም ሴቶች ለውበትና ለፍቅር ያላቸው ዝንባሌ ከፍተኛ በመሆኑ በትምህርት መስክ ያላቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑን የሚገልፁ ናቸው። በዚህ ጥናትም ከመምህራኑም ሆነ ከተማሪዎች የተገኙት አስተያየቶች በምዕራፍ ሁለት በተለያዩ ምሁራን ከተሰጡት ምክንያቶች ጋር የሚጣጣሙ ሆነው ተገኝተዋል።

በመጨረሻም በመምህራኑ መጠይቅ ላይ በክፍል ሶስት ለቀረበላቸው ጥያቄ አብዛኞዎቹ መምህራን የመረጧቸው በጥናቱ ትኩረት ከሚሰጥባቸው ነጥቦች አንፃር እንደሚከተለው ቀርበዋል።

ሰንጠረዥ 12፡- የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ የሆነበትን ምክንያት በተመለከተ ከመምህራን የተሰጡት አስተያየቶች በምን ላይ ያተኮሩ እንደሆኑ የሚያሳይ፡-

| ተ.ቁ | ጥያቄ | ብዛት | % |
|---|---|---|---|
| 1 | የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ የሆነባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? | | |
| | ሀ. መምህራን ወንዶችና ሴቶችን እኩል ስለማያሳትፉ (ለሴቶች የሚሰጡት ትኩረት አነስተኛ በመሆኑ) | 2 | 33.3 |
| | ለ. በክፍል ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ ወንዶች የበለጠ ተሳታፊዎች በመሆናቸው | 2 | 33.3 |
| | ሐ. ሴቶች "ብናገር እሳሳታለሁ" በዚህም "ይስቁብኛል" በሚል የሚኖራቸው ፍርሃት ከፍተኛ በመሆኑና ዝምታን ስለሚመርጡ | 4 | 66.7 |
| | መ. ሴቶች በራስ የመተማመን ችሎታቸውም ሆነ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ዝቅተኛ በመሆኑ | 3 | 50 |
| | ሰ. በክፍል ውስጥ ሴቶች ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከወንዶች እኩል እድል ስለማያገኙ | 4 | 66.7 |
| | ሸ. ሴቶች በሚኖሩበት ጊዜ በመምህሮቻቸውና በጓደኞቻቸው ንግግራቸው በመቋረጡ | 3 | 50 |
| | ቀ. ሴቶች አይናፋር በመሆናቸው ለመሳተፍ ስለማይነሳሱ | 4 | 66.7 |
| | በ. በትምህርት ችሎታ ሴቶች ከወንዶች ያነሱ በመሆናቸው | 1 | 16.7 |
| | ተ. ሴቶች ከወንዶች እኩል ትምህርቱን ለመከታተል ስለማይችሉ | 2 | 33.3 |

* የመልስ ሰጪዎች ቁጥር የበለጠው አንድ መምህር ከአንድ በላይ ምክንያቶችን በመምረጡ ነው

ከላይ ለቀረበው ጥያቄ ማለትም ሴቶች ከወንዶች ያነሰ ተሳትፎ ሊኖራቸው የቻለው በሚከተሉት ምክንያቶች መሆኑን አብዛኞዎቹ መምህራን የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ ነው፡፡

1. ሴቶች "ብሳሳት ይስቁብኛል" በሚል ለመናገር ስለማይደፍሩ
2. ሴቶች በክፍል ውስጥ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እንዲችሉ ከወንዶች እኩል እድል ስለማያገኙ
3. ሴቶች ስለሚፈሩ ወይም አይናፋር በመሆናቸው ለመሳተፍ ስለማይነሳሱ
4. ሴቶች በራስ የመተማመን ችሎታቸውም ሆነ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ዝቅተኛ በመሆኑ

5. ሴቶች በሚናገሩበት ጊዜ በመምህሮቻቸውና በጓደኞቻቸው ንግግራቸው በመቋረጡ ከ1-5 የቀረቡት ነጥቦች ለሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ማነስ በምክንያትነት የተሰጡ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም መምህራኑ የሚከተሉት ምክንያቶች እንዳሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በነጅ ባህል ተፅዕኖ ሴቶች ወደ ጓዳ በሚለው የቤተሰብ ባህል ምክንያት ሴቶች ከማህበረሰቡ ጋር ሰፊ ተራክቦ ስለማይኖራቸው

ከወንዶች እኩል ድፍረት ስለሌላቸው

ሴቶች የቤት ስራ ሰርተው ስለማይመጡ

የሚሉት በዋናነት በአብዛኞዎቹ መምህራን የተሰጡ ናቸው። መምህራኑ አስተያየታቸውን አክለው ሲገልፁም ሴቶች ከወንዶች እኩል እንዲናገሩና ከህብረተሰቡም ጋር ያላቸው ተራክቦ ከፍተኛ እንዲሆን ቢደረግ የተሻለ ተሳትፎ ይኖራቸዋል። እንዲሁም ከመምህራኑም ጋር ከወንዶች እኩል ቅርበት ቢኖራቸው በተሳትፎም ከወንዶች እኩል ብቻ ሳይሆን ሊበልጡም ይችላሉ በማለት ገልፀዋል።

## 4.3. መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት (Teacher treatment) እና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ (Verbal-feedback)

Irvin 1986), Potter (1987), Ehrlich (1997), Kelly (1988) እና Holmes (1994)ን ጠቅሰው እንደሚሉት በክፍል ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ የወንዶችና የሴቶችን ተሳትፎ ከመምህሩ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ጋር ያለውን ግንኙነት ሲታይ ሴቶች በተሳትፎም ሆነ ከመምህሩ በሚያገኙት ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ ከወንዶች ያነሱ መሆናቸውን ለመረዳት ይቻላል። እንዲሁም ሴቶች በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሱ የሆኑበት ምክንያት መምህራን ለሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች እኩል ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ስለማይሰጧቸው (Ehrlich 1997) ገልፀዋል። ከዚህ አንፃር በዚህ ጥናትም በየምድቦቹ የወንዶችና የሴቶች መጠነ ንግግር ማነስና መብዛት በሴቶች ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ያለውን ተፅዕኖ ከመመርመር በተጨማሪ የመምህራኑ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተሳትፎአቸው ላይ ያለውን ተፅዕኖ ማየት አስፈላጊ በመሆኑ በዚህ ጥናት የተተኮረበት ሌላው ጉዳይ ነው።

የመምህራን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተም በመስኩ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን ከላይ የተጠቀሱትን ጨምሮ ካነሷቸው ጉዳዮች ከዚህ ጥናት አላማ ጋር የሚዛመዱትን በመውሰድ የተገኘውን መረጃ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተችሏል፡

### 4.3.1. መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ከቪዲዮ ምዝግቡ የተገኘ መረጃ ትንተና

#### 4.3.1.1. የመምህራኑን ትኩረት በተመለከተ ከቪዲዮ ምዝግቡ የተገኘ መረጃ ውጤት

የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከጾታና ከመምህሩ ትኩረት እና ምጋቤ ምላሽ አንፃር የመረመሩ በርካታ ምሁራን መኖራቸው ቀደም ብሎ ተገልጿል:: ከእነዚህም መካከል Foster(1978), Irvin(1986), Grima and Smith(1993) ጥቂቶቹ ናቸው:: እነዚህ ምሁራን የመምህሩን ትኩረት በተመለከተ ሊጠኑ ከሚገባቸው ጉዳዮች አንፃር የሚከተሉትን ነጥቦች አንስተዋል፡

- ተማሪዎቹ ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ መምህራን ለተማሪዎች፡ የሚሰጡት እድል በሌላ አገላለፅ በመምህሩ ከተጠየቁ ጥያቄዎች የበለጠውን ጥያቄ የተጠየቁት ወንዶች ወይስ ሴቶች (ከፈቃደኛነታቸው አንፃር)
- ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ላልሆኑ ወይም እጃቸውን ላላወጡ ተማሪዎች መምህሩ የሚሰጡት እድል፡-
- ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች ትዕዛዞችን ለማዘዝ የተማሪዎችን ስም በተደጋጋሚ መጥራት
- ተማሪዎቹ ለጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ቢሳሳቱ እንደገና እንዲሞክሩ መምህሩ የሚሰጡት እድል
- ተማሪዎቹ መልስ በሚሰጡበት ጊዜ በሚያደርጉት ንግግር መምህራኑ ጣልቃ በመግባት ንግግራቸውን ማቋረጥ

እነዚህ ከላይ የተገለፁት ነጥቦች መምህራን ለተማሪዎቻቸው የሚሰጡት ትኩረት የሚገመገምባቸው ሲሆን በዚህ ጥናትም ከእነዚህ ነጥቦች አንፃር የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ የሚታየውን ልዩነት ለማመልከት በያንዳንዱ ምድብ የተገኘው ውጤት አማካይ (mean) ተወዳድሯል::

ሰንጠረዥ 13፡- መምህራን እጃቸውን ላወጡ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች ያደረሱት ጥያቄ መጠን የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| | | ለወንዶች የተሰጠ | | | ለሴቶች የተሰጠ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምድብ | የጥያቄዎች ብዛት | ብዛት | አማካይ(mean) | % | ብዛት | አማካይ(mean) | % |
| 1 | 105 | 57 | 3.35 | 54.3 | 48 | 1.65 | 45.7 |
| 2 | 56 | 40 | 1.7 | 71.4 | 16 | 0.73 | 28.6 |
| 3 | 82 | 54 | 1.42 | 65.8 | 28 | 1.64 | 34.2 |
| ጠቅላላ | 243 | 151 | 1.9 | 62.1 | 92 | 1.35 | 37.9 |

* ምድብ አንድ ሴቶች የሚበዙበት

* ምድብ ሁለት ሴቶችና ወንዶች እኩል የሆኑበት

* ምድብ ሶስት ወንዶች የሚበዙበት

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው በሶስቱም ምድቦች ከታደሉት ጥያቄዎች የበለጠውን ያገኙት ወንዶች ሲሆኑ ይህም ከጠቅላላው 243 ጥያቄ 151 ወይም 62.1% ለወንዶች ሲሰጡ ቀሪዎቹ 92ቱ ወይም 37.9% ለሴቶች የተሰጡ ናቸው:: ከዚህም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን በርካታ ጥያቄዎች በማግኘታቸው የመምህሩንም ትኩረት ከሴቶች የበለጠ አግኝተዋል ለማለት ይቻላል:: ሆኖም አማካያቸውን ስናወዳድር የጎላ ልዩነት አይታይም::

በየምድቦች በሚማሩት ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች መካከል ያለውን ልዩነት በግምት ለማሳየት ደግሞ በምድብ አንድና ሁለት የሚማሩ ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ከመምህሩ ያገኙት ጥያቄ መጠን ዝቅተኛ መሆኑን በአማካያቸው መካከል ያለው ልዩነት ያሳያል በምድብ ሶስት የሚማሩት ሴቶች በምድብ አንድና ሁለት ከሚማሩት ሴቶች ጋር ሲነፃፀር የተሻለ የጥያቄ መጠን ያገኙ መሆኑን ውጤቱ ያሳያል:: ሆኖም በየምድቦቹ በወንዶችና በሴቶች መካከል የጎላ ልዩነት አለመኖሩን አማካያቸው ያሳያል::

ሰንጠረዥ 14፡- ለመመለስ ፈቃደኛ ላልሆኑ (እጃቸውን ላላወጡ) ወንዶችና ሴቶች መምህሩ የሰጡትን ጥያቄ መጠን የሚያሳይ

| ምድብ | የጥያቄዎች ብዛት | ለወንዶች የተሰጠ | | | ለሴቶች የተሰጠ | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ብዛት | አማካይ(mean) | % | ብዛት | አማካይ(mean) | % |
| 1 | 12 | 10 | 0.6 | 83.3 | 2 | 0.1 | 16.7 |
| 2 | 11 | 8 | 0.4 | 72.7 | 3 | 0.1 | 27.3 |
| 3 | 17 | 13 | 0.5 | 76.4 | 4 | 0.3 | 23.6 |
| ጠቅላላ | 40 | 31 | 0.5 | 77.5 | 9 | 0.1 | 22.5 |

ከላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ እንደምንመለከተው መምህራኑ እጅ ላላወጡ ወንዶችና ሴቶች ከሚሰጡት ጥያቄ አንፃር የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ በርካታ ጥያቄዎችን አግኝተዋል:: ይህም መምህራኑ እጅ ላላወጡ ወንዶችና ሴቶች ከሰጡት 40 ጥያቄዎች 31 ወይም 77.5% ለወንዶች የተሰጡ ሲሆን ቀሪዎቹ 9 ወይም 22.5% ለሴቶች የተሰጡ ናቸው:: ከዚህ አንፃርም አብዛኛዎቹ ጥያቄዎች ለወንዶች የተሰጡ በመሆኑ ወንዶች የመምህራን ትኩረት ከሴቶች የበለጠ አግኝተዋል:: ሆኖም አስተማማኝ ልዩነት አለመኖሩን አማካያቸው ያሳያል::

ሰንጠረዥ 15:- ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ መምህራኑ ስማቸውን በተደጋጋሚ የጠሯቸው ወንዶችና ሴቶች ብዛት

| | | የወንዶች | | | የሴቶችን | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ምድብ | ድግግሞሽ | ብዛት | አማካይ(mean) | % | ብዛት | አማካይ(mean) | % |
| 1 | 6 | 5 | 0.3 | 80 | 1 | 0.03 | 20 |
| 2 | 3 | 3 | 0.1 | 100 | -- | -- | -- |
| 3 | 12 | 9 | 0.3 | 75 | 3 | 0.2 | 25 |
| ጠቅላላ | 21 | 17 | 0.3 | 82.4 | 4 | 0.1 | 17.6 |

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው በመምህሩ ከተጠሩ ስሞች ማለትም መምህሩ ስማቸውን በተደጋጋሚ ከጠሯቸው ተማሪዎች ወንዶች ከሴቶች የበለጡ ናቸው:: በዚህም በሶስቱም ምድቦች መምህራኑ በተደጋጋሚ በስማቸው ከጠሯቸው 21 ተማሪዎች 17ቱ ወይም 82.4% ወንዶች ሲሆኑ ቀሪዎቹ 4ቱ ወይም 17.6% ሴቶች ናቸው:: በዚህም በሶስቱም ምድቦች መምህራን የወንዶችን ስም በተደጋጋሚ የሚጠሩ ሲሆን ከሴቶች ጋር ያለውን ልዩነት በሚመለከት ግን የጎላ ልዩነት አለመኖሩን አማካያቸው ያሳያል::

የየምድቦችን ውጤት ለየብቻ ስንመለከት ደግሞ በምድብ ሶስት የሚያስተምሩት መምህር የወንዶችንም ሆነ የሴቶችን ስም ከሌሎቹ ምድቦች መምህራን የበለጠ በተደጋጋሚ የጠሩ ሲሆን በተቃራኒው በምድብ ሁለት የሚያስተምሩት መምህር ጥቂት ወንዶችን ብቻ ሲጠሩ የሴቶችን ስም በጭራሽ አልጠሩም::

መምህራኑ ለሚጠይቋቸው ጥያቄዎች ተማሪዎቹ መልስ እንዲሰጡ የአንድ ተማሪን ብቻ ወይም የበርካታ ተማሪዎችን ስም በተደጋጋሚ ይጠራሉ:: ከላይ የቀረበው ሰንጠረዥም የሚያሳየው ይህንኑ ነው:: መምህራኑ የተማሪዎችን ስም ከመጥራት አንፃር በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል የሚታየው ልዩነት በተማሪዎቹ ጾታ ተዕለና ብቻ የተወሰነ አይደለም::

ግለትም ከዚህ ሁኔታ ማስተዋል ያለብን ጉዳይ መምህራኑ የወንዶችን ስም ከሴቶች የበለጠ በተደጋጋሚ ጠርተዋል የሚለውን ብቻ ሳይሆን ስማቸው በተደጋጋሚ የተጠራው ተማሪዎች አንድ ወይም ሁለት ብቻ ሊሆኑ እንደሚችሉም መገንዘብ ያስፈልጋል:: ይህም በመምህሩ ግላዊ ልዩነት (Individual difference) ሊሆን ይችላል:: ምክንያቱም መምህሩ አንድን ተማሪ በደንብ የሚያውቀውና የሚግባቡት ከሆነ ለጥያቄም መልስ እንዲሰጥ የዛን ተማሪ ስም በተደጋጋሚ ሊጠሩ ይችላሉ:: ከዚህ አንፃር መምህሩ ለወንዶች የበለጠ ትኩረት ሰጥተዋል ለማለት አይቻልም:: የአንድን ተማሪ ስም በተደጋጋሚ ቢጠሩም በተቃራኒው በጭራሽ ስማቸው ያልተጠሩ ወንዶች ስለሚኖሩ ወንዶች በአጠቃላይ በመምህሩ ስማቸው በተደጋጋሚ ተጠርቷልና የመምህሩን ትኩረት የበለጠ አግኝተዋል ለማለት አያስደፍርም::

ከላይ እንደተገለፀው የወንዶችና የሴቶችን ስም በተደጋጋሚ ከመጥራት አንፃር መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡት ትኩረት የተለያየ ሊሆን የቻለው በመምህሩ ግላዊ ልዩነት ሊሆን ከዚህም ሌላ በተማሪዎች ችሎታ መለያየት የተነሳም ሊሆን እንደሚችል ለመገመት ይቻላል:: ምክንያቱም መምህራኑ ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት ከሴቶች የበለጠ ሆኖ መገኘቱ በተማሪዎች ጾታ መለያየት የተነሳ ብቻ ሳይሆን ጎበዝና ንቁ ተሳትፎ ያላቸው ተማሪዎችም የመምህሩን ትኩረት የበለጠ የሚያገኙ በመሆኑም ይሆናል:: በዚህም John and Glendinning (1996) የመምህሩ ትኩረት ከተማሪዎች ጾታ ጋር ብቻ ሳይሆን ከችሎታቸው መለያየት ጋርም ግንኙነት ያለው መሆኑን ገልፀዋል:: ስለዚህ በዚህ ጥናትም ከላይ እንደተገለፀው መምህሩ የተማሪዎችን ስም በተደጋጋሚ ከመጥራት አኳያ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡት ትኩረት የተለያየ ሊሆን የቻለው ከተማሪዎቹ ጾታ መለያየት በተጨማሪም ተማሪዎቹ በችሎታ የተለያዩ በመሆናቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል::

መምህሩን ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ በሶስቱ ምድቦች በሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች መካከል የሚታየውን ልዩነት በተመለከተ ደግሞ የመምህሩን ትኩረት በሚመለከት ከተገኙት ነጥቦች አንፃር በምድብ አንድና ሶስት የሚማሩ ሴቶች በምድብ ሁለት ከሚማሩት ሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረት ማግኘታቸውን ከውጤቱ ለመረዳት ይቻላል::

በሶስቱም ምድቦች የሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች ከመምህሩ የሚያገኙት ትኩረት የተለያየ የሆነበት ምክንያት በየምድቦቹ የሴቶች ተማሪዎች ቁጥር መብዛትና ማነስ ምክንያት ሳይሆን በመምህሩ የማስተማር ዘዴና ግላዊ ልዩነት ሊሆን ይችላል:: ይህም ለምሳሌ:- መምህራኑ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆኑ (እጃቸውን ያላወጡ) ተማሪዎችን ከመጠየቅ አንፃር የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ በምድብ ሶስት የሚያስተምሩት መምህር ከሌሎቹ የበለጠ ውጤት አስመዝግበዋል:: እንዲሁም የተማሪዎችን ስም ከመጥራት አንፃርም በምድብ ሶስት የሚያስተምሩት መምህር የወንዶችንም ሆነ የሴቶችን ስም በተደጋጋሚ እንደሚጠሩ

ለመረዳት ተችሏል። ስለዚህ መምህራኑ ባላቸው የማስተማር ስልት መለያየት ምክንያት በየምድቦቹ የሚገኙ ሴቶች ተማሪዎች የመምህሩን ትኩረት በተለያየ ሁኔታ አግኝተዋል።

#### 4.3.1.2. የመምህራኑን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ከቪዲዮ ምዝግቡ የተገኘ መረጃ ውጤት

ከላይ የቀረበው መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ትኩረት በሚመለከት ከተለያዩ ምሁራን ከተወሰዱት ነጥቦች አንፃር ከቪዲዮ ምዝግቡ የተገኘው መረጃ ውጤት ነው። በመቀጠል ደግሞ መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በሚመለከት በመስኩ ምርምር ያካሄዱ ምሁራን ከሚያነሷቸው ጉዳዮች አንፃር ከቪዲዮ ምዝግቡ የተገኘውን መረጃ ውጤት ለማቅረብ ተሞክሯል።

መምህራን ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ለሚያደርጉት ተሳትፎ የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ Irvin (1986), Potter(1978), Grima and Smith [illegible] ሊነሱ የሚገባቸውን ጉዳዮች እንደሚከተለው ገልፀዋል፤

1. <u>አዎንታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ</u> (Positive verbal- feedback):-በዚህ ስር የሚነሱ የመምህሩ ምላሾች ተማሪዎች ለተጠየቁት ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ሲሰጡ፡- መምህሩ ትክክለኛነታቸውን ለማረጋገጥ የሚጠቀምባቸውን ለምሳሌ አዎ፣ ትክክል፣ እሺ፣ እና ማሞገስን ለምሳሌ፦ በጣም ጥሩ፣ ጎበዝ፣ ጥሩ፣ ወዘተ. የሚሉት ናቸው።

2. <u>አሉታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ</u> (Negative verbal-feedback):- ተማሪዎቹ ለጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ሳይሰጡ ሲቀሩ ወይም ሲሳሳቱ መምህሩ የሚያስከትሉትን ትችት ወይም ገሳጼ (Criticism and reprimands) የሚይዝ ሲሆን ለምሳሌ ትክክል አይደለም! ተሳስተሃል፣ ከዚህ የተሻለ አትሞክርም/ሪም? ወዘተ. የሚሉትን የሚይዝ ነው።

3. <u>አዎንታዊ አሉታዊም ያልሆነ (Neutral) የመምህሩ፣ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ</u>:- ይህ መምህሩ የተማሪው መልስ በከፊል የተሳሳተ ወይም ማሻሻያ የሚያስፈልገው ሲሆን ለማሻሻል ወይም ለማሟላት የተማሪውን መልስ ሲደግሙ የሚመዘገብ የመምህሩ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ነው።

የመምህሩን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በሚመለከት የሚነሱ ጉዳዮች ከላይ የተጠቀሱት ብቻ ሳይሆን ሌሎችም አሉ። ለምሳሌ አካዳሚክና አካዳሚክ ያልሆነ ምጋቤ ምላሽ በማለት በሁለት ከፍለው የሚያቀርቡ ምሁራን አሉ። አካዳሚክ የሚባለው ከትምህርቱ ጋር ተያይዞ መምህሩ ለተማሪዎች የሚሰጡት ምላሽ ሲሆን አካዳሚክ ያልሆነው ደግሞ ከትምህርት ጋር የተያያዙ

ሳይሆን ከትምህርት ውጭ በሆኑ ጉዳዮች ለተማሪዎች የክፍል ውስጥ ባህርይ የሚሰጥ ምላሽ ነው። በዚህ ጥናት ከላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች በመውሰድ መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ በሶስቱም ምድቦች የተገኘው ውጤት እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 16፦ በምድብ አንድ (ሴቶች በሚበዙበት) የመምህሩን አዎንታዊ፣ አሉታዊና መካከለኛ (Neutral) ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘ መረጃ ውጤት

| | | ለወንዶች የተሰጠ | | | ለሴቶች የተሰጠ | | | ቲ-ስሌት | ጉልህ ልዩነት |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| [illegible] | ጠቅላላ | ብዛት | አማካይ (mean) | % | ብዛት | አማካይ (mean) | % | | |
| የመምህሩ አዎንታዊ ምጋቤ ምላሽ | 30 | 18 | 1.1 | 60 | 12 | 0.4 | 40 | 1.13 | የለውም |
| የመምህሩ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ | 15 | 9 | 0.5 | 60 | 6 | 0.2 | 40 | 6.8 | |
| መካከለኛ (neutral) ምጋቤ ምላሽ | 64 | 32 | 1.9 | 50 | 32 | 1.1 | 50 | 0.97 | |
| ጠቅላላ | 105 | 54 | 3.2 | 51.4 | 51 | 1.8 | 48.6 | 0.4 | |

ከዚህ ሰንጠረዥ ለመመልከት እንደሚቻለው የመምህሩን አዎንታዊ፣ አሉታዊና መካከለኛ(Neutral) ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ያገኙ መሆኑን ውጤቱ ቢያሳይም ልዩነቱ አስተማማኝ አለመሆኑን የተገኘው የቲ-ስሌት ዋጋ ያሳያል።

ሰንጠረዥ 17፦ የመምህሩን አዎንታዊ፥ አሉታዊና መካከለኛ (Neutral) ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ በምድብ ሁለት (ወንዶችና ሴቶች እኩል በሆኑበት) የተገኘ መረጃ ውጤት

| | | ለወንዶች የተሰጠ | | | ለሴቶች የተሰጠ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| [illegible] | ጠቅላላ ብዛት | ብዛት | አማካይ (mean) | % | ብዛት | አማካይ (mean) | % | ቲ-ስሌት | ጉልህ ልዩነት |
| የመምህሩ አዎንታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ | 16 | 14 | 0.6 | 87.5 | 2 | 0.1 | 12.5 | 1.4 | የለውም |
| የመምህሩ አሉታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ | 8 | 5 | 0.2 | 62.5 | 3 | 0.14 | 37.5 | 0.3 | |
| መካከለኛ (neutral) ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ | 11 | 9 | 0.4 | 81.8 | 2 | 0.1 | 18.2 | 1.0 | |
| ጠቅላላ | 35 | 28 | 1.3 | 80 | 7 | 0.3 | 20 | 1.66 | |

ከላይ ለማሳየት የተሞከረው የመምህሩ አዎንታዊ፥ አሉታዊና መካከለኛ (Neutral) ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ወንዶችና ሴቶች እኩል በሆኑበት ምድብ የሚታየውን ልዩነት ሲሆን ከተገኙት ውጤቶች አንፃርም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ያገኙ መሆኑን ውጤቱ ቢያሳይም ልዩነቱ አስተማማኝ ወይም ጉልህ አለመሆኑን የተገኘው የቲ-ስሌት ዋጋ ያሳያል።

ሰንጠረዥ 18፦ የመምህሩን አዎንታዊ፥ አሉታዊና መካከለኛ (Neutral) ቀላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ከምድብ ሶስት (ወንዶች በሚበዙበት) የተገኘ መረጃ ውጤት

| | | ለወንዶች የተሰጠ | | | ለሴቶች የተሰጠ | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| [illegible] | ጠቅላላ ብዛት | ብዛት | አማካይ (mean) | % | ብዛት | አማካይ (mean) | % | ቲ-ስሌት | ጉልህ ልዩነት |
| የመምህሩ አዎንታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ | 19 | 15 | 6.4 | 78.9 | 4 | 0.2 | 21.1 | 0.50 | የለውም |
| የመምህሩ አሉታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ | 5 | 4 | 0.1 | 80 | 1 | 0.1 | 20 | 0.30 | |
| መካከለኛ (neutral) ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ | 41 | 30 | 0.8 | 73.2 | 11 | 0.7 | 26.8 | 0.30 | |
| ጠቅላላ | 65 | 49 | 1.3 | 75.4 | 16 | 0.9 | 24.6 | 0.40 | |

መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ከተነሱት ነጥቦች አንፃር ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ምላሽ ያገኙ መሆኑን ከሰንጠረዡ ለመመልከት ቢቻልም የሚታየው ልዩነት ግን ጉልህ ወይም አስተማማኝ አለመሆኑን ከተገኘው የቲ ስሌት ዋጋ መረዳት ይቻላል፡፡ ስለዚህ በወንዶችና በሴቶች አማካይ (Mean) መካከል የሚታየው ልዩነት አስተማማኝ ባይሆንም ውጤቱ በመቶኛ ሲሰላ ግን ወንዶች በጠቅላላ ከመምህሩ ከተመለሱ ቃላዊ ምላሾች 75.4% የወሰዱ ሲሆን ቀሪዎቹ 24.6% ብቻ ለሴቶች የደረሱ ናቸው፡፡ ይህም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሊያስመዘግቡ የቻሉት ከዚህ አንፃር ሊሆን ይችላል፡፡ዝርዝሩን በሚቀጥለው ክፍል ለመመልከት ይቻላል፡፡

### 4.3.2. መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት

ቀደም ብሎ እንደተገለፀው የዚህ ጥናት ዋና አላማ የሴት ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መመርመር ሲሆን ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡት ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ይለያያልን? የሚለውንም ጥናቱ ይዳስሳል፡፡ ምክንያቱም በሴቶች ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርጉ ነገሮች አንዱ የመምህራን እኩል ያልሆነ አያያዝ (Unfair treatment) ወይም ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ ነው በማለት የተናገሩ ተቸውን ውጤት ያቀረቡ ምሁራን የገለፁትን መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ ይህን በሚመለከት ከላይ የቀረበው ከቪዲዮ ምዝግቡ የተገኘው መረጃ ውጤት ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ ከዚሁ ጋር በተያያዘ መልኩ ለተማሪዎች ከቀረቡት ጥያቄዎች የተገኘው መረጃ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡ በፅሁፍ መጠይቁ ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች መምህራን የበለጠ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡት ለወንዶች? ወይስ ለሴቶች? በሚለው ይዘት ዙሪያ የተከሩ ናቸው፡፡

### 4.3.2.1. የመምህራኑን ትኩረት በተመለከተ ከተማሪዎች መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

ሰንጠረዥ 19፡- መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ትኩረት በሚመለከት በምድብ አንድ ከሚማሩ ተማሪዎች የተገኘ ውጤት

| ተ.ቁ | ጥያቄ | 5 | | | | 4 | | | | 3 | | | | 2 | | | | 1 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | [illegible] | 8 | 47 | 7 | 24 | 4 | 23.5 | 10 | 34.5 | 2 | 11.8 | 3 | 10.3 | 3 | 17.6 | 8 | 27.6 | - | - | 1 | 3.5 |
| 2 | [illegible] | 10 | 58.8 | 9 | 31 | 5 | 29.4 | 10 | 34.5 | 2 | 11.8 | 4 | 13.8 | | - | 3 | 10.3 | - | - | 3 | 10.3 |
| 3 | [illegible] | 7 | 41.2 | 11 | 37.9 | 6 | 35.3 | 8 | 27.6 | 2 | 11.8 | [illegible] | [illegible] | 1 | 5.9 | 4 | 13.8 | 1 | 5.9 | 3 | 10.3 |
| 4 | [illegible] | 7 | 41.2 | [illegible] | [illegible] | 7 | 41.2 | 8 | 27.6 | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | 4 | [illegible] | - | - | 1 | [illegible] |
| 5 | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | 41.2 | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | [illegible] | | | 4 | 13.8 |

* በእማራጭነት የቀረቡት ቁጥሮች የሊከርት ደረጃ መለኪያ የሚወክሉ ናቸው:: እነዚህም 5 ="በጣም ከፍተኛ"፣ 4 ="ከፍተኛ"፣ 3 ="መካከለኛ"፣ 2 ="ዝቅተኛ"፣ 1="በጣም ዝቅተኛ" የሚሉትን ይወክላሉ::

ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ እንደተመለከተው ለተማሪዎች የቀረቡት ጥያቄዎች ይዘት መምህሩን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት የሚመለከት ነው:: በዚህም ለቀረቡት አምስት ጥያቄዎች ከሰጧቸው መልሶች ወንዶች ከሴቶች የተሻለ የመምህሩን ትኩረት የሚያገኙ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል::

በተራ ቁጥር አንድ "ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሽን ስታወጣ/ጪ መልስ እንድትሰጥ/ጪ መምህሩ የሚሰጡህ/ሽ እድል" በሚል ለቀረበው ጥያቄ ከመላሾቹ 12 ወይም [illegible] ወንዶችና 17 ወይም 59% ሴቶች "በጣም ከፍተኛ" እና "ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል:: ከዚህ አንፃር ወንዶች ከሴቶች የተሻለ እድል የሚያገኙ መሆኑን ለመመልከት ይቻላል:: ይህም ተናም በሉ ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘው ውጤት ጋር የሚጣጣም ሆኖአል::

"ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሽን ብታወጣ/ጪም ባታወጣም/ጪም እንድትመልስ/ሽ የሚሰጡህ/ሽ እድል" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ 15 ወይም 88.2% ወንዶችና 19 ወይም 65.5% ሴቶች "ከፍተኛ" እና "በጣም ከፍተኛ" በማለት መልስ ሰጥተዋል:: በዚህም ወንዶች ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጃቸውን ቢያወጡም ባያወጡም እንዲመልሱ የሚሰጣቸው እድል ከሴቶች የበለጠ ነው:: "የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ መልስ በምትሰጥ/ጪበት ጊዜ ብተሳሳት/ቺ እንደገና እንድትሞክር/ሪ የሚሰጡህ/ሽ እድል" በሚል ለቀረበ ጥያቄም ከመላሾቹ 13 ወይም 76.5% ወንዶችና 18 ወይም 51.7% ሴቶች" በጣም ከፍተኛ" እና "ከፍተኛ" በማለት መልስ ሰጥተዋል:: በመቀጠልም "የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች ትዕዛዞችን ለማዘዝ ሲፈልጉ ስምህ/ሽን በተደጋጋሚ የመጥራት ልምዳቸው" በሚል ለቀረበ ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 14 ወይም 82.4% ወንዶችና 17 ወይም [illegible] ሴቶች "ከፍተኛ" ና "በጣም ከፍተኛ" በማለት ሲመልሱ ይህንኑ በሚመለከት ከዚህ ለየት ባለ አቀራረብ ለቀረበ ጥያቄም የሰጡት ምላሽ ይህንኑ የሚያጠናክር ነው::

ይህም "የአማርኛ ቋንቋ መምህሩ በሚያስተምሩበት ወቅት በአብዛኛው ስም የሚጠሩት የወንዶችን ነው ወይንስ የሴቶችን?" በሚል ለቀረበ ጥያቄ ከመላሾቹ 68.2% ወንዶችና 34.5% ሴቶች የወንዶችን ስም በተደጋጋሚ የሚጠሩ መሆኑን ገልፀዋል:: ይህም ከላይ ከተገለፀው ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ሆኖአል::

በመጨረሻም "የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ሀሳብህ/ሽን ለጓደኞችህ/ሽ እንድትገልጽ/ጪ የሚያደርጉልህ/ሽ ማበረታቻ" በሚል ለቀረበ ጥያቄ 13 ወይም 70.5% ወንዶችና 15 ወይም 51.7% ሴቶች "በጣም ከፍተኛ"ና "ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል:: ከዚህ ውጤትም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ሀሳባቸውን በጓደኞቻቸው ፊት እንዲገልጹ በመምህሩ የሚበረታቱ መሆናቸውን

ለመረዳት ይቻላል:: ሆኖም ሴቶችም የተሻለ መበረታታት እንደሚያገኙ ከሰጡት አዎንታዊ ምላሽ ለመመልከት ይቻላል::

በአጠቃላይ ከላይ በሰንጠረዡ እንደታየው ወንዶች ተማሪዎች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረት ያገኛሉ:: ይህንን ውጤት የሚያጠናክር ከመምህራን መጠይቅ የተገኘ መረጃ ደግሞ "በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ብዙ እድል የሚያገኙት" በሚል ለቀረበ ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 6 መምህራን አራቱ "ወንዶች" በማለት ሲመልሱ ቀሪዎቹ ሁለቱ "ሴቶች" ብለዋል:: ከዚህ ውጤትም ወንዶች ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ከሴቶች የበለጠ እድል ስለሚያገኙ የመምህሩን ትኩረት ከሴቶች የበለጠ ያገኛሉ ለማለት ይቻላል:: ለዚህም አብዛኞቹ መምህራን የሰጧቸው ምክንያቶች:-

- በሴቶች ተማሪዎች ላይ የባህል ተፅዕኖ ስላለ ጥያቄ ለመመለስ እጅ አያወጡም በዚህም ለመመለስ እድል አያገኙም፤
- ወንዶች ደፋሮችና የማይጨነቁ በመሆናቸው ብዙ ጊዜ ጥያቄ ለመመለስ እጃቸውን በተደጋጋሚ የሚያወጡት ወንዶቹ በመሆናቸው
- ሴቶች ጥያቄ ለመመለስም ሆነ ለመጠየቅ ፍላጎት ስለሌላቸው የሚሉት ዋና ዋናዎቹ ናቸው::

ተማሪዎችም በክፍት ጥያቄ አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ተጠይቀው አብዛኞዎቹ ተማሪዎች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እድል የሚያገኙበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስፍረዋል:-

መምህራን ሴቶች ተሳትፎ አያደርጉም፣ በችሎታም ከወንዶች ያንሳሉ ብለው ስለሚያምኑና ለሴቶች ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ በተደጋጋሚ ስለማይጠይቋቸው

ሴቶች ስለሚፈሩ

መምህራኑ ሴቶችን አዘውትሮ መጠየቅን እንደጎጅ ባህል ስለሚቆጥሩት ማለትም ሲደን በተደጋጋሚ መምህሩ ጥያቄ ከጠየቀ የተማሪው አመለካከት ስለሚቀየር ብዙውን ዕድል ለወንዶች ስለሚሰጡ የሚሉት በዋናነት የተጠቀሱ ናቸው::

ስለዚህ በመምህራኑም ሆነ በተማሪዎች በተሰጡት አስተያየቶች ሴቶች ተማሪዎች ስለሚፈሩና ለመናገር ፈቃደኛ ስለማይሆኑ መምህራኑም ለሴቶች ተሳትፎ ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑና በባህል ተፅዕኖም ምክንያት ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ከወንዶች እኩል እድል የማያገኙ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል::

ከላይ በመምህራኑና በተማሪዎች በተሰጡት አስተያየቶች ሴቶች ከመምህሮቻቸው ጋር ያላቸው ቅርበት በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: ይህን በሚመለከትም ለተማሪዎች በቀረበ መጠይቅ "በመማር ማስተማሩ ሂደት ከአማርኛ ቋንቋ መምህርህን/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ቅርበት" በሚል ለቀረበው ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 17 ወንዶች 14ቱ ወይም 82.4% ወንዶች

ከፍተኛ" እና "በጣም ከፍተኛ" በማለት ሲመልሱ በተቃራኒው መጠይቁን ከሞሉት 24 ሴቶች 11 ወይም 37.9% ብቻ በጣም ከፍተኛና ከፍተኛ ሲሉ ቀሪዎቹ ዝቅተኛና በጣም ዝቅተኛ በማለት መልሰዋል:: ከዚህ አንፃርም ሴቶች ከመምህሮቻቸው ጋር ያላቸው ቅርበት ከወንዶች ያነሰ ከመሆኑም በተጨማሪ ዝቅተኛ በመሆኑ ከመምህሮቻቸው የሚያገኙት ትኩረትም በዚህ ምክንያት ዝቅተኛ ሊሆን እንደቻለ መገመት ይቻላል::

የተማሪዎችን ስም ከመጥራት አንፃርም መምህራኑ ለሴቶችና ለወንዶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ለተማሪዎች ቀደም ብሎ በሰንጠረዡ ከቀረበው ጥያቄ በተለየ መልኩ ቀርቦላቸው የሰጡት ምላሽ ከላይ ከተገለፀው ጋር የሚጣጣም ነው:: ይህም "የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች ትዕዛዞችን ለማዘዝ ሲፈልጉ በተደጋጋሚ ስም የሚጠሩት የወንዶችን ወይስ የሴቶችን?" በሚል የቀረበ ሲሆን ከመላሾቹም 33ቱ ወይም 71.7% የወንዶችን በማለት ሲመልሱ ቀሪዎቹ 13ቱ ወይም 28.2% የሴቶችን በማለት መልሰዋል:: ለዚህም ከሰጧቸው ምክንያቶች በአብዛኛዎቹ መላሾች የተጠቀሱት ከላይ ከተዘረዘሩት ጋር የሚቀራረቡ ሲሆን መምህራኑ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ችሎታ አላቸው ብለው ስለሚገምቱ፣ ለሴቶች ተማሪዎች ያላቸው አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑና መምህራኑ የሴቶችን ስም በተደጋጋሚ ከጠሩ የተማሪዎች አመለካከት ይቀየራል በሚል ስለሚፈሩ የሚሉት ዋናዋናዎቹ ናቸው:: በእነዚህ ምክንያቶች መምህራኑ የተማሪዎችን ስም ከመጥራት አንፃር ለሴት ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት ያነሰ ነው:: ከቪዲዮ ምዝገባ የተገኘው መረጃም ይህንኑ የሚያጠናክር ነው

ሰንጠረዥ 20፡- መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ በምድብ ሁለት ከሚማሩ ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተቁ | ጥያቄ | 5 | | | | 4 | | | | 3 | | | | 2 | | | | 1 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሽን ስታወጣ/ጪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ እንድትመልስ/ሺ የሚሰጥህ/ሽ እድል | 9 | 40.9 | 5 | 22.7 | 8 | 36.4 | 3 | 13.6 | 3 | 13.6 | 6 | 27.3 | 2 | 9.1 | 6 | 27.3 | - | - | 2 | 9 |
| 2 | ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሽን ብታወጣ/ጪም ባታወጣም/ጪም የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ እንድትመልስ/ሺ የሚሰጥህ/ሽ እድል | 12 | 54.5 | 4 | 18.2 | 7 | 31.8 | 3 | 13.6 | 1 | 4.5 | 5 | 22.7 | 2 | 9.1 | 6 | 27.3 | - | - | 4 | 1 |
| 3 | መልስ በምትሰጥ/ጪ ጊዜ ብትሳሳት/ቺ እንደገና እንድትሞክር/ሪ መምህሩ የሚሰጥህ/ሽ ዕድል | 8 | 36.4 | 7 | 31.8 | 6 | 27.3 | 3 | 13.6 | 6 | 27.3 | 5 | 22.7 | - | - | 4 | 18.2 | 2 | 9.1 | 3 | 1 |
| 4 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ጥያቄ ለመጠየቅ ሲፈልጉ ስምህ/ሽን በየቢጋኑም የመጥራት ልመዳቸው | 7 | 31.8 | 3 | 13.6 | 5 | 22.7 | 4 | 18.2 | 6 | 27.3 | 3 | 13.6 | 3 | 13.6 | 7 | 31.8 | 1 | 4.5 | 5 | 2 |
| 5 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ሀሳብህ/ሽ ለሌሎች እንድትገልጽ/ጪ የሚያደርጉበት ሚዛን | 6 | 27.3 | 7 | 31.8 | 9 | 40.9 | 6 | 27.3 | 4 | 18.2 | 5 | 22.7 | 2 | 9.1 | 3 | 13.6 | 1 | 4.5 | 1 | 4 |

* በአማራጭነት የቀረቡት ቁጥሮች የ 'ሊከርት' ደረጃ መለኪያ የሚወክሉ ናቸው እነዚህም 5= "በጣም ከፍተኛ"፣ 4="ከፍተኛ" 3= "መካከለኛ" 2= "ዝቅተኛ" 1 ="በጣም ዝቅተኛ" የሚሉትን ይወክላሉ::

ከላይ በሰንጠረዡ ለማሳየት የተሞከረው መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ለቀረቡት ጥያቄዎች ተማሪዎቹ የሰጧቸውን መልሶች ሲሆን በዚህም ወንዶች ከሴቶች የተሻለ የመምህራን ትኩረት የሚያገኙ መሆኑን መልሶቻቸው ያሳያሉ::

"በተራ ቁጥር አንድ ላይ" ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሽን ስታወጣ/ጪ መምህሩ እንድትመልስ/ሽ የሚሰጡህ/ሽ እድል" በሚል ለቀረበው ጥያቄ 77.3% ወንዶችና [illegible] ሴቶች "ከፍተኛ" እና "በጣም ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል:: እንዲሁም ቁጥራቸው የማይናቅ ሴቶች "ዝቅተኛ" ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት መልሰዋል:: እነዚህም 36.3% ሲሆኑ ወንዶች 9.1% ብቻ አሉታዊ መልስ ሰጥተዋል:: በዚህም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ለጥያቄዎች መልስ የመስጠት ዕድል ያገኛሉ ለማለት ይቻላል:: ይህም ከቪዲዮ ምዝግቡ ውጤት ጋር የሚጣጣም ነው::

በመቀጠልም "ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሺን ብታወጣ/ጪም ባታወጣ/ጪም መምህሩ የሚሰጡህ/ሽ እድል በሚል ለቀረበው ጥያቄ 86.4% ወንዶችና 31.8% ብቻ ሴቶች "ከፍተኛ" ና "በጣም ከፍተኛ" ሲሉ 45.5% ሴቶች በተቃራኒው "ዝቅተኛ"ና "በጣም ዝቀተኛ" በማለት መልሰዋል:: ከዚህ አንፃርም መምህሩ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጃቸውን ቢያወጡም ባያወጡም ለወንዶች የሚሰጡት ዕድል የተሻለ መሆኑን ከውጤቱ ለመመልከት ይቻላል:: ይህም ከቪዲዮ ምዝገቡ እንደታየው መምህራን እጅ ላላወጡ ወይም ፈቃደኛ ላልሆኑ ሴቶች ከሚሰጡት ዕድል ዝቅተኛ መሆን ጋር የሚዛመድ ነው::

"የአማርኛ ቋንቋ መምህር/ሽ መልስ በምትሰጥ/ጪበት ጊዜ ብትሳሳት/ቺ እንደገና እንድትሞክር/ሪ የሚሰጡህ/ሽ ዕድል" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄም 63.6% ወንዶችና 45.5% ሴቶች "ከፍተኛ" "በጣም ከፍተኛ" በማለት ሲመልሱ 31.8% ሴቶች ደግሞ "ዝቅተኛ" ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት መልሰዋል:: በዚህም ለጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ ቢሳሳቱ እንደገና እንዲሞክሩ ዕድል የሚያገኙት በአብዛኛው ወንዶቹ መሆናቸውን መመልከት ይቻላል፡ የመጨረሻውም ከላይ ለተገለፀው ጥያቄ ወንዶች የሰጡት አዎንታዊ መልስ ከሴቶች የበለጠ መሆኑን ነው:: መምህሩን የተማሪዎችን ስም ከመጥራት አንፃር ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ለቀረበ ጥያቄ 54.5% ወንዶችና 31.8% ሴቶች "ከፍተኛ" እና "በጣም ከፍተኛ" በማለት ሲመልሱ 54.5% ሴቶችና 18.2% ወንዶች በተቃራኒው "ዝቅተኛ" እና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት መልሰዋል:: ከዚህም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩ ትኩረት የሚያገኙ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡

በመጨረሻም ‘የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ሀሳብህ/ሽን እንድትገልፅ/ጪ የሚያደርጉልህ/ሽ ማበረታቻ’ በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ 68.2% ወንዶችና 40.9% ሴቶች “ከፍተኛ” እና “በጣም ከፍተኛ” በማለት ሲመልሱ በተቃራኒው 27.3% ሴቶችና 12.5% ብቻ ወንዶች “ዝቅተኛ” እና “በጣም ዝቅተኛ” በማለት መልስ ሰጥተዋል:: በዚህም ተማሪዎቹ በሰጧቸው ምላሾች ወንዶች ከሴቶች የተሻለ የመምህሩን ማበረታቻ አግኝተዋል ለማለት ይቻላል::

በአጠቃላይ ከላይ በሰንጠረዡ ለማሳየት እንደተሞከረውና በምድብ አንድ እንደተመለከትነው በዚህ ምድብም የሚማሩ ወንዶች ተማሪዎች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረት የሚያገኙ መሆናቸውን ለሁሉም ጥያቄዎች የሰጧቸው መልሶች ያሳያሉ::

ሰንጠረዥ 21 መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ከምድብ ሶስት ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፡

| ተ.ቁ | ጉዳይ | 5 | | | | 4 | | | | 3 | | | | 2 | | | | 1 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | ለወንዶቹም መልስ ለመስጠት እጃቸውን ሲያወጡ የሴቶችም ቅንዓ መምህሩ/ሯ እንድትመልሱ የሚሰጠው/ሽ እድል | 12 | 31.6 | 5 | 29.4 | 13 | 34.2 | 3 | 17.6 | 9 | 23.7 | 6 | 35.3 | 3 | 7.9 | 2 | 11.8 | 1 | 2.6 | 1 | 5.9 |
| 2 | ለወንዶቹም መልስ ለመስጠት እጃቸውን ሲያወጡም እንድትመልሱ መምህሩ የሚሰጠው/ሽ እድል | 15 | 39.5 | 4 | 23.5 | 9 | 23.7 | 6 | 35.3 | 6 | 15.8 | 4 | 23.5 | 5 | 13.2 | 2 | 11.8 | 3 | 7.9 | 1 | 5.9 |
| 3 | መልስ በምትሰጥበት ጊዜ በተሳሳትክ/ሽ እንደገና እንድትሞክር/ሪ መምህሩ የሚሰጠው/ሽ እድል | 13 | 34.2 | 8 | 47 | 14 | 36.8 | 4 | 23.5 | 5 | 13.2 | 3 | 17.6 | 4 | 10.5 | 2 | 11.8 | 2 | 5.3 | - | - |
| 4 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች ትዕዛዞችን ለማዘዝ ሲፈልጉ ስምህን/ሽን የመጥራት ልምዳቸው | 21 | 55.3 | 5 | 29.4 | 11 | 28.9 | 8 | 47 | 3 | 7.9 | 2 | 11.8 | - | - | 1 | 5.9 | 3 | 7.9 | 1 | 5.9 |
| 5 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ሀሳብህን/ሽን ለጓደኞችህ/ሽ እንድትገልፅ/ጪ የሚሰጡህ/ሽ ማበረታቻ | 19 | 50 | 4 | 23.5 | 10 | 26.3 | 3 | 17.6 | 3 | 7.9 | 5 | 29.4 | 4 | 10.5 | 4 | 23.5 | 2 | 5.3 | 1 | 5.9 |

ከላይ ከሰንጠረዡ እንደምንመለከተው መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ትኩረት በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች ወንዶችና ሴቶች በሰጧቸው መልሶች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረት የሚወስዱ መሆናቸውን አመልክተዋል።

በተራ ቁጥር አንድ "ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሽን ስታወጣ/ጪ መምህርህ/ሽ እንድትመልስ የሚሰጥህ/ሽ ዕድል" በሚል ለቀረበ ጥያቄ ከመላሾቹ 65.8% ወንዶችና 47.1% ሴቶች "በጣም ከፍተኛ" ና "ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል። እንዲሁም "ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህን/ሽን ብታወጣ/ጪ ባታወጣ/ጪም መልስ እንድትሰጥ/ጪ መምህሩ የሚሰጥህ/ሽ እድል" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ደግሞ 88.2% ወንዶችና 65.5% ሴቶች "ከፍተኛ" ና "በጣም ከፍተኛ" ብለዋል። ለእነዚህ ለሁለቱ ጥያቄዎች ከሰጧቸው አዎንታዊ መልሶች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረት የሚያገኙ መሆኑንና ሴቶችም ቀደም ብለው ከቀረቡት ምድቦች ሴቶች ተማሪዎች ይበልጥ የመምህሩን ትኩረት የሚያገኙ መሆናቸውን መረዳት ይቻላል።

በተጨማሪም "የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ መልስ ስትሰጥ/ጪ ብትሳሳት/ቺ እንደገና እንድትሞክር/ሪ የሚሰጥህ/ሽ ዕድል" በሚል ለቀረበ ጥያቄም 76.5% ወንዶችና 51.7% ሴቶች "በጣም ከፍተኛ" ና "ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል። "የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች ትዕዛዞችን ለማዘዝ ሲፈልጉ ስምህ/ሽን በተደጋጋሚ የመጥራት ልምዳቸው" በሚል ለቀረበ ጥያቄ 82.4% ወንዶችና 58.6% ሴቶች "ከፍተኛ" ና "በጣም ከፍተኛ" በማለት መልሰዋል። ከዚህም ከሰጧቸው አዎንታዊ መልሶች ወንዶች ከሴቶች የተሻለ የመምህሩን ትኩረት የሚያገኙ መሆኑንና ሴቶችም ከላይ ከቀረቡት ነጥቦች አንፃር የሚያገኙት ትኩረት አነስተኛ አለመሆኑን ለመገንዘብ ተችሏል።

የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ሀሳብህ/ሽን ለጓደኞችህ/ሽ እንድትገልፅ/ጪ የሚያደርግልህ/ሽ ማበረታቻ" በሚል ለቀረበ ጥያቄ 70.5% ወንዶችና 51.7% ሴቶች "በጣም ከፍተኛ" ና "ከፍተኛ" በማለት መልስ ሰጥተዋል። ከዚህ ውጤትም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ሀሳባቸውን ለጓደኞቻቸው እንዲገልፁ የሚበረታቱ ሲሆን ሴቶችም የሚያገኙት ማበረታቻ አነስተኛ አይደለም። ስለዚህ በምድብ ሰስት የሚገኙ ተማሪዎች ለሁሉም ጥያቄዎች ከሰጧቸው አዎንታዊ ምላሾች የመምህሩን ትኩረት በሚመለከት ወንዶች ከሴቶች የበለጡ ቢሆንም ሴቶችም የተሻለ ትኩረት እንደሚያገኙ ለመመልከት ተችሏል።

ለዚህም በምድብ አንድ እንደተገለፀው መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በቀረቡላቸው መጠይቆች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረት እንደሚወስዱ ገልፀዋል። ለዚህም የሰጧቸው ምክንያቶች፦

ሴቶች ጥያቄ ለመመለስ እጅ አያወጡም በዚህም እድል አያገኙም

ሴቶች ስለሚፈሩ ለመሳተፍ አይፈልጉም

መምህራን ሴቶችን ተሳትፎ አያአደርጉም፣ በችሎታም ከወንዶች ያንሳሉ ብለው ስለሚገምቱ ጥያቄ በተደጋጋሚ አይጠይቋቸውም፡

መምህራን ሴቶችን አዘውትረው ከጠየቁም የተማሪዎች አመለካከት ይለወጣል ብለው ስለማይፈሩ ሴቶችን ከወንዶች እኩል አያቀርቡም የሚሉት በሁሉም ምድቦች የሚማሩ ተማሪዎች ከሰጧቸው አስተያየቶች በአብዛኛው ተማሪ የተሰነዘሩ ምክንያቶች ናቸው፡፡

በመምህራንና በተማሪዎች በተሰጡት አስተያየቶች ሴቶች ከመምህሮቻቸው ጋር ያላቸው ቅርበት በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ ይህን በሚመለከትም ለተማሪዎች "በመማር-ማስተማሩ ሂደት ከአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ቅርበት" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ከመላሾቹ 82.4% ወንዶችና 37.9% ሴቶች "ከፍተኛ" ና "በጣም ከፍተኛ" ቅርበት እንዳላቸው ገልጸዋል፡ ከዚህ አንፃር ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ከመምህራቸው ጋር ቅርበት ሲኖራቸው ሴቶች በተቃራኒው ዝቅተኛ ቅርበት አላቸው፡፡ ይህም ከላይ በተማሪዎች ከተሰጠው አስተያየት ጋር የሚጣጣም ሆኖአል፡

በአጠቃላይ ተማሪዎቹ መምህሮቻቸው የሚሰጧቸውን ትኩረት ለመገምገም ለቀረቡላቸው አምስት ጥያቄዎች በስቱም ምድቦች የሚማሩ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች የሰጧቸው መልሶች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህራኑን ትኩረት ያገኛሉ ለማለት የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ይህም በምዕራፍ ሁለት ስር እንደተገለፀው በክፍል ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህራኑን ትኩረት ይወስዳሉ ማለት እነ Kelly (1988), Sunderland(1994), Irvin (1986), Potter(1987), Grima and Smith(1993) ካቀረቡት የጥናት ግኝት ጋር የሚጣጣም ሆኖ ተገኝቷል፡

4.3.2.2.2 የመምህራንን ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ውጤት

ሰንጠረዥ 22፡ መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከምድብ አንድ ተማሪዎች የተገኘ መረጃ ውጤት

| ተ.ቁ | ጉዳዩ | 5 | | | | 4 | | | | 3 | | | | 2 | | | | 1 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 6 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር/ሯ ለተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ስትሰጥ/ጪ የሚሰጠው/ሯ ማበረታቻ ወይም ሙገሳ | 6 | 35.3 | 9 | 31 | 8 | 47 | 7 | 24 | 2 | 11.8 | 4 | 13.8 | 1 | 5.9 | 5 | 17.2 | - | - | 4 | 13.8 |
| 7 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር/ሯ መልስ ስትሰጥ/ጪ ብትሳሳት/ቺ የሚያስከትሉት ትችት ወይም ገሳጺ/Reprimands/ | 3 | 17.6 | 5 | 17.2 | 6 | 35.3 | 6 | 20.7 | 4 | 23.5 | 7 | 27.6 | 3 | 17.6 | 7 | 24 | 1 | 5.9 | 3 | 103 |

ከሰንጠረዥ 22 ላይ ለመመልከት እንደሚቻለው መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ለቀረቡላቸው ሁለት ጥያቄዎች ከሰጧቸው አዎንታዊ መልሶች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የሚያገኙ መሆኑን ለመረዳት ይቻላል። ይህም ከቪዲዮ ምዝግቡ ውጤት ጋር የሚጣጣም ነው

ሰንጠረዥ 23 መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ቃላዊ ምላሽ ምጣኔ በተመለከተ ከሞዴብ ሁለት ተማሪዎች የተገኘ መረጃ ውጤት

| ተ.ቁ | ጉዳይ | 5 | | | | 4 | | | | 3 | | | | 2 | | | | 1 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህር/ሯ ለተማሪዎች ትክክለኛ መልስ ሲሰጡ/ሲመልሱ የሚሰጡት ማበረታቻ ቃላዊ ምላሽ | 5 | 22.7 | 4 | 18.2 | 7 | 31.8 | 6 | 27.3 | 5 | 22.7 | 6 | 22.3 | 3 | 13.6 | 4 | 18.2 | 2 | 9.1 | 2 | 9.1 |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህር/ሯ መልስ ሲሳሳቱ ለተማሪዎች/ሯ የሚያስከትሉት ትችት ቃላዊ ግብረ (Reprimands) | 8 | 33.3 | 5 | 22.7 | 5 | 20.8 | 4 | 18.2 | 4 | 16.7 | 6 | 27.3 | 5 | 20.8 | 5 | 22.7 | 2 | 8.3 | 2 | 9.1 |

ከላይ በሰንጠረዡ ለማሳየት የተሞከረው መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ ሲሆን ከተማሪዎቹ መልሶችም መምህሩ ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች የበለጠ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ምጋቢ ምላሽ እንደሚሰጡ ለመረዳት ተችሏል። ይህም ከቪዲዮ ምዝገባ ውጤት ጋር የሚጣጣም ነው።

ሰንጠረዥ 24፦ መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ በተመለከተ ከምድብ ስምንት ተማሪዎች የተገኘ መረጃ ውጤት

| ተ.ቁ | ይዘት | 5 | | | | 4 | | | | 3 | | | | 2 | | | | 1 | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | | ወንድ | | ሴት | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 6 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን ለጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስንሰጥ የሚሰጡን ማበረታቻ ቃላዊ መገብ | 9 | 23.7 | 5 | 29.4 | 14 | 36.8 | 6 | 35.3 | 7 | 18.4 | 4 | 23.5 | 5 | 13.2 | 2 | 11.8 | 3 | 7.9 | 2 | 11.8 |
| 7 | የአማርኛ ቋንቋ መምህራችን መልስ ስንሰጥ ስህተት የሚያስከትሉ ትችት ቃላዊ ግብረ /Reprimands/ | 12 | 31.6 | 2 | 11.8 | 8 | 21.1 | 6 | 35.3 | 9 | 23.7 | 3 | 17.6 | 4 | 10.5 | 2 | 11.8 | 5 | 13.2 | 3 | 17.6 |

በሰንጠረዥ 24 ላይ እንደተመለከተው መምህሩ ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡትን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ በሚመለከት ተማሪዎቹ ከሰጧቸው አዎንታዊ መልሶች ("ከፍተኛ" ና "በጣም ከፍተኛ" በማለት) ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ማግኘታቸውን ለመረዳት ተችሏል።

ሰንጠረዥ 24 ላይ ከቀረቡት ጥያቄዎች በተጨማሪም "በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከመምህርህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ቅርበት" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ከመላሾቹ 28ቱ ወይም 73.7% ወንዶችና 9 ወይም 53% ሴቶች ከመምህራቸው ጋር ያላቸው ቅርበት ከፍተኛ መሆኑን ከሰጡት አዎንታዊ መልስ ለመመልከት ተችሏል። በዚህም ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ከመምህራቸው ጋር የቀረበ ግንኙነት እንዳላቸው ለመረዳት ይቻላል።

መምህሩን የወንዶችንና የሴቶችን ንግግር ከማቋረጥ አንፃር ያላቸውን ትኩረት በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ከላይ ከተገኘው መረጃ ውጤት ጋር የሚጣጣም ነው። ይህም "የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ በንግግርህ/ሽ መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግርህ/ሽን የማቋረጥ ሁኔታቸው" በሚል ለቀረበ ጥያቄ በምድብ አንድ መጠይቁን ከሞሉት 17 ወንዶች 12ቱ ወይም 70.6%፣ ከ24 ሴቶች 11 ወይም 37.9% "ዝቅተኛ" ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት መልሰዋል። በዚህም በምድብ አንድ የሚያስተምሩት መምህር ከወንዶች ይልቅ የሴቶችን ንግግር የሚያቋርጡ መሆኑን ከመልሶቻቸው ለመረዳት ተችሏል።

በምድብ ሁለት ከላይ ለቀረበው ተመሳሳይ ጥያቄ የሰጡት ምላሽ ደግሞ መጠይቁን ከሞሉት 24 ወንዶች 15ቱ ወይም 62.5% ከ22 ሴቶች 17ቱ ወይም 31.8% መምህሩ በንግግራቸው መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግራቸው እንዲቋረጥ የማድረጋቸው ሁኔታ ዝቅተኛ መሆኑን ሲገልፁ፣ በዚህም መምህሩ ከወንዶች ይልቅ የሴቶችን ንግግር በተደጋጋሚ የሚያቋርጡ መሆኑን ከመልሶቻቸው እንረዳለን። ምክንያቱም በርካታ ሴቶች ተማሪዎች ለቀረበው ጥያቄ የሰጡት መልስ አዎንታዊ በመሆኑ ነው። ማለትም 41.2% "ከፍተኛ" ና "በጣም ከፍተኛ" ብለው ከመለሱት በመነሳት ነው። በምድብ ሶስትም ለተመሳሳይ ጥያቄ መጠይቁን ከሞሉት 38 ወንዶች 22 ወይም 57.9% እና ከ17 ሴቶች 9 ወይም 52.9% "ዝቅተኛ"ና "በጣም ዝቅተኛ" በማለት መልሰዋል። ከዚህ አንፃር በዚህ ምድብ የሚያስተምሩት መምህር በወንዶችም ሆነ በሴቶች ንግግር መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግራቸውን የማቋረጥ ሁኔታቸው ዝቅተኛ እንደሆነ ተማሪዎች ከሰጡት ምላሽ ለመገንዘብ ይቻላል።

በአጠቃላይ በዝርዝር ለማትረብ እንደተሞከረው መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ በሁሉም ምድቦች ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ማግኘታቸውን እንረዳለን።

በየምድቦቹ በሚማሩ ሴቶች ተማሪዎች መካከል የመምህሩን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ ደግሞ በምድብ ሶስት ማለትም ወንዶች በሚበዙበት ምድብ የሚማሩ ሴቶች

በምድብ አንድና ሁለት ከሚማሩት የበለጠ የመምህሩን አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽና ትኩረት ማግኘታቸውን በየምድቦቹ ከተገኙት መረጃዎች ለማየት ይቻላል። ይህም ከቢዲየ ምዝገባም ውጤት ጋር የሚጣጣም ነው።

የተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መምህራት ከሚሰጧቸው ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ጋር ያለውን ግንኙነት በተመለከተደግሞ በሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው መረጃ ውጤት እንደሚያሳየው ወንዶች ተማሪዎች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ያገኙ ሲሆን በተሳትፎም የተሻለ ውጤት አስመዝግበዋል። ሴቶች በተቃራኒው ከመምህሮቻቸው የሚያገኙት ትኩረትም ሆነ ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ዝቅተኛ በመሆን በክፍል ውስጥ ተሳትፎም ያነሰ ውጤት ማስመዝገባቸውን መረጃው አሳይቷል። ከዚህ አንፃርም በመምህሩ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽና በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መካከል አዎንታዊ ግንኙነት አለ ብሎ ለማጠቃለል ይቻላል።

በዚህም ይህ ጥናት Sunderland (1994), Bank and Hall (1997), Kabira and Masinjila (1997) እና ሌሎችም ሴቶች ከመምህሮቻቸው የሚያገኙት ድጋፍ ወይም ማበረታቻ በጣም ያነሰና በሚናገሩበት ጊዜም ንግግራቸው እንዲቀተል መምህራት የሚያደርጉላቸው ማበረታቻ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ከገለፁት ጋር የሚዛመድና ከላይ የተገለፀውን የምሁራኑን የጥናት ግኝት የሚደግፍ ሆኖአል።

# ምዕራፍ አምስት

## ማጠቃለያና አስተያየት

### 5.1. ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ ስር እንደተገለፀው ይህን ጥናት ለማካሄድ መነሻ የሆነው መሰረታዊ ጉዳይ ሴቶች ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በሚከናወን የመምህር ተማሪ ቃላዊ ተራክቦ የሚኖራቸው ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆኑን፣ መምህራን በመማር ማስተማሩ ሂደት ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ የተለያየ መሆኑ በተለያዩ ምሁራን መገለፁ ነው፡፡ ሆኖም በክፍል ውስጥ የመምህር ተማሪ ተራክቦ ላይ የጾታን ልዩነት የመረመሩ ጥናቶች የጥናታቸውን አቅጣጫ ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎች እኩል በሆኑበት ቡድንና ምድብ ያደረጉ ይሁን እንጂ የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎች መጠን ንፃሬ /Ratio/ የተለያየ የሆነበት ምድብ ወይም ቡድን ውስጥ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ የመረመሩ ጥናቶች ጥቂት ናቸው፡፡

ስለዚህም የሴት ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶች በሚበልጥበት፣ እኩል የሚሆኑበትና ከወንዶች በሚያንስበት ምድብ ውስጥ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር ምን ይመስላል? በሚለውና መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ይለያያልን? በሚለው ጥያቄ መነሻነት ጥናት ለማድረግ ተሞክሯል፡፡

የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ መጠን ሴቶች በሚበዙበት፣ ከወንዶች ጋር እኩል በሚሆኑበትና ወንዶች በሚበዙበት ምድብ እና መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡትን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ አስመልክቶ በጥናቱ ለመመለስ የተሞከሩት ጥያቄዎችን የሚከተሉት ናቸው፣

1. የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ጋር ሲነፃፀር፣
    - 1.1. ሴቶች በሚበዙበት ምድብ ምን ያህል ነው?
    - 1.2. ሴቶችና ወንዶች እኩል በሚሆኑበት ምድብ ምን ያህል ነው
    - 1.3. ወንዶች በሚበዙበት ምድብ ምን ያህል ነው?
2. መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ ይለያያልን?
3. የመምህሩ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ያለው ተፅዕኖ ምን ይመስላል?

እነዚህን የጥናት ጥያቄዎች በጥናቱ ለመመለስ እያንዳንዱ ምድብ ለ40 ደቂቃ በመማር ማስተማሩ ሂደት በቪዲዮ ካሜራ ተቀርጿል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በእያንዳንዱ ምድብ የሶስት ቀናት ምልከታ ተግባራዊ ሆኖአል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም መምህራንና ተማሪዎች የፅሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ከቪዲዮ ቀረፃው የተገኘው የተማሪዎች ተሳትፎ መጠን፣ የመምህራኑ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የሚያሳይ ውጤት በስታቲስቲካዊ ስሌት መሰረት እንዲተነተን ተደርጓል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረትም የጥናቱ ዋንኛ ጥያቄዎች እንደሚከተለው ተመልሰዋል፡፡

ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች በሚበዙበት፥ እኩል በሚሆኑበትና ወንዶች በሚበዙበት የሴቶች ተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መጠን በተመለከተ ከሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያሳየውና በምዕራፍ አራት እንደተብራራው በሶስቱም ምድቦች የወንዶች ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከሴቶች የተሻለ መሆኑ ተረጋግጧል። ይህም (Webb,1984) የወንዶችና የሴቶች ተማሪዎች መጠነ-ንፃሬ የተለያየ በሆነበት ቡድን ውስጥ የወንዶችንና የሴቶችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ልዩነት በመመርመር ያገኙት ውጤት ጋር የሚቃረን ነው። ቀደም ብሎ የተጠቀሱት ምሁር ሴቶች በሚበዙበት ቡድን የሴቶች ተማሪዎች ተሳትፎ ከወንዶች የበለጠ መሆኑንና ሴቶችና ወንዶች እኩል በሆኑበት ቡድን ተሳትፎአቸውም እኩል እንዲሁም ወንዶች በሚበዙበት ቡድን የወንዶች ተሳትፎ ከሴቶች የበለጠ መሆኑን በጥናታቸው ውጤት ገልፀዋል። ይህ ጥናትም ከላይ የተጠቀሰውን የጥናት ግኝት መላምት አድርጎ ቢነሳም የተገኘው ውጤት ግን መላምቱን የሚያፈርስ ሆኖ ተገኝቷል። ምንም እንኳን በወንዶችና በሴቶች መካከል የታየው ልዩነት በስታቲስቲካዊ ስሌት የጎላ ባይሆንም በሶስቱም ምድቦች ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ እንዳላቸው ጥናቱ አረጋግጧል።

በዚህ ጥናት ውጤት መሰረትም የሴት ተማሪዎች በየምድቦቹ መብዛትና ማነስ በክፍል ውስጥ ተሳትፎአቸው ላይ ተፅዕኖ እንደሌለው ለማረጋገጥ ተሞክሯል። ምክንያቱም ሴቶች በሚበዙበትም፣ በሚያንሱበትም ምድብ ተሳትፎአቸው ልዩነት እንደሌለው ከመረጃ ትንተናው ለመመልከት ተችሏል።

ስለዚህም Webb(1984) ሴቶችና ወንዶች አብረው በሚማሩባቸው ምድቦች የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ዝቅተኛ የሚሆንባቸው ምክንያቶችን ሴቶች በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ዝቅተኛ በመሆናቸውና ሴቶች ከወንዶች ጋር ሲማሩ ተሳትፎአቸው የሚቀንስ በመሆኑ ሊሆን ይችላል በማለት ይገልፃሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት ምክንያቶች በዚህ ጥናት ለተገኘው ውጤት ሴቶች በአጠቃላይ በክፍል ውስጥ ተሳትፎ ዝቅተኛ መሆናቸው የሚለው ምክንያት ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም ሴቶች ከወንዶች በሚበዙበትም ሆነ እኩል በሚሆኑበትና ከወንዶች በሚያንሱበት የሴቶች ተሳትፎ እኩል ሲሆን ከወንዶችም ያነሰ ነው። ስለሆነም የዚህ ጥናት ግኝት Potter (1986), Irvin (1987), Kelly (1988), Sunder land (1994), King and Hill (1994), Golombok and Fivush,(1995), Kilo (1995) እና ሌሎችም በርካታ ተመራማሪዎች በጥናቶቻቸው ከገለፁት ሀሳብ ጋር የሚጣጣም ነው። እንዲሁም ለሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ማነስ ዋና ዋና ምክንያቶች መምህራንም ሆነ ተማሪዎች በሰጧቸው አስተያየቶች እንደሚከተለው ገልፀዋል፤ ሴቶች አይናፋር በመሆናቸውና ብሎት ይስቁብኛል ከሚል ለመናገር ስለማይደፍሩ፣ ለመሳተፍ ቢፈልጉም እንኳን በመምህሮቻቸው ስለማይበረታቱ፤ በመማር ማስተማሩ ሂደት ከመምህሮቻቸው ጋር ያላቸው ቅርበት ዝቅተኛ በመሆኑ፤ መምህራንም ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ከወንዶች እኩል እድል ስለማይሰጧቸውና መምህራን ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ፤ ሴቶች በባህል ተፅዕኖ ከወንዶች እኩል ማውራትና መከራከር ስለማይችሉ የሚሉት ናቸው። እነዚህ ምክንያቶች ከላይ በተጠቀሱትና በሌሎችም ምሁራን የተጠቀሱ መሆናቸውን ከምዕራፍ ሁለት ለመመልከት ይቻላል።

የመምህራኑን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተመለከተ፣ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል የሚታየው ልዩነት በስታቲስቲካዊ ስሌት የጎላ ባይሆንም ወንዶች ከሴቶች የተሻለ የመምህሩን ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ የሚያገኙ መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል:: ስለዚህ በሶስቱም ምድቦች የሚያስተምሩ መምህራን ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ተደጋጋሚ ዕድል በመስጠት፣ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች ትዕዛዞችን ለማዘዝ ሲፈልጉ ስማቸውን በተደጋጋሚ በመጥራት፣ የበለጠ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ምጋቤ ምላሽ በመስጠት፣ የተማሪዎችን መልስ ከመድገም አንፃር ከሴቶች ይልቅ ለወንዶች የበለጠ ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ እንደሚሰጡና ወንዶች ከሴቶች የተሻለ ተሳትፎ ሊኖራቸው እንደቻለ የጥናቱ ውጤት አመልክቷል:: በመምህራንም ሆነ በተማሪዎች የተሰጠው አስተያየትም በክፍል ውስጥ ተሳትፎም ሆነ የመምህሩን የተሻለ ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በማግኘት ወንዶች ከሴቶች የበለጡ መሆናቸውንና ለዚህም ወንዶች ጥያቄ ለመመለስ እንዲችሉ ተደጋጋሚ ዕድል በማግኘታቸው ስለማይፈሩ ከመምህራንም ጋር ቅርበት ስላላቸው ደፋሮች በመሆናቸው እንደሆነ ገልፀዋል::

መምህራን ለወንዶችና ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረትና ቃላዊ ምጋቤ ምላሽ በተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ላይ ያለውን ተፅዕኖ በሚመለከት በተደረገው ምርመራ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ የመምህሩን ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ የሚያገኙ ሲሆን፣ በክፍል ውስጥ ተሳትፎም የተሻሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ተሞክሯል:: ስለዚህ የመምህሩን ትኩረትና ምጋቤ ምላሽ በተሻለ ሁኔታ የሚወስዱ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ተሳትፎም የተሻሉ ናቸው በማለት ጥናቱን ለማጠቃለል ይቻላል

## 5.2. አስተያየት

ባለፉት ምዕራፎች እንደተገለፀው፣ በክፍል ውስጥ በሚከናወን የመምህር ተማሪ ተራክቦ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከወንዶች በጣም ያነሰ ነው:: ለዚህም በርካታ ምሁራን የተለያዩ ምክንያቶችን የተገለሉ በዚህ ጥናት ተጠኝ መምህራንና ተማሪዎችም የሰጧቸው አስተያየቶች ምሁራኑ ከሰጧቸው ምክንያቶች ጋር የሚጣጣሙ ናቸው:: ስለዚህም እነዚህን ምክንያቶች በመገንዘብ ለሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ መሻሻል መፍትሄዎችን መፈለግ አስፈላጊ ነው:: በዚህ ጥናት የተሞከረውም የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሴቶች በሚበዙበት፣ ከወንዶች ጋር እኩል በሚሆኑበትና ወንዶች በሚበዙበት ምን መልክ እንዳለውና በየትኛው ምድብ የተሻለ ተሳትፎ ይኖራቸዋል በሚል ሁኔታ የተደረገ ምርምርም በመሆን ለሴት ተማሪዎች ተሳትፎ መሻሻል መፍትሄ ለመጠቆም ታስቦ ነው በዚሁ መሰረት ጥናቱ ያነሳቸውን ጥያቄዎች በመመለስና በጥናቱ ላይ በመመስረት የሚከተሉት አስተያየቶች ቀርበዋል::

5.2.1. ሴቶች ተማሪዎች ለራሳቸው የሚሰጡትን ግምት ከፍ እንዲያደርጉና የሚኖራቸውን ፍርሃት እንዲያስወግዱ በትምህርት ቤቶች ወንዶችንና ሴቶችን እኩል የሚያሳትፍ የተለያየ የውይይት መድረክ በመክፈት ሴቶችና ወንዶች በጋራ እንዲወያዩና እንዲከራከሩ ቢደረግ የሴቶች ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሊሻሻል እንደሚችል የጥናት አቅራቢዋ እምነት ነው::

5.2.2. አብዛኛዎቹ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት ጥያቄ የሚጠይቁ እጅ ያወጡ ተማሪዎችን ብቻ ነው። ነገር ግን ሴቶች ተማሪዎች ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ቢፈልጉም እጃቸውን ለማውጣት እንደሚፈሩ በጥናቱ ተደርሶበታል። ስለዚህ መምህራን ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ እጅ ያላወጡ ተማሪዎችንም ሲጠይቁ ሁሉንም በጋራ በሚያሳትፍ መንገድ ቢጠይቁ ሴቶች የመሳተፍ እድል ያገኛሉ፤ በዚህም ተሳትፎአቸው ሊሻሻል ይችላል።

5.2.3. መምህራን ማህበረሰቡ ለሴት ተማሪዎች ያለውን ዝቅተኛ አመለከካከት በማንፀባረቅና ሴቶችን ከወንዶች እኩል ካቀረቡ የተማሪው አመለከካት ይቀየራል በማለት ለወንዶችና ለሴቶች የሚሰጡት እኩል ያልሆነ ትኩረት /Unfair treatment/ በሴቶች ተማሪዎች ተሳትፎ ላይ ተፅዕኖ እንዳለው በመገንዘብ ለወንዶችና ለሴቶች እኩል ትኩረት ቢሰጡ የሴት ተማሪዎች ተሳትፎ ከወንዶች እኩል ወይም የተሻለ ሊሆን እንደሚችል እንዲገነዘቡ የመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት ጥረት የስፈልጋል።

5.2.4. በሌሎች የትምህርት አይነቶችና በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ተመሳሳይ ጥናት ቢደረግ፣ በመምህር ተማሪ የክፍል ውስጥ ተራክቦ ላይ የሴት ተማሪዎችን ተሳትፎ ዝቅተኛ እንዲሆን የሚያደርጉት ችግሮች ይበልጥ ስለሚታወቁ ተሳትፎአቸው እንዲሻሻል ተጨማሪ መፍትሄ ለመፈለግ ያስችላል።

## ዋቢ ምንጮች (References)


Abdulkadir Ali. 1983. "Student-Teacher Interaction in English Classes in Four Schools in Addis Ababa." (Unpublished M.A. Thesis) submitted to ILS. Addis Ababa University.

Allwright, D. 1991. "Integrating 'Research' and 'Pedagogy': Appropriate Criteria and Practical Possibilities." Lancaster Center for Research in Language Education.

Allwright, D. and Bailey, M.K. 1991. Focus on Language Classroom: An Introduction to Classroom Research for Language Teachers. Cambridge: Cambridge University Press.

Almaz Eshetie. 1991. "Perspectives on Gender and Development." In Gender Issues in Ethiopia." Tsehay Berhane Selassie (Ed.) Addis Ababa.

Amanuel Gebru. 1996. "Gender Differences in participation in Group Discussion in Freshman English Classes at AAU." (Unpublished M.A. Thesis) submitted to ILS, Addis Ababa University.

Bank, B.J. and Hall, P.M. (Ed.) 1997. Gender, Equity, and Schooling: Policy and Practice. New York. Garland Publishing, Inc.

Betz, N. and L. Fitzegerald. 1987. The Career Psychology of Women. London. Academic Press, Inc.

Clark, A. And Tranford, J. 1995. "An Investigation of Discrepancy in Attitudes Performance between Boys and Girls in Modern Language. Gender and Education. 7(3): 317-330.

Coates, J. 1993. Women, Men and Language : A Socio Linguistic Account of Sex Differences in Language. London: Longman.

Darling, John and A. Glendinning. 1996. Gender Matters in Schools. " Pupils and Teachers.

Ehrlich, S. 1997. "Gender As Social Practice." Dec. 1997. Vol. 19 No. 4 Cambrdige University Press.

Genet Zewdie. 1991. "Women in Education : A Study of Academic Performance and Participation of Female Students in High Schools of Addis Ababa." Addis Ababa.

Golombok, S. And Robyn Fivush. 1995. Gender Development. Cambrdige: Cambridge University Press..

Hammersley, M. 1993. "An Evaluation of A Study of Gender in Imbalance in Primary Schools." In: Woods, P. And Hammersley, M. (Eds.) Gender and Ethnicity in Schools. Richard Clay Ltd.

Hilton, T.L. and Berglund, G.W. 1979. "Sex Difference in Mathematics Achievement." Journal of Educational Testing Service. Princeton.

Holmes, J. 1994. "Improving the Lot of Female Language Learners." In Sunderland, J. (ed.) Exploring Gender: Questions and Implications for English Language Education. Prentice Hall.

Irvine, J. 1986. "Teacher-Students Interactions: Effects of Students Race, Sex and Grade Level." Journal of Educational Psychology. 78(1):14-21.

Jones, L. And L. Smart. 1995. "Confidence and Maths: A Gender Issue." Gender and Education. 7(2)

Kabira, W.M. and MaSinjila, M. 1997. "Classroom Interaction and ABC of Gender Analysis Frame Work." Nairobi.

Kelly, A. 1988. "Gender Difference in Teacher-Pupil Interaction: A Meta Analytic Review". Research in Education. Vol 39(1), 1-3.

King, E.M. and Hill, M.A. 1983. Women's Education in Developing Countries. The Hopkins University Press.

Lee, V.E. and Bryk, A.S. 1986. "Effects of Single-Sex Secondary Schools on Students Achievement and Attitudes." Journal of Educational Psychology. 78(5):381.

Lindroos, M. 1995. "The Production of 'Girl' in An Educational Setting. Gender and Educaiton.7(2) 143-154

Lockead, M.E. and Hall, K.P. 1970. "Conceptualising Sex and as a States Characterstics: Applications to Leadership Training Strategies." In Berliner, David. 1987. Educational Psychology. New York: Heignters Mifflin. Company.

Lott, B. 1987. Women's Lives: Themes and Variations in Gender Learning.California:Brooks/cole Pub. Company

Lyle, Sue. 1997. "An Investigation in to the attitude of Teachers at Key Stage 2 to Speaking and Listening in the National Curriculum in Wales." Educational Studies. 23(1): 39-52.

MacCoal, P. 1994. "Teacher-Pupil Interactions in Mathematics Classes. A Study of Current Classroom Practice in Selected Secondary Schools in Addis Ababa." (Unpublished M.A. Thesis.) A.A.U.

Maccoby, E. 1990. "Gender and Relation Ships: A Developmental Account." American Psychologist. 45:513-520.

Maccoby, E. And Jacklin, C.N. 1974. The Psychology of Sex Differences. Stanford, CA: Stanford University.

Marsh, Herbert. 1989. "Effects of Attending Single-Sex and Coeducational High Schools on Achievement, Attitudes, Behaviours and Sex Differences." Journal of Educational Psychology. 81(1): 70-85.

Odaga, A. And Heneveld, W. 1995. Girls and Schools in Sub-Saharan Africa From Analysis to Acltion. Washington: DC.

Potter, E.F. 1978. "Sex Differences in Classroom Participation." A Paper Present at the Annual Convention of the South Eastern Psychological Association. Atlanta: Georgia, March, 15-18, 1978.

Richards, J. and D. Nunan (Eds.) 1990. Second Language Teaching Education. Cambridge: CUP.

Schneider, F.W. and Coutts, L.M. 1982. "The High School Environment: A Comparison of Coeducational and Single-Sex Schools." Journal of Educational Psychology. 74(6): 898.

Semunesh Abebe. 1997. "Female Students' Level of Assertiveness and their Verbal Interaction in EFL Classrooms in High School in Addis Ababa." (Unpublished M.A. Thesis) submitted to ILS, Addis Ababa University.

Spender, D. 1982. Invisible Women. London. The Women's Press.

Sunderland, J. 1992. "Gender in the EFL Class room." ELT Journal. Vol. 46(1)81-90

______ 1994. "Differential Teatement by Gender in the EFL Classroom: Using Exparticipant Perspectives." In Sunderland, J. (ed.) Exploring Gender: Questions and Implications for English Language Education. New York: Prentice Hall.

______ 1998. "Girls being Quite: A Problem for Foreign Language Classrooms. In Language Teaching Research. V. 2(1) pp.49.

Thomas, K. 1990. Gender and Subject in Higher Education. Open University Press.

Thomas, M. 1991. Classroom Interaction. Oxford: OUP.

Tsige Haile. 1991. "An Assessment of the Acadfemic Persformance of Female Students in Higher Educaitonal Institution." Addis Ababa. In Women and Development in Eastern Africa. An Agenda for Research. (eds.) Zeinab El-Bakyi and Besha, R.M. OSSREA. A.A.

Victoria, R. And Diane, Richards. 1997. Introducing Women's Studies. (Second Edition): MaCmillan Press.

Webb, N. 1984. "Sex Differences in Interaction and Acheivement in Co-Operative Small Group." Journal of Educational Psychology. 78(1): 33-44.

World Bank. 1996. "Girls and Schools in Sub Saharan Africa: From Analysis to Action." In Findings. Africa Region.

ብርሃኑ ገብረማርያም። 1986። "የመምህር-ተማሪ ተራክቦ በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በሚገኙ አራት ከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ጊዜያት ውስጥ እንደሚታየው።" (ያልታተመ ኤም. ኤ. ቴስስ) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ፋንታ ደምሴ። 1989። "ቋንቋን በመማር ረገድ የጾታ ልዩነት።" (ያልታተመ ኤም. ኤ. ቴስስ) አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

# አባሪዎች

አባሪ አንድ

## ምዝግብ ቪዲዮ (Vedio Transcription)

<u>ምድብ አንድ</u>

መ.ር: ሰነዘረ የሚለው ቃል በአድራጊ ሲረባ ምን ይባላል?

ወ.ተ: ሰነዘረ

መ.ር: ሰነዘረ።     አስደራጊ ሲሆን?

ወ.ተ: አስነዘረ

መ.ር: አስነዘረ። በአጻራጊ ላይ ሲሆን?

ሴ.ተ: አሰናዘረ

መ.ር: አሰናዘረ። እሺ! ደራራጊ ላይ ሲሆን?

ሴ.ተ: ተሰነዘረ

መ.ር: ልክ አይደለም። አደራራጊ ላይ ሲሆን?

ሴ.ተ: አሰናዘረ

መ.ር: ልክ አይደለም

ወ.ተ: አሰናዘረ።

መ.ር: ልክ አይደለም

ወ.ተ: አስነነዘረ

መ.ር: ትክክል ነው። አስነነዘረ። ተደራጊ ላይ ሲሆን?

ወ.ተ: መሰናዘር

መ.ር: ልክ አይደለም

ወ.ተ: ተሰነዘረ

መ.ር: ተሰነዘረ። ተጻራጊ ላይ ሲሆን?

ሴ.ተ: አሰናዘረ

መ.ር: ልክ አይደለም። ተጻራጊ ላይ ሲሆን?

ሴ.ተ: ተሰናዘረ

መ.ር: ልክ አይደለም ። ተጻራጊ ላይ ሲሆን?

ሴ.ተ: ተሰናዘረ

ወ.ተ: ተሰናዘረ ትርጉሙ ምንድን ነው?

መ.ር: ተሰናዘረ። ትክክል! ተደራራጊ ላይ ሲሆን?

ወ.ተ: ተሰነነዘረ

መ.ር: ተሰነነዘረ። ትክክል! ደራራጊ?

ሴ.ተ: ተሰንዘሯል

መ.ር: አይደለም።

ሴ.ተ: ተሰናዘረ

መ.ር: ተሰናዘረ። ደራራጊ ላይ ሲሆን? እሽ! አስቴር!

ሴ.ተ፡ ሰነጫዘረ

መ፡ ሰነጫዘረ፡፡ እንደምታውቁት ትናንት በሰጠኋችሁ ማስታወሻ ላይ እንዳሳየኋችሁ እነዚህ ቃሎች የየራሳቸው የሆነ ተግባር አላቸው፡፡ አድራጊ ማለት አንድ ሰው አንድ ጉዳይ ሲፈፅም በራሱ አነሳሽነት አንድ ጉዳይ ሲፈፅም ነው፡፡ አድራጊ ማለት ሰነዘረ ስንል አንድ ሰው የመሰንዘር ተግባር ፈፀመ ማለት ነው፡፡ አስሰነዘረ ስንል ምን ማለታችን ነው? አስሰነዘረ ስንል?

ወ.ተ፡ ድርጊቱን እሱ አስፈፀመ፡፡

መ፡ አዎ ድርጊቱን እንዲፈፅም ትዕዛዝ ሰጠ ነው፡፡ እሱ የሚለውን ቅጥያ እንጠቀማለን፡፡ አድራጊ ላይስ? አዳራጊ ማለት ምን ማለት ነው? አዳራጊ ስንል ምን አድራጊ ማለት ነው?

ወ.ተ፡ (ድጠድቃል አይሰማማም)

ሴ.ተ፡ ድርጊቱን የሚፈፅመውን ሰው ሌላ ሰው ሲያግዘው ማለት ነው፡፡

መ፡ አዎ! ድርጊቱን የሚፈፅመውን ሰው ስንተባበር ማለት ነው፡፡ ወይም ስናግዘው ማለት ነው፡፡ አደራራጊስ? አደራራጊ? ሀብታሙ!

ወ.ተ፡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ነገሮችን የሚያግዝ ድርጊቱን የሚያስፈፅም፡፡

መ፡ አዎ! ሁለት ሰዎችን ወይም ቡድኖችን አንድ ድርጊት እንዲፈፅሙ ትዕዛዝ የሚሰጥ ወይም የሚያሰጥ ማለት ነው፡፡ ተደራጊስ? ተደራጊ?

ሴ.ተ፡ ቃላቶች ድርጊት ተቀባይ ሲሆኑ ድርጊት አድራጊ ሳይሆን ድርጊት ተቀባይ፡፡

መ፡ አዎ! ድርጊት ተቀባይ ድርጊት የሚፈፀምበት አድራጊ ሳይሆን ድርጊት ተቀባይ ድርጊቱን የሚቀበል ማለታችን ነው፡፡ እሺ! ተሰናጫዘረስ ምንድን ነው? ተሰነዛዘረ? ሰዎቹ ተሰነዛዘሩ ወይም በቃላት ውስጥ ተሰነዛዘሩ ስንል ምን ማለታችን ነው? ሀብታሙ!

ወ.ተ፡ ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች አንድን ነገር በጋራ ሲያደርጉ የሚታይ

መ፡ ከሁለት በላይ የሆኑ ሰዎች አንድን ድርጊት ተለዋወጡ አንድ ድርጊት ተፈፃፀሙ! ድርጊት መፈፃፀም ተካሄደ ማለታችን ነው፡፡

ደራራጊስ ምንድን ነው? የደራራጊ ስራው ምንድን ነው?

ወ.ተ፡ አንድ ድርጊት እየተደጋገመ መፈፀም ነው::

መ.ር፡ አንድ ድርጊት እየተደጋገመ መፈፀሙን የሚያሳይ ነው:: ሁለተኛው ግን ቀመስ ነው:: ቀመስ በአድራጊ አምድ ምን ይሆናል?

ሴ.ተ፡ ቀመስ

መ.ር፡ እራሱ ቀመስ ይሆናል:: በአስደራጊ አምድ ሲሆን? አስቀመስ ይሆናል:: በአዳራጊ አምድ ሲሆን? በአዳራጊ አምድ ሲሆን?

ሴ.ተ፡ አቃመሰ::

መ.ር፡ አቃመሰ:: በአደራራጊ አምድ ላይ ሲሆን?

ወ.ተ፡ አተማመሰ::

መ.ር፡ አተማመሰ:: በተደራጊ አምድ ላይ ሲሆን ምን ይሆናል?

ወ.ተ፡ ተቃመሰ

መ.ር፡ በተደራጊ? በተደራጊ ላይ ሲሆን? ተቃመሰ አይደለም የሚሆነው::

ሴ.ተ፡ ተቀመሰ

መ.ር፡ ተቀመሰ ነው የሚሆነው:: ተዳራጊ አምድ ሲሆንስ? ተዳራጊ ሲሆን?

ወ.ተ፡ ተቃመሰ

መ.ር፡ ተቃመሰ:: በተዳራጊ አምድ ሲሆን?

ወ.ተ፡ ተተማመሰ

መ.ር፡ ተተማመሰ:: በደራራጊ አምድ ሲሆንስ?

ሴ.ተ፡ ቀማመሰ

መ.ር፡ ቀማመሰ:: ሶስተኛው አምድ ረበሸ በአድራጊ አምድ ሲሆን

ሴ.ተ፡ ረበሸ እራሱ::

መ.ር፡ በአስደራጊ አምድ ሲሆን?

ወ.ተ፡ አስረበሸ::

ሴ.ተ፡ አራበሸ አይደለም እንዴ ቲቸር የሚባለው?

መ.ር፡ (አይደለም)አስረበሸ ነው የሚባል በአዳራጊ አምድ ሲሆን?

ሴ.ተ፡ አራበሸ

መ.ር፡ አራበሸ:: እም! በአደራራጊ አምድ ሲሆን?

ወ.ተ፡ አረባበሸ:: (ቀጥሎ ይናገራል፡ ጥያቄ የሚጠይቅ ይመስላል)

መ.ር፡ አረባበሸ ነው የሚባለው ምክንያቱም አዳራጊ ስለሆነ ነው አምዱ. በተደራጊ አምድ ሲሆን?

ሴ.ተ፡ ተረበሸ

መ.ር፡ ተረበሸ:: በተዳራጊ አምድ ሲሆን?

ወ.ተ፡ ተረባበሸ::

መ/ር: ተረባበሽ:: አራተኛው ነገደ የሚለው ግስ ይሆናል:: ነገድ በአድራጊ አምድ?

ሲ.ተ: ነገደ

መ/ር: ነገደ እራሱ:: በአስደራጊ አምድ ሲሆን? በአስደራጊ አምድ?

ሲ.ተ: አናገደ::

መ/ር: አናገደ ይሆናል እንዴ? አናገደማ አይሆንም:: ይሄንን አካሄድ እነዚህ ቃሎች በሙሉ አላቸው:: በውስጣቸው ምን መነሻ ቅጥያ አላቸው?

ሲ.ተ: አስነገደ::

መ/ር: የለም! ጥያቄውን መልሽልኝ! እነኝህ ግሶች ለየት የሚያደርጋቸው ነገር አለ አይደል? ከሌላው ለየት የሚያደርጋቸው ነገር ምንድን ነው? ሀብታሙ (የተማሪ ስም ጠሩ)

ወ.ተ: "እሱ" ነው?

መ/ር: "አስ" የሚል ቅደመ ግንድ ቅጥያ አላቸው ስለዚህ ነገደ የሚለው ምን ይሆናል?

ተ (በሙሉ) አስነገደ::

መ/ር: እሺ! በአጻፊጊ አምድ ሲሆን ምን ይሆናል?

ሲ.ተ: አናገደ::

መ/ር: በአስጻፊጊ አምድ ሲሆን? አነጋገደ ነው:: በተጻራጊ አምድ ስር ሲሆንስ? እሺ?

ሲ.ተ: ተናገደ

መ/ር: እም! ተናገደ:: በተጻፊጊ አምድ ሲሆን?

ሲ.ተ: ተነጋገደ

መ/ር: በደራፊጊ አምድ ስር ሲሆን?

ወ.ተ: ነጋገደ

መ/ር: ነጋገደ እሽ! ለበሰ የሚለውን ግስ እናያለን:: ለበሰ በአድራጊ አምድ ስር ሲሆን? እሽ!

ሲ.ተ: ለበሰ::

መ/ር: ለበሰ እራሱ እሽ! በአስደራጊ አምድ ስር ሲሆን?

ሲ.ተ: አስለባበሰ

መ: አስለበሰ ነው:: በአደራጊ አምድ ስር ሲሆን?

ሲ.ተ: አስለበሰ::

መ/ር: አለባበሰ:: በተጻፊጊ አምድ ስር ሲሆን?

ወ.ተ: ተለበሰ

መ/ር: ተለበሰ እም! በደራፊጊ አምድ ስርስ?

ወ.ተ: ተላበሰ::

መ/ር: ተላበሰ:: በተደራራጊ አምድ ስር? ተለባበሰ:: በደራራጊ አምድ ስር

ወ/ተ: ለባበሰ

መ/ር: ለባበሰ እሺ! ስድስተኛው ቀደስ ነው:: በአድራጊ አምድ ስር ሲሆን ምን ይሆናል?

ሴ/ተ: ቀደሰ::

መ: ቀደሰ እራሱ:: በአስደራጊ አምድ ስር?

ወ/ተ: አስቀደሰ

መ/ር: አስቀደሰ:: በአዳራጊ አምድ ስር?

ሴ/ተ: ቀደሰ

መ/ር: በአደራራጊ? በአደራራጊ አምድ ስር ሲሆን ምን ይሆናል?

ሴ/ተ: አቀደሰ

መ/ር: አቀደሰ:: አቀደሰ ምንድን ነው ትረጉሙ? ፍችው ምንድን ነው? አቃደሰ?

እሺ!

ወ/ተ: ሁለት ካህናት ቢኖሩ አንዱ ካህን ሌላውን አቀዳደሰ አብሮ ቅዳሴ ቆመ

መ/ር: አቀዳደሰ አይደለም አቃደሰ ምንድን ነው?

ወ/ተ: አቃደሰ ማለት ሰውዬው አብሮ ቅዳሴውን ፈፀመ ማለት ነው::

መ/ር: አዎ! ቅዳሴ ሲፈፀም እገዛ አደረገ:: ቅዳሴ ሲያደርግ ሲቀደስ አገዘው:: ወይም ትብብር አደረገ ማለት ነው:: እሺ! እዛጋ!

ሴ/ተ: አቀዳደሰ

መ/ር: አቀዳደሰ:: ቀደሰ የሚለው የግዕዝ ቃል ነው በአማርኛ ፍቺው ምንድን ነው? ቀደሰ?

ሴ/ተ: ዘመረ

መ/ር: አይደለም:: እሺ! ዮሴፍ!?

ወ/ተ: ፀለየ

መ/ር: ፀለየ! አመሰገነ:: አቀዳደሰ ሲባል ምን ማለት ነው? እንዲመሰገኑ አደረገ:: ምስጋና እንዲለዋወጡ ትዕዛዝ ሰጠ ማለት ነው:: እሺ! ተደራጊ? ተደራጊ ላይ ምን ይሆናል?

ሴ/ተ: ተቀዳደሰ

መ/ር: ተቀዳደሰ:: ደራራጊ ላይ ቀዳደሰ እሺ! ይችኛዋን በዚህ መልክ ስሯት:: ወደ መልመጃው እንሂዳለን:: መልመጃውን ስሩት ብያችሁ ነበር:: አይደል? መልመጃ አንድን አብረን እንሰራለን:: ምንባቡን እንብቤላችኋለሁ:: በዛ መሰረት የመልመጃ አንድን ጥያቄ በቃል ሰርተን ወደ መልመጃ ሁለት እናልፋለን:: እሺ! መልመጃ አንድ አንደኛው ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት መልስ ይላል:: አንድ ሰው የልጅነት ጊዜውን በደበልጥ የሚያስታውሰው በምን

ምክንያት ነው ይላል? አንድ ሰው ተማሪዎች (በጠቅላላ) አቋረጡትና አልፃፍንም በማለት ተናገሩ።

መ/ር: አላፃፍኳችሁም? ካስበብኩላቸሁ በኋላ እየተነሳችሁ መልሱልኝ አንድ ሰው የልጅነት ጊዜውን የሚያስታውሰው በምን ምክንያት ነው? በምንባቡ መሰረት የሚለው የሚያስታውስበት ምክንያት ምንድን ነው? ለምንድን ነው የልጅነት ጊዜውን የሚያስታውሰው?

ሴ/ተ: አርጅቶ በልጅነት የሰራቸውን ስራዎች መስራት በማይችልበት ወቅት

መ/ር: አዎ! የልጅነት ጊዜ ምን ስለሆነ ነው።

(አንድ ተማሪ ሲቷ የተናገረችውን እንድትደግም ጠየቀ።)

መ/ር: እጃችሁን አውጡ። የልጅነት ጊዜ ምን ስለሆነ ነው? የሰው ልጅ ሁልጊዜ የልጅነት ጊዜውን ያስታውሳል ይላል ምንባቡ ላይ ታስታወሱ እንደሆን እና የልጅነት ጊዜውን የማያስታውስበት ምክንያት ምንድን ነው? እሽ!

ሴ/ተ: የማይመለስ ነገር ስለሆነ ነው።

መ/ር: የማይመለስ ብቻ በመሆኑ ነው እንዴ? የልጅነት ጊዜ በተለይ በምን ባህርይው ነው የሚታወቀው? በልጅነት ጊዜያችን ምንድን ነው የምናከናውነው ነገር? እሺ! ህቢታሙ!

ወ/ተ: የጨዋታ ጊዜ

መ/ር: አዎ! የጨዋታ ጊዜ በመሆኑ፥ ሀላፊነት የሚሰማን ጊዜ ባለመሆኑ እሽ! ለ/ የአዋቂነት ጊዜ ተለይቶ የሚታወቀው በምንድን ነው? አንድ ሰው አዋቂ ሆነ። የልጅነት ጊዜውን አልፎ፥ የወጣትነት ጊዜውን አልፎ አዋቂ ሆነ የሚባለው ምን ሲሆን ነው?

ሴ/ተ: ሀላፊነት የሚሰማን ማለት ነው? በማለት ጠየቀች። (መምህሩ መልስ ሰጡ አይሰጥም)

ወ/ተ: ሀላፊነት ሲሰማው። እራሱን ሲችል።

መ/ር: አዎ! ሀላፊነት ሲሰማው። እራሱን ሲችል። ሌሎችን ማስተዳደር ሲጀምር ነው። አዋቂነት እሺ! አንድ ሰው ምራቁን የዋጠና ጭምት የሚሆነው በየትኛው የዕድሜ ክልል ነው ይላል?

ወ/ተ: ከአርባ አመት በኋላ።

መ/ር: ከአርባ አመት በኋላ ያለው ጊዜ ምን በመባል ይታወቃል?

ወ/ተ: ጉርምስና

መ/ር: ጉርምስና ወይም በምንባቡ መሰረት አዋቂነት ያዋቂነት ጊዜ ነው የሚለው ምንባቡ ላይ። እሺ አንድ ሰው በእርጅና ምክንያት ወደ ህፃንነት መመለስ የሚፈልገው መቼ ነው?

ምን የሚባል የዘመን ክልል ሲደርስ ነው? ሀብታሙ(የተማሪን ስም ጠሩ)

ወ/ተ (ሀብታሙ)የመጃጀት

መ/ር አዎ! የመጃጀት ዘመን ሲደርስ ነው:: በምንባቡ ላይ እንደተነገራችሁ ምንባቡ ላይ እንዳየነው የሰው ልጅ እድሜ በመጀመሪያ ልጅነት ከዚያ በኋላ ጉርምስና ከዚያ በኋላ እርጅና መጨረሻ ላይ መጃጀት ዙሪያ ጥምጥም ነው የሚሽከረከረው እንደምታዩት መጃጀት ላይ ወደ ልጅነት የተቃረበበት ጊዜ ነው እሺ! ሁለተኛው የሚከተለውን ሀ.ነገሮች በምንባቡ መሰረት እውነት ወይም ሀሰት በል:: በጉርምስናና በወጣትነት እድሜ መካከል የጎላ ልዩነት የለም:: ይላል? በጉርምስናና በወጣትነት እደሜ መካከል የጎላ ልዩነት የለም ይላል:: ከምንባቡ አኳያ እውነት ነው ሀሰት ነው?

ወ/ተ ሀሰት

መ/ር ሀሰት ነው:: የጎላ ልዩነት አለ:: የልጅነት ጊዜ የሚታወሰው እንደገጠመኙ መብዛትና ማነስ እንደትዝታው ደብዛዛነትና ጥራት ነው?

ሲ/ተ እውነት

መ/ር እውነት ነው:: የልጅነት ጊዜያችንን የምናስታውሰው እንደገጠመኞቻችን ነው::

ወ/ተ እንደገጠመኞቻችን የሚለው አልገባኝም?

መ/ር እሺ!ጥሩ የልጅነት ጊዜ ያሳለፍን ከሆነ በመጫወት፥ በመደሰት፥ ጥሩ እንክብካቤ እያገኘን አሳልፈነው ከሆነ ጥሩ እናስታውሰዋለን:: በችግር፥በሀሙም፥በመበሳቆል ያሳለፍን ከሆነ በመጥፎ እናስታውሰዋለን:: እሺ! ምኞት እውነተኛ መልኩን የሚያገኘው በልጅነት ዘመን ነው::

ሲ/ተ እውነት

መ/ር አይደለም

ሲ/ተ ሀሰት::

መ/ር ሀሰት ነው:: ምኞት እውነተኛ መልኩን የሚያገኘው መቼ ነው?

ወ/ተ በአዋቂነት::

መ/ር በአዋቂነት:: ለምሳሌ አንድ ልጅ ሳድግ አውሮፕላን አብራሪ፥ ዶክተር፥ እሆናለሁ ይላል አይደል? ይህ ሊተረጎም የሚችለው ከወጣትነት መጨረሻ አካባቢ ላይ ነው:: "መ" የቤተሰብ ሀላፊነት

የሚሰማን በወጣትነት ጊዜ ነው ይላል ይህ ሀሳብ እውነት ነው ሀሰት? እንቺ?

ሊ፣ ሀሰት

መ፡ ሀሰት ነው:: መቼ ነው የሚሰማን?

(ሁሉም ተማሪዎች) በእዋቂነት ጊዜያችን ላይ ነው::

መ፡ እሺ! ወደ መልመጃ ሁለት እናልፋለን:: የተሳሳታችሁትን እያረማችሁ:: መልመጃ ሁለት አንደኛ በሚከተሉት ጥንድ ቃላት መካከል ያለውን ልዩነት ከአብረረሀ በኋላ ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ ዐ.ነገር ስሩባቸው:: ጉርምስና/ወጣትነት ይላል:: ሁለቱም ቃሎች እድሜን የሚገልፁ ናቸው በሁለቱም ቃላት መካከል ተመሳሳይነት አለ:: ልዩነትስ አለ የለም? ጉርምስና ምንድን ነው? ወጣትነትስ ምንድን ነው? ጉርምስና የምንለው የምን ዘመንን ነው?

ወ፣ አፍላ ጊዜ

መ፡ እሽ! ውጣተንት?

ወ፣ (የተናገረው አይሰማም)

መ፡ (አይሰማም)

ወ፣ ጉርምስና የምንለው የተለያየ የሰውነት ለውጥ የሚታይበት ጊዜ ነው:: እና ደግሞ ሰውነት ወደ ህፃንነት የሚገባበት ጊዜ ነው::

መ፡ አዎ!

ወ፣ ወጣትነት የሚባለው ደግሞ ከጉርምስና ለየት ብሎ ወይ ጉልምስና የሚደረስበት ነው::

መ፡ ትክክል! ጉርምስና ዘመን የልጅነት ጊዜ ማብቂያ ላይ ነው:: በሁለቱ ቃላት መካከል ልዩነት አለ::

ወ፣ የልጅነት ጊዜ ማብቂያ እንዴት ጉርምስና ይባላል?

መ፡ አንድ ሰው ጎረመሰ የሚባለው የልጅነት ጊዜውን ሲጨርስ ነው እሽ!

ጉርምስና/ጉልምስና በሁለቱ ቃላት መካከል ልዩነት አለ? ጉርምስና ምንድን ነው? ጉልምስና ምንድን ነው?

ወ፡ የአፍላነት ጊዜ የሚጀምርበት፡፡

መ፡ የአፍላነት ጊዜ የምትለውን እስኪ ንገረኝ?

ወ፡ ወንዶች ከ15ና ከ16 አመት በላይና ሴቶች ደግሞ ከዚያ ዝቅ ብለው የሚጀምሩት አፍላ የስሜት ለውጥ የሚጀምርበት ጊዜ ማለት ነው፡፡

መ፡ አዎ! አፍላ የስሜት ለውጥ የሚታይበት ጊዜ ጥሩ ነው! እንዲያውም በባዮሎጂ የተማራውን ነገር ነው የነገረን፡፡ የሰውነት ለውጥ የሚካሄድበት ነው ብሎ ነው የነገረን፡፡ ጉልምስናስ ምንድን ነው? ሁለተኛው? ሀብታሙ?

ወ፡ ጉልምስና የምንለው ጭንቅላታችን ሲበስልና ወደ አዋቂነት ስንገባ

መ፡ አዎ! ወደ አዋቂነት ደረጃ ስንሸጋገር ነው፡፡ እሽ! "ለ" አዋቂነትና ሽምግልና በሁለቱ ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? አንድ ሰው አዋቂ ነው እንላለን፡፡ አዋቂ ነው ስንል ምን ማለታችን ነው፡፡ ልዩነት አለ አይደለም እንዴ? እሽ!

ወ፡ አዋቂነት ማለት ትልቅ መሆን ሽማግሌነት ሲሰማን እና ሽምግልና ማለት ደግሞ ትልቅ መሆን፡፡

መ፡ አዎ! ልክ ነው ከሞላ ጎደል ተመልሷል፡፡ አዋቂነት የምንለው ምንድን ነው? ቅድም እንደተባለው የቤተሰብ ሀላፊነት መሸከም ስንጀምር የአዋቂነት እድሜ ይባላል፡፡ ሽምግልናስ ደግሞ ምንድን ነው? በሰውነት እ? ቅድም እንደመለሰክልኝ ግለፅ? ፍቃዱ?

ወ፡ ከዚህ ከአዋቂነት ጊዜ ተለውጦ ከዚህኛው ወደ ባስ ወደ እርጅናው የሚደርስበት ጊዜ ነው፡፡

መ፡ እርጅና በምን ባህርይው ይታወቃል? በእርጅና ጊዜ ሰውነታችን ምን ይሆናል?

ሴ፡ ሰውነታችን ይደክማል፡፡

መ፡ አዎ! ሰውነታችን የሚደክምንት ጊዜ ነው፡፡ አዋቂነት የምንለው የቤተሰብ ሀላፊነት ሲሰማን ነው፡፡ ምራት መዋጥ ስንችል፡፡ ጭምት ስንሆን እ! ሽምግልና የምንለው ምንድን ነው? ስንደክም፣ ሰውነታችን መዛል ሲጀምር እሽ! ማርጀት/መጃጀት ይኖራል? ማርጀትና መጃጀት ማርጀት ምንድን ነው? መጃጀት ምንድን ነው? ሀብታሙ?

ወ፡ ማርጀት በጣም እራሱን ሳይስት በመድከም ላይ ያለ መጃጀት በጣም ከማርጀት አልፎ ወደ ህፃንነት ደረጃ የምንደርስበት

መ፡ ትክክል! ማርጀት የምንለው አንድ ሰው የቀድሞ ጉልበቱን ሲያጣ ቀደሞ ሲሰራ ከነበረው በስራ ሲቀንስ፣ መጃጀት የምንለው ግን ምን ሲሆን ነው? አንድ

ሰው ከመድከሙ የተነሳ አእምሮው የቀድሞውን ማስታወስ ትቶ ልክ እንደ ህፃን

መሆን ሲጀምር ማለት ነው፡፡ እሺ! መንገላታት/መጎሳቆል ይባላል፡፡ በሁለቱ ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው፡፡

ሴ.ተ መንገላታት መንከራተት ሲሆን መጎሳቆል ደግሞ በኑሮ አለመመቸት ማለት ነው፡፡

መ፡ እስኪ ሌላ ተጨማሪ በዚ ላይ? ትክክል ነው፡፡ ተጨማሪ ማብራሪያ?!

ወ.ተ መንገላታት መሰቃየት ሲሆን መጎሳቆል መኩራመት ማለት ነው፡፡

መ፡ መኩራመት ምንድን ነው? ለምሳሌ ብለህ ንገረኝ በዐ.ነገር

ወ.ተ አሁን ለምሳሌ በሀብት ሰው ካለበት ደረጃ ዝቅ ሲል ማለት ነው፡፡

መ፡ ካለበት ደረጃ ዝቅ ሲል ምንድን ነው የሚባለው ታዲያ? እሽ! ታጠቅ?

ወ.ተ መኩራመት

መ፡ አይደለም

ወ.ተ መንገላታት የምንለው መልፋት፣ መድከም ወይም ደግሞ መውጣት መውረድ ያለበት ሂደት ሲሆን መጎሳቆል ከመጠን በላይ መሰቃየት እንዲሁም በሰቆቃ መኖር፡፡

መ፡ አዎ! ከሞላ ጎደል መልስታል መንገላታት ማለት በአካል ድካም ሲሰማን ነው፡፡ ከቦታ ቦታ ውጣ ውረድ ሲደርስብን ነው፡፡ ተጎሳቆለስንል ግን ምንድን ነው? በአካላችን ላይ ጉዳት ሲደርስ ሰውነታችን ሲለዋወጥ፣ የሰውነታችን መልክ፣ ቅርፅ ሲለዋወጥ ተጎሳቆለ እንላለን፡፡ መንገላታትን ግን እንዳለን ሆነን የተለያየ ችግር ሲደርስብን፡፡ እሽ! ሁለተኛ ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ትርጉማቸውን ስጥ ይላል፡፡ የሚዘገንን ይላል?

ወ.ተ የሚያሳዝን

መ፡ ሌላስ?

ሴ.ተ የሚያስፈራ

መ፡ የሚያስፈራ፣ የሚሰቀጥጥ፡፡ እሽ! ደበዛነት?

ወ.ተ ፈዛዛነት

መ፡ ፈዛዛነት ሌላስ?

ወ.ተ ብርሃን ያነሰው፡፡

መ፡ ብርሃን ያነሰው ሌላስ?

ወ.ተ ደማቅ ያልሆነ

መ፡ ደማቅ ያልሆነ፣ ዉለምለም ያለ ነው መቦረቅ?

ሴ.ተ መደሰት

መ፡ መደሰት፣ የደስታ ስሜት መሰማት፡፡ ደንገዝገዝ ሲል? እሽ! አንቺ?

ሴ.ተ ዉለምለም ሲል፣

መ፡ ዉለምለም ሲል፣ መሽትሽት ሲል፡፡ ወፍ ሲንጫጫ?

ሴ፡ ሲንጋጋ

መ፡ እዎ! ሲንጋጋ፡ መንጋት ሲጀምር ወይም ምን ይባላል?

ወ፡ ጎህ ሲቀድ

መ፡ እዎ! ጎህ ሲቀድ። እያረማችሁ ነው አይደል?

ሁሉም ተማሪዎች ፡እዎ!

መ፡ እሽ! የተስፋ ቡቃያ?

ሴ፡ አዲስ ህይወት

መ፡ አዲስ?

ሴ፡ ህይወት

መ፡ አዲስ ህይወት፡ አዲስ ተስፋ እሽ! በሚከተሉት መስተዋድዶች ዐ.ነገሮችን ስር፡ታችሁ አሳዩ ይላል? "ህ" ቢሆንም የሚል ቃል አለ። እስኪ ቢሆንም በሚለው ቃል ዐ.ነገር ስሩ። እሽ!

ሴ፡ ስሉምን ሰካራም ነው። ቢሆንም በመስሪያ ቤቱ ስራውን በደንብ ስለሚሰራ አለቃው ያደንቁታል።

መ፡ ትክክል! ትክክለኛ ዐ.ነገር ነው። እሽ! ነገር ግን ይላል። ነገር ግን በሚለው?

ወ፡ አበበ ጎበዝ ተማሪ ነው። ነገር ግን ንፅህናውን አይጠብቅም።

መ፡ አበበ ጎበዝ ተማሪ ነው። ነገር ግን?

ወ፡ ንፅህናውን አይጠብቅም

መ፡ እዎ! ነገር ግን ንፅህናውን አይጠብቅም። ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን ነው የአያያዘው ነገር ግን የሚለው ቃል መስተዋድድ ነው። መስተዋድድ ማለት ምን ማለት ነው? መስተዋድድ የምንለው ምን የሚያደርግ ነገር ነው?

ወ፡ ሁለት ነገሮችን የሚያያይዝ

መ፡ እዎ! ሁለት ነገሮችን (ሀሳቦችን) የሚያያይዝ የሚያዋድድ የሚያስተሳስር ማለት ነው። ሁለቱን አያይዞ የሚያሳይ ማለት ነው። እንግዲያስ በሚለው ዐ.ነገር?እሽ!ስተ አርጌ?

ወ፡ ወርቁ ደብተሩን እረስቼ መጣሁ ስላለ እንግዲያስ ተመልሰህ ወደቤትህ ሄደህ አምጣ ተባለ።

መ፡ እሽ! ይሁን እንጂ ይላል! ይሁን እንጂ በሚለው? እሽ?

ወ፡ ተሻሁንን በጣም እወደዋለሁ። ይሁን እንጅ እንደበቀለ አይሆንም።

መ፡ ይሁን እንጂ የሚለው ቃል ሁለት የተለያየ ሀሳቦችን የሚያይዝ ነው።ሆኖም በሚለውስ?

ወ፡ ልጅቷ በፕሮግራሙ ላይ አልተሳተፈችም።ሆኖም በሚቀጥለው ጊዜ እንደምትገኝ ቃል ገብታለች።

መ፡ እዎ! ትክክል! እንጂ በሚለው ?

ሲ.ተ፡ የሆንስ ስላልተመቸው ነው እንጂ ይመጣ ነበር።

መ፡ እሽ፣ እነዚህ ናቸው እንግዲህ መስተዋድድ የምንላቸው መስተዋድድ ማለት ሁለት ነገሮችን የሚያዋድድ ማለት ነው። የራሳቸው ባህርይ አላቸው። ባህርያቸውን በሚቀጥለው ጊዜ እናያለን። በዚህ የዛሬውን ትምህርት እናጠቃልላለን።

## መዝገበ ቪዲዮ(Vedio Transcription)

### 1.2. ምድብ ሁለት

መ፡ በአለፈው ጊዜ ስለአእማድ ሰርተን ነበር፡፡አሁንም ቀሪውን ካየን በኋላ ዕድሜ መስታወት ነው የሚለውን ምንባብ አንብበን ከዚ የወጡ ጥያቄዎችን መልመጃ ሁለትን እንሰራለን፡፡ አእማዱን ለመሥራት እርባታውን በኋላ በቃል እንሰራለን፡፡ እሽ!አእማድ ሁለት ናቸው፡፡ ጽኑአንና ድኩማን (የሚረቡና የማይረቡ) ለምሳሌ እስከ ሰባት እርባታ ሊዱ የሚችሉና አንዳንዶቹ እስከ ሁለት የሚሄዱ ናቸው፡፡

ለምሳሌ ሰበር የሚለው ቃል በሚረባበት ጊዜ አድራጊው ሰበር ይሆናል፡፡ አስደራጊው አሰበረ፤አዳራጊው አሰበረ፥ አደራራጊ አሰባበረ፡ ተደራጊ ተሰበረ፥ ተዳራጊ ተሳበረ፥ ተደራራጊ ተሰባበረ፥ወዘተ ይህ በቤተክርስቲያን የሀይማኖት ምሁራን የሚጠቀሙበት ነው፡፡ አሁን ዘመናዊ መጽሀፍት ትርጉን በመከተል አዳዲስ ቃላትን መመስረት ይቻላል፡፡ ለምሳሌ የቃሉ ግሥ ወደቀ ቢሆን ሲረባ እንዴት ነው?

ወ/ተ አድራጊው ወደቀ፤አስደራጊው አስወደቀ

መ፡ አደራራጊው?

ሴ/ተ አስወደቀ

መ፡ ልክ አይደለም

ወ/ተ ወደቀት

ወ/ተ አዋደቀ

መ፡ አዋደቀ፡፡ እሽ አደራራጊ?

ወ/ተ አወዳደቀ

መ፡ ተደራጊ?

ወ/ተ ተዋደቀ

መ፡ ና፣

ወ/ተ ተወደቀ

መ፡ ተዳራጊ

ሴ/ተ ተዋዳቂ

መ፡ ተደራራጊ

ሴ/ተ ተወዳደቀ

መ፡ ተወዳደቀ እንደገና?

መ፡ ደራራጊ?

ወ.ተ ወዳደቀ

መ፡ እሽ! ሌላ አንድ ግሥ እንውሰድና ያንን እናድርግ። ሄደ አድራጊ?

ሴ.ተ ሙሄድ

መ፡ ትክክል አይደለም

ሴ.ተ ሄደ

መ፡ ሄደ እሽ! አስደራጊ?

ወ.ተ አስሄደ

መ፡ እሽ! አዳሪጊ?

ወ.ተ አኳሄደ

መ፡ ተደራጊ?

ወ.ተ ተኳሄደ

መ፡ ተደራጊ?

(ሁሉም ተማሪዎች) ተኳሄደ

መ፡ ተደራራጊ ምንድን ነው?

ወ.ተ ተኳሄደ

መ፡ አይደለም አብረቻም?

ወ.ተ አኳሄደ

ሴ.ተ ሄደ

ሴ.ተ አስኬደ

ሴ.ተ ተኳሄደ

መ፡ ተኳሄደ ቢሆንስ?

ወ.ተ ተኳሄደ ተብሎ የለም እንዴ ታዲያ?

ሴ.ተ (የተናገረችው አይሰማም የምትጠይቅ ይመስላል)

መ፡ እዚህ ላይ እሰግድን በተመለከተ ሌሎች ቃላትን መስረት በማድረግ እንድትሰሩ። በሌላ ጊዜ የሚቀጥለው መልመጃ ሁለት ነው። ምንድን ነው የሚለው? አንድ በሚከተሉት ጥንድ ቃላት መካከል ያለውን ልዩነት ከአብራራህ በኋላ ልዩነቱን በዐ.ነገር አሳይ ነው የሚለው ለምሳሌ ንርምስና/ መጣትንት ንርምስና ማለት ምን ማለት ነው?

ወ.ተ አፍላ ጊዜ

መ፡ አፍላ ጊዜን ግልፅ ብታደርገው?

ወ.ተ ለነገሮች የሚቸኩል

ወ.ተ ለነገሮች የሚቸኩል በራሱ ትርጉሙ ምንድን ነው?

መ/፡ ለነገሮች የሚቸኩል እድሜን በምናይበት ጊዜ የተለያዩ ደረጃዎች ይኖሩታል። ጉርምስና ምንድን ነው?አፍላ ጊዜ ልክ ነው። ይበልጥ የሚያብራራ?

ተ/፡ ለአቅመ አዳም ያልደረሰ።

መ/፡ ለአቅመ አዳም ያልደረሰ ማለት ምን አይነት ባህርይ ነው?

ሊ/፡ በህፃናትና በወጣትነት መካከል ያለ

መ/፡ ጉርምስና ማለት በህፃንነትና በወጣትነት መካከል ያለ፥ አፍላ ጊዜ፥ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ከ15-18 ዕድሜ ሊደርስ የሚችልጊዜ ነው። ወጣትነትስ? ወጣትነት የሚለው ቃል?

መ/፡ ጥሩ ነው። ወጣትነት ስንል ብዙ ነገር የምንሰራበት ብዙ ነገር እንሰራለን የምንልበት፥ የምንመኝበት አለምን የምንጨብጥ የሚመስለን ጊዜ ነው። እነዚህም ሀ.ነገር ስንሰራባቸው ጉርምስና በሀ.ነገር ውስጥ? እሽ?

ተ/፡ ብዙ ነገር የምንሰራበት ጊዜ የጉርምስና ሊሆን አይችልም?

መ/፡ ድምፅ! ድምፅ!

ተ/፡ (የሚናገረው አይሰማም)

ተ/፡ ከአሉት የዕድሜ ክልሎች ውስጥ ጉርምስና አንዱ ነው።

መ/፡ ከአሉት የዕድሜ ክልሎች ውስጥ ጉርምስና አንዱ ነው።በሀ.ነገር ውስጥ ገብቶ ትርጉሙን ሊያሳየን አይችልም። እሽ!

ተ/፡ የጉርምስና ጊዜ በጣም አስቸጋሪ በመሆኑ በጥንቃቄ ካልተወጡት በሙሉው ህይወት ላይ መጥፎ ጠባሳ ጥሎ ያልፋል።

መ/፡ እሽ! የጉርምስና ጊዜ በጣም ጥንቃቄ የሚያስፈልገው ነው። በፈረንጆች (Fire Age) የሚባለው ነው። ጥሩ ነው ባህርይው ምንድነው? ጎርምስሀል መስለኝ ይላል። እና ጉርምስና የሚለው ቃል በሀ.ነገር በአገባብ ምን ይመስላል?

ተ/፡ ጉርምስና በሰሚቶቻችን ላይ የሚታይ የአካል ለውጥ ነው።

መ/፡ ጥሩ ነው ሳይንሳዊ የሆን ፍቺ ነው።እሽ! በጉርምስና ወቅት በሴቶችም ሆነ በወንዶች ላይ የአካል ለውጥ ይታያል።እሽ!አዋቂነት/ሽምግልና? በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት?

ተ/፡ መጥፎውንም ሆነ ጥሩውን ነገር ያውቃል የሚባልበት ደረጃ

ተ/፡ መጥፎውንና ጥሩውን በጉርምስና ጊዜም ያውቃል። ስለዚህ ከጉርምስና እንዴት ይለያል?

መ/፡ በጉርምስና ጊዜ መጥፎውንና ጥሩውን ቢያውቅም በአዋቂነት ጊዜ የበለጠ ያውቃል እሽ!

መ/፡ ጥሩ ነው? ሌላስ? ሌላስ? እሽ? ዮናስ!

ተ/፡ የአስተሳሰብ ዕድገት የሚታይበት

መ፡ የአስተሳሰብ ዕድገት የሚታይበት ሌላስ?

ሊ፡ተ አዋቂነት ማለት ከልምድም ሆነ ከትምህርት የሚገኝ ዕውቀት ሲሆን
ሸምግልና የዕድሜያችን መጨረሻ ነው፡፡

መ፡ (ያቋርጡትና) መጀመሪያ አዋቂነትን እንጨርሰው አዋቂነት ምንድነው አልሽ?

ሊ፡ተ አዋቂነት ከልምድም ሆነ ከትምህርት የሚገኝ ዕውቀት ነው፡፡

መ፡ አዎ! ብዙ ትምህርቶች አሉ፡፡ ከኅብረተሰቡ የምንማረው ከመደበኛ ትምህርት
ከምናገኘው በተጨማሪ ከኅብረተሰቡ ያገኘውን ዕውቀት ያዳበረ ምን ይባላል?
አዋቂ የአዋቂነት የዕድሜ ክልል ስንት ይመስላችኋል?

ሊ፡ተ ከ15 - 55

መ፡ ጥሩ! አንዳንድ ጊዜ ከ50-60 ሊሆን ይችላል እሺ! ሸምግልና የሚለው ቃል
ትርጉሙ ምንድነው? ስለሺ!

መ፡ ሸምግልና ማለት ያላረጀ ማለት ነው? አልተተረጎመም፡፡ እና እሺ?

ው፡ተ መሸምገል ማለት መድከም፡፡

መ፡ እሺ! የአካላዊ........(አይሰማም)

ው፡ተ ዘገምነት

መ፡ ትክክል! ዘገምነት፥ የአካል መድከም የሚታይበት በዐ.ነገር እንዴት አድርገን
እንስራለን? አዋቂነት በዐ.ነገር ውስጥ እሺ?

ው፡ተ ነገሮችን ማመን አዋቂነት ያስኛል

መ፡ እ! ነገሮችን ማመዛዘን አዋቂነት ያስኛል.....(የማይሰማ)
እንዴት! ትንሽ ብታብራራው?

ው፡ተ ነገሮችን አመዛዛኝ ጥሩ ግምት የሚሰጥ....

መ፡ ጥሩ ነው ግን የቤት ስራ ስለሆን ይኸኛው በደብተር ላይ ቢሠራ
ይሻላል፡፡ ሸምግልና የሚለው?

ው፡ተ በሸምግልና የዕድሜ ደረጃ የሚገኝ

መ፡ ግልጽ አይደለም፡፡ የሸምግልና የዕድሜ ደረጃ ምንን ይገልጻል? አንድ ሰው
ህፃንነት፥ጉርምስና፥ ወጣትነት፥ አዋቂነት፥ሸምግልናና መጃጀት የሚሉትን
ደረጃዎች ያልፋል፥እነዚህን መሠረት በማድረግ

ው፡ተ የእውቁ ሼክስፒር ጥቅስ እንደሚለው ዕውቀት በወጣትነትመኩሪያ፥በጉርምስና
መከበሪያ፥ በሸምግልና ምርኩዝ ናት፡፡

መ፡ የዕውቁ ሼክስፒርን አባባል ነው አሁን ያልከው፡፡ እዚያ ጋ ስምተሻል?
ዕውቀት በወጣትነት መኩሪያ፥ በጉርምስና መከበሪያ፥ በሸምግልና ምርኩዝ
ናት ነው ያለው? አሁን ወደ ስድስተኛው ማርጀትና መጃጀት እንሂድ፡፡ በሁለቱ
መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? ማርጀት ስንል ምን ማለት ነው?

ተ፡ የዕድሜ ማብቂያ

መ፡ ማርጀት ምን ማለት ነው? የሰው ልጅ የመጨረሻ የዕድገት ዘመኑን የሚያሳይ ነው፡

ተ፡ አዎ፡

መ፡ ሌላ፡ ማርጀት የሚለው እሽ! ያሬድ!

ተ፡ በዕድሜ መግፋት አቁውንት መሆን

መ፡ አቁውንት ማለት ምን ማለት ነው?

አሁንም ገልጸንት ይነገደለዋል።ምንድነው የሚደረገው ማርጀት ሲባል

ምንድነው? ማርጀት ሲባል?

ሰ፡ ማርጀት ማለት መሸምገል

መ፡ ገልጸ አይደለም።

ተ፡ ማርጀት ማለት የአዋቂነትን ዘመን አልፎ የመጃጀት ደረጃ ከመድረሳችን በፊት ሲሆን መጃጀት ማለት ደግሞ የዕድሜያችን የመጨረሻ ደረጃ መድረስ ማለት ነው።

መ፡ እ፡ ዕድሜ ይመስናል? ይህ የመጨረሻ ነው ብለን እንወስናለን? የመጨረሻ ነው ለማለት ምን ምክንያት ነው የምንሰጠው? አንድ ቃል ራሱን የቻለ ትርጉሙም አለው። አንድ ቃል ሌላውን ቃል መቶ በመቶ ተክቶ ሊቀርብ አይችልም። ስለዚህ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ለይቶ ማሳየት መቻል አለብን።

ተ፡ ማርጀት ማለት ነገሮችን የመርሳት

መ፡ መጃጀትስ?

ተ፡ መጃጀት ማለት ደግሞ የህጻንነትን ባህርይ መልሶ የሚያቃርብ

መ፡ መጃጀት የሚለው ትሩ ነው። ግን ማርጀት የሚለው ምንን ያሳያል።የሰው ልጅ ምን የከባቢያዊ ለውጥ ያሳያል? ምንድነው ልዩነቱ?

ተ፡ ማርጀት ከድር ወብትና ቅርጽ መለወጥና መጃጀት ነገሮችን አለማወቅ መርሳት።

መ፡ እሽ፡ ሌላ ተጨማሪ አለ?

ተ፡ ማርጀት የምዋትና የተስፋ ጊዜ ሲያከትም፤ መጃጀት ደግሞ እንደገና ልጅ መሆን።

መ፡ ማርጀት መድከም፤ መጃጀት የልጅነት ዘመን እንደገና የሚመጣበት የማስብ ሁኔታው ወደ ህፃንነት የሚያመዘን ነው። በዐ.ነገር በዐ.ነገር ሲታይ?

ተ፡ ፕሬዚዳንት ማንዴላ የሥልጣን ወንበራቸውን የለቀቁት በእርጅና ምክንያት ነው።

መ፡ ትሩ ነው። ዐ.ነገሩ ወቅታዊ ነው። ትክክለኛ ዐ.ነገር ነው።አንድ ሰው ከልምድ ያገኘውን፤ ከውጭው ዓለም የሰማውን፤ከሬዲዮ ከቴሌቪዥን የሰማውን ከሬዲዮ

ኩቲሊቭኘርን የስማውን በመጠቀም ዐነገር በሳል እንዲሆን ማድረጉ ጥሩ ምሳሌ ነው። መጃጀት?

ሴ፤ መጃጀት ማለት የእርጅና ዘመን ማብቂያ ነው::

መ፤ ምንድን ነው የሚያሳየው? አንድ ጊዜ አቶ ዮናስ አድማሱ በፃፉት ውስጥ ያየሁት ቃላት ይወለዳሉ፥ ያድጋሉ፥ ይሞታሉ:: ከጥሩ ደራሲ እጅ ሲሆኑ ያድጋሉ፥ ያብባሉ፥ ባለሙያ ባልሆነ እጅ ግን ይጫጫሉ:: ቃላትን ባልሰራንባቸው ይጠፋሉ። ይቀጭጫሉ ስለዚህ የምንሰጣቸው ሀሳቦች ደረጃውን የጠበቁ መሆን አለባቸው። እሺ! ለምሳሌ

ተ፤ አንድ ሰው ከመጃጀቱ የተነሳ የሚሰራውን አያውቅም::

መ፤ አንድ ሰው ከመጃጀቱ የተነሳ የሚሰራውን አያውቅም ሊላውስ በወጣትነት በጉርምስና ጊዜስ? ጥሩ ነው ሀሳቡ ግን አንድ?

ተ፤ መጃጀት ማለት ተፈጥሮ ለሰው ልጅ ካበረከተቻቸው ነገሮች አንዱ አስቀያሚ ነገር ነው።

መ፤ ጥሩ ነው። ተፈጥሮ ካበረከተቻቸው አንዱ አስቀያሚ ነገር ነው:: ኧ! የመጨረሻው ምንድን ነው? መንገላታትና መሳቀቅ? መንገላታትና መሳቀቅ? ምን ማለት ነው? መሳቀቅ ሲባልስ ምን ማለት ነው? እሺ?

ተ፤ መንገላታት ማለት በስራ መዛል ሲሆን መሳቀቅ ደግሞ ከሰውነት ደረጃ መውጣት

መ፤ መሳቀቅ ለሚለው ከሰውነት ደረጃ መውጣት የሚለው የሁለተኛው ጥሩ ነው:: መንገላታት የሚለውስ? መንገላታት?

ተ፤ መንከራተት

መ፤ መንከራተት። ሌላስ? መንገላታት የሚለው አሁንም በደንብ አልተመለሰም::

ተ፤ መንላላት

መ፤ መንላላት ማለት? አልተመለሰም:: እሺ! ብርቱ!

ሴ፤ መሰቃየት

ተ፤ መሰቃየት በኑሮ ወይም በድካም ምክንያት ለአጭር ጊዜ መሰቃየት መሳቀቅ ማለት የልድሜ ጉግሹን ወይም ከዚያ በላይ መሳቀቅ ማለት ነው::

መ፤ ሌላስ፣ አልተመለሰም ምክንያቱም መንገላታት ሲል ምን ማለቱ ነው? መሳቀቅ ሲል ምን ማለቱ ነው?

ተ፤ መንገላታት ማለት መንከራተት ሲሆን ማለት ስቃይን ያሳያል:: መሳቀቅ ማለት ደግሞ መጨቆን

መ፤ ሁለቱም መልስህ ቢቻል... (የማይሰማ)

ሌ/ተ መንገላታት ማለት የሰው ልጅ በችግር ምክንያት ከቦታ ቦታ መሰደድ ሲሆን መንገላታት ማለት ከሰውነት ደረጃ መውጣት

መ/ር እስኪ የመጨረሻ?

ተ/ሪ መንገላታት ማለት (የማይሰማ)

መንገላታት ማለት በኑሮውም ሆነ በተለያዩ ምክንያቶች መሰቃየት

መ/ር እሺ፣

ተ/ሪ መንገላታት ማለት አንድ ሰው በሌላው ላይ የሚያደርሰው ማሰቃየት ማለት ነው። መንገላታት ማለት በችግር ምክንያት የራሱን የሰጋዊ የሆነውን ነገር ማጣት።

መ/ር እሺ፣ ይህ መንገላታት የሚለው በውጫዊ ሀይል በሰው መንገላታት በሌላው ላይ የሚያደርሱት ችግር ያሳያል። መንሳቆል እናንተ እንዳላችሁት በራስ ላይ የሚደርስ ችግር፣ ስቃይ፣ ድህነት፣ ከሰውነት ውጭ የመሆንን ያሳያል። እናም በሁለቱ መካከል ልዩነት አለ። ልክ ሞተና ተሰናበተ የሚሉት ሁለት ቃላት ትርጉማቸው አንድ አይደለም። ሁለቱም ቃላት በጋራ የሚያሳዩት አለ። እስትንፋስን ማጣት ሌላው ማንኛውም ሰው በህመምም ሆነ በሌላ ምክንያት ከዚህ አለም በሞት መለየትን ያሳያል። ተሰናበተ ከተባለ ግን በዕድሜ በግልፅ ብዙ ነገሮችን ካየ በኋላ ልክ አንድ ሰው ወደ ጉዞ በሚሄድበት ጊዜ እንደሚያደርገው ያም በዕድሜ የበለፀገ ሰው ሲሞት እንጂ ተሰናበተ እንላለን እና ለዛሬው እዚህ ላይ ይበቃል በሚቀጥለው በተለይ በጉንድ ቃላት ላይ የበለጠ ውይይት እናደርጋለን።

## ምዝገባ ቪዲዮ (Vedio Transcription)

### ምድብ ሶስት

[illegible] እሺ፣ ተማሪዎች ባለፈው ጊዜ "ጊዜ ክቡር የህይወት አስኳል ነው።" የሚለውን ምንባብ አንብበን የመጨረሻውን መልመጃ ሰባትን ጀምረናል። ያንን ስንጨርስ ወደሚቀጥለው ርዕስ "እድሜ መስተዋት ነው።" ምንባብ መልመጃ ሁለትን እንሰራለን ማለት ነው። እሺ! እስኪ እንግዲህ በተማራችሁት መሰረት እነዚህን ቃላት ወደያንዳንዱ አምድ ለመቀየር ሞክሩ። ለምሳሌ ባለፈው ጊዜ ሰበረ የሚለውን ቃል ወስደናል። ስለዚህ ይህ ሰበረ የሚለውን በአዕማድ አምድ መሰረት የሚሰራልኝ ማነው? እሺ ሳምሶን?

[illegible] በሁሉም አምድ ነው?

[illegible] አዎ፣

[illegible] ሰበረ አድራጊ ሰበረ፣ አስደራጊ አሰበረ፣ አዳራጊ አሳበረ፣

[illegible] ጥሩ ተደራጊ ተሰበረ

[illegible] ጥሩ፣ ተዳራጊ?

[illegible] ተሰበረ

[illegible] እሺ፣

[illegible] ተሰበረ እንዴት ይሆናል?

[illegible] ተሰበረ ነው አደራራጊ?

[illegible] ተሰባበረ

[illegible] እሺ፣ ጥሩ ፣፣ ተደራራጊ?

[illegible] ሰባበረ

[illegible] እሺ፣ ሽ፣ እዚህ ላይ ሰባበር የሚለው ደራራጊ አምድ ነው ብለናል። ደራራጊ አምድ ማለት ምን ማለት ነው? በዐ.ነገር ሰርቶ የሚያሳየኝ ማነው? ለምሳሌ መቃ የሚለውን ብንወስድ ደራራጊ ላይ ምንድን ነው የሚሆነው?

[illegible] መቃቃ

[illegible] መቃቃ ነው። ስለዚህ ሰባበረ የሚለውን ዐ.ነገር የሚሰራልኝ?እሺ ደምስ?

[illegible] ሊጂ ጠርሙሱን ሰባበረ።

[illegible] ሊጂ ጠርሙሱን እ! ሰባበረ። ሌላ ምሳሌ ሰባበረ ከሚለው ውጭ ደራራጊ አምድን በመጠቀም ሌላ ምሳሌ የሚሰጠኝ? ልጃገረዶችስ ምን ሆናችኋል? እጃቸውን አታወጡም? እሺ! ሂሊን? ቆመሽ!

[illegible] መገበረ ከሚለው ደራራጊ ላይ መገባበረ ይሆናል።

[illegible] (ደናንሴል የሚጠይቅ ይመስላል) የተናገረው አይሰማም

[illegible] አዎ፣ ድምፅሽን ከፍ አድርገሽ ከላላ ያለሽው ይሰማኛል? ቃሉ ምንድን ነው?

[illegible] መገበረ

መር፡ እሺ፣ ደራራጊ ላይ?

ሴ.ተ፡ መንገዳገዳ ይሆናል! መር፡ እሺ! እኔ አንድን ሰው ብመታ አደራጊ አምድ ላይ መቶ የሚለውን እንዴት ነው ማርባት የሚቻለው? ጥያቄው ግልፅ ነው? (ጥያቄውን ደጋመች)።

ሴ.ተ፡ መቶ የሚለው አደራራጊ ላይ አመታታ

መር፡ እንደገና?

ሴ.ተ፡ መቶ የሚለው አደራራጊ ላይ አመታታ

መር፡ አመታታ ይሆናል ደበደበ የሚለውስ? አስደራጊ አምድ ላይ ምን ይሆናል? እ! የሚነግረኝ ሰምህ ማነው?

ወ.ተ፡ የኔ

መር፡ እሺ፣ የኔ!

ወ.ተ፡ አስደበደበ

መር፡ አደራራጊ ላይ

ወ.ተ፡ አስደ ብዳቢ

መር፡ አስደ ብዳቢ። ጥሩ! ወደሚቀጥለው ጥያቄ እዚህ ላይ ግልፅ ያልሆነ አለ? በተለይ አምድን በተመለከተ ወደሚቀጥለው መልመጃ ሁለት ላይ እንሄዳለን። መልመጃ ሁለት ላይ ስንመጣ የሚከተሉትን ቃላት ልዩነታቸውን አሳይ ነው የሚለው። አንደኛው ምንድን ነው የሚለው? እሺ! አበባ?

ሴ.ተ፡ ነፈርምስና/ወጣትነት

መር፡ ነፈርምስናና ወጣትነት በእነዚህ ቃላት መካከል አንደኛ ልዩነቱን ትናገራላችሁ ከዚያ በኋላ ፍቺውን ይበልጥ ለማጉላበት በያንዳንዳቸው ላይ ምን እናደርጋለን? እሺ፣ አዎ!

ወ.ተ፡ ነፈርምስና ማለት የተለያዩ ምልክቶች የሚከሰቱበት ሲሆን ወጣትነት ደረጃ ደግሞ ከነፈርምስና ቀጥሎ የሚገኝ የዕድሜ ደረጃ ሲሆን ይህም የድፍረት፣ የችኩልነት፣ አስተሳሰብን ወደ ተግባር የምንለውጥበት ነው።

መር፡ በጣም ጥሩ! እሺ! ትርጉሙን ተስፋዬ በጥሩ ሁኔታ አስቀምጦታል የሀን ተስፋዬ የነገረንን በሁለቱ ግልፅ ለማድረግ በቃላት መካከል ያለውን ልዩነት ይበልጥ ግልፅ ለማድረግ በነፈርምስናና በወጣትነት ዐ.ነገር ሰርቶ የሚያሳየኝ? ማነው ስም`ሽ፣ እሺ፣ ውዴ?

ሴ.ተ፡ አብዛኛው ሰው የነፈርምስና ጊዜውን የሚያስታውሰው በመጥፎ ባህርይው ነው። የኢትዮጵያ ሳር ድንበር በመደፈሩ አብዛኛው ወጣት በጣም ተናደደ።

መር፡ ጥሩ ዐ.ነገር ነው። ወደሁለተኛው እንሂድ ። ሁለተኛውን ጥያቄ የሚነግረኝ? ወደም የሚያነብልኝ አንተ! ለማንበብም እጅ አታወጣም? ታጠቅ!

ወ.ተ፡ አዋቂነትና ሽምግልና

መ/ር እንደኛው አዋቂነት ሲሆን ሁለተኛው ሽምግልና እነዚህ ሁለት ቃላት የሚጎዳኙት ባህርይ አላቸው። ሁለቱም የዕድሜ ክልል ናቸው። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው። ልዩነቱን የሚገልፅልኝ? እሽ? ስምሽ ማነው?

ሊ/ቶ ለምለም

መ/ር እሽ፤ ለምለም!

ሊ/ቶ የአዋቂነት ጊዜ በወጣትነት ጊዜ የአሰብናቸውን የምናከናውንበትና ቤተሰብ የምናስተዳድርበት ጊዜ ነው። ሽምግልና በአዋቂነት ጊዜ ትዳር ከተያዘና ሁሉም ነገር ከተስተካከለ በኋላ የመጠሪያ ጊዜ ነው።

መ/ር በጣም ጥሩ! በጣም ጥሩ! በዚህ ነገር ይበልጥ ይህን ሀሳብ የሚያዳብር? እሽ! ማን ነህ ስምህ? አስናቀ እሽ?

መ/ቶ አዋቂነት ከሌሎች የዕድሜ ክልል ብዙ የበሳል ሁኔታዎች የሚታይበት ነው። የሽምግልና የዕድሜ ክልል አእምሮ በጣም እየደከመ የሚሄድበት የዕድሜ ክልል ነው።

መ/ር ከዚህ በተለየ ሌላ ሀሳብ ሰርቶ የሚያሳየኝ? እሽ!

ሊ/ቶ አዋቂነት ማለት አበበ በአዋቂነት ዘመን ጥምት ሆነ ሽምግልና በሚለው አቶ አስፋው በሽምግልና የተጣሉ ሰዎችን ያስታርቃሉ።

መ/ር እሷ ከሰራችው ሀሳብ ሌላ አቶ አስፋው ሁለት የተጣሉ ሰዎች ሲሄዱ ኑ እኔ ጋ በሉ ወስዶ አስታረቃቸው ነው የምትለው። ሌላ ሀሳብ?

መ/ቶ አዋቂነት በሚለው እኔ በወጣትነት ጊዜዬ ሳይሆን በአዋቂነት የዕድሜ ደረጃ የቤት ጓደኛ እንደምይዝ እተማመናለሁ። ሽምግልና በሚለው አየለ የሽምግልና እድሜ ላይ ስለደረሰ ለወደፊቱ የተሻለ አመራርና አስተሳሰብ ይኖረዋል ማለት ይቻላል።

መ/ር ጥሩ ሀሳብ ነው። ወደ ሶስተኛው እንሂድ ሶስተኛውን የሚያነብልኝ?

ሊ/ቶ ማርጀትና መጃጀት

መ/ር ማርጀትና መጃጀት። በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት የሚያብራራልኝ? እሽ! አስቴር?

ሊ/ቶ ማርጀት ማለት የሰሜት ህዋሳት መድከም ማለት ሲሆን እነዚህም አይን፥ጆሮ ንዲሁም የመሳሰሉት የሰውነት ክፍሎች አይን ጆሮ ስራቸውን የሚያቆሙበት ጊዜ ሲሆን፤ መጃጀት ደግሞ የእርጅና ጊዜ አለፎ የሚመጣ ሲሆን ብዙ ስሜታዊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ እንደሚቀዘቅዙና የመጃጀት የእድሜ ክልል ሲደርስ ብዙዎቹ ጥምት መሞት እንደሚመኙ ልንመለከት እንችላለን። ምክንያቱም ብዙዎቹ የስሜት ህዋሳቶቻቸው ተግባራቸውን ስለሚያቆሙ ነው።

መ፡ ጥሩ ነው! እስቲ የእስቴርን ሀሳብ ወስዶ የመጨረሻውን መጃጀት የሚለውን ብያኔ የሚሰጠኝ? ወይም ፍቺ?

ተ፡ መጃጀት የሚለው የመጨረሻ የዕድሜ ክልል ሆኖ ወደ ህፃንነት የሚመጣ ነው:: እና ይህንን ነው

መ፡ በዚህ ጊዜ ይሚሰራውን ያጣና ተመልሶ ወደ ልጅነት እደሚ ይመለሳል:: እሺ! ዐ.ነገር የሚሰራልኝ? ይቅርታ! ዐ.ነገር የሚሰራልኝ? ማውጣት ትችላለህ እኮ! አንተም እሺ!

ተ፡ የአበበ አባት የማርጀት እደሚያቸው ተቃርቧል:: ሰው የዕርጅና ዘመን ጨርሶ ወደ መጃጀት ዘመን መሻገሩ አይቀሬ ነው::

መ፡ ጥሩ! ሌላ ዐ.ነገር? መሰረት! እሺ!

ሌ፡ (አልመለስኩም)

ተ፡ አስተማሪያችን ቢያረጁም እስካሁን ጡረታ አልወጡም አያታችን ከመጃጀቱ የተነሳ ሰውን ከቅርብም አያይም::

መ፡ መስተአምር ነው! የተጠቀምከው ያ የትኛውን እንደሆነ አንተ ታውቀዋለህ:: እሺ! ወደሚቀጥለው ጥያቄ እንሂድ የሚያነብልኝ? እሺ! መሰረት?

ሌ፡ መንገላታትና መጎሳቆል

መ፡ እሺ! ትርጉማቸውን የሚነግረኝ? የሁለቱ ልዩነት ምንድን ነው? እሺ!

ሌ፡ መንገላታት ስንል መንከራተትን ያመለክታል:: መጎሳቆል ደግሞ መገርጣትን፥ ከሰውነት ተራ መውጣትን ያመለክታል::

መ፡ ጥሩ! ዐ.ነገር የሚሰራልኝ? ወይም የሰራውን የሚያነብልኝ?

ተ፡ ሌባው ወደ እስር ቤት ሄዶ መንገላታት ደረሰበት:: መጎሳቆል በሚለው ደግሞ ሀይሉ በኤድስ ቫይረስ በሽታ መጎሳቆሉ ይታወቅበታል:: (በጣም ያስታውቅበታል)::

መ፡ የሚቀጥለውን ጥያቄ የሚያነብልኝ? ታጠቅ!

ተ፡ ለሚከተሉት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ መሰረት ትርጉም ስጥ?!

መ፡ ([illegible]) የመጀመሪያው ቃል ምንድን ነው የሚለው?

ተ፡ (የተናገረው አይሰማም)

መ፡ ቆይ! አንተ የመጀመሪያው ቃል ምንድን ነው የሚለው? እሺ!

ተ፡ የሚዘገንን

መ፡ የሚዘገንን የዚህን ቃል ትርጉም የሚነግረኝ?

ተ፡ የሚዘገንን ማለት የሚያስፈራ ወይም የሚያስጠላ

መ፡ ሌላ?

ተ፡ የሚሰቀጥጥ

መ፡ የሚሰቀጥጥ የሚለው ይሆናል:: ሁለተኛው ምንድን ነው የሚለው? አበበ!

ው፣ ደብዛዛነት

መ፣ ደብዛዛነት ደብዛዛነት ማለት ምን ማለት ነው? ማነው ስምህ?

ው፣ ፈዛዛነት

መ፣ ፈዛዛነት። ሌላስ ከዚህ በተሻለ መንገድ ምን ማለት ይቻላል? የበለጠ የሚቀርበው?

ው፣ ግልፅ ያልሆነ

መ፣ ግልፅ ያልሆነ። እሽ! መሰረት?

ሊ፣ ደምቆ የማይታይ

መ፣ ደምቆ የማይታይ

ው፣ ጉልህ ያልሆነ

መ፣ ጉልህ ያልሆነ! በምንባቡ መሰረት ደብዛዛነት ያለው ምኑን ነው?

ሊ፣ ነጠቱ የማይታይ

መ፣ ነጠቱ የማይታይ ወደ ስድስተኛው እንሂድ። ምንድን ነው የሚለው? ከሳምሶን ኋላ!

ው፣ መቦረቅ

መ፣ መቦረቅ። መቦረቅ የሚታየው ብዙውን ጊዜ በየትኛው የዕድሜ ክልል ውስጥ ነው፣ ትርጉሙስ ምን ማለት ነው? ከደምስ ኋላ?

ው፣ በልጅነት የዕድሜ ክልል ውስጥ

መ፣ በልጅነት የዕድሜ ክልል ውስጥ ነው። እሽ! እና መቦረቅን ምን ብለህ ትተረጉመዋለህ?

ው፣ መደሰት

መ፣ ሌላስ?

ሊ፣ መፈንጠዝ

መ፣ መፈንጠዝ

ው፣ መፈንደቅ

መ፣ መፈንደቅ እሽ! ይህ ሁሉ ትርጉም ይሆናል። የሚቀጥለው ጥያቄ ምንድን ነው የሚለው? ከታጠቅ ነን? (ተማሪን ለመጥራት ነው)

ው፣ ድንግዝግዝ ሲል

መ፣ ድንግዝግዝ ሲል ይላል ድንግዝግዝ ሲል ያለው ምኑን ለመግለፅ ፈልጎ ነው? እዚያ ምንባቡ ውስጥ? ምንን ለመግለፅ ታስቦ ወይም ምንን ለመግለፅ ፈልጎ ነው፣ ደራሲው ወይም ፀሐፊው ድንግዝግዝ ሲል ያለው? እሽ!

ሊ፣ መምሸቱን ለመግለፅ

መ፣ ቆመሽ እንደገና ድምፅሽን ከፍ አድርገሽ እሽ!

ሊ፣ መምሸቱን ለመግለፅ

መ፡ መምሸቱን ለመግለፅ ፈልጎ ነው ድንግዝግዝ ሲል ያለው ትርጉሙስ ምንድን ነው? በዚያ ምንባብ መሰረት አገባቡ ወይም ድንግዝግዝ ሲል ትርጉሙ ምንድን ነው? እሺ! እ!እም!

ተ፡ ውስብስብ ሲሆን

መ፡ ውስብስብ ሲሆን? አይደለም ጀንበር ወይም ፀሀይ ሲወርድ ወይም ድንግዝግዝ ሲል!! የሳምሶን ጓደኛ?

ተ፡ ጨለምለም ሲል

መ፡ ጨለምለም ሲል ሳይሆን ከዚያ በተሻለ ጨለምለም ሲል ሳይሆን አልጨለመም ገና ነው

ተ፡ (መምህሩ ንግግር ሳያልቅ በመግባት ተናገር) (የሚለውን ግን አይሰማም)

መ፡ ጨለምለም ከማለት ይልቅ ምን ብንለው ይሻላል?

ሲ፡ ሲመሻሽ አካባቢ

መ፡ ድምፅሽ አይሰማም በጣም ኮሳሳ ነው።

ሲ፡ ሲመሻሽ አካባቢ

መ፡ መሸትሸት… እ? ሲል ለአይን ያዝ …?

(ተማሪዎቹ (በአንድ) 'ሲያደርግ'

መ፡ እኔ አልናገርም እናንተ ተናገሩ እሺ!

ተ፡ ለአይን ያዝ ሲያደርግ

መ፡ ድምፃችሁ አይሰማም! እሺ!

ተ፡ ለአይን ያዝ ሲያደርግ

መ፡ ለአይን እ! ያዝ ሲያደርግ ጥሩ! ኧ! ወፍ ሲንጫጫ የሚል መሰለኝ የሚቀጥለው ጥያቄ ባልሳሳት። እሺ!

ሲ፡ ሊነጋጋ ሲል

መ፡ ድምፅሽን ከፍ አድርገሽ

ሲ፡ ሊነጋጋ ሲል

መ፡ ሊነጋጋ ሲል ወይም (ተማሪዎቹ ሳያልቃ ገቡ) ኖ! እየሳቀ)

ተ፡ (የተናገረው አይሰማም)

መ፡ አልተሰማኝም

ተ፡ ጎህ ሲቀድ

መ፡ ጎህ ሲቀድ! ጎህ ሲቀድ ጥሩ! እንግዲህ መልመጃ ሁለት..

ተ፡ (የቀረ ጥያቄ መኖሩን አሳሰበ)

መ፡ አንድ ይቀራል? እ! ምንድን ነው የቀረው?

(ተማሪዎቹ (በአንድ) የተሰፉ ቡቃያ

መ፡ ኖ! እሺ!

ወ፣ የተስፋ ቡቃያ

መ፣ የተስፋ ቡቃያ፣ ትርጉሙን አንተው ተጥልበት?

ወ፣ ተስፋ የሚጣልበት

መ፣ የተስፋ ቡቃያ ተስፋ የሚጣልበት ማለት ነው:: ሌላስ? እሽ!

ሊ፣ የተስፋ ጭላንጭል

መ፣ የተስፋ ጭላንጭል ኧ!

ሊ፣ ተስፋ የሚደረግበት

መ፣ ድምፅሽን ትንሽ ከፍ አድርገሽ

ሊ፣ የተስፋ ጭላንጭል

መ፣ ማለት? እ! እሽ!

ሊ፣ የተስፋ ቡቃያ

መ፣ ጥሩ! ሌላስ! ሌላ ከዚህ የተሻለ ምን ሌላ አለ? እናንተ እኮ! ነገ፣ ነገ እኛን የምትተኩ የተስፋ ቡቃያዎች ናችሁ ብዬ ብል ምን ለማለት ፈልጌ ነው? (የማይሰማ ነገር ተናገሩ ተማሪን የሚጠቁሙ ይመስላል) እሽ!

ወ፣ ተስፋ የሚጣልበት ትውልድ

መ፣ ተስፋ የሚጣልበት ትውልድ እሽ!

ወ፣ ተከታይ

መ፣ ተከታይ ምንን ተከታታይ? ማንን?

ወ፣ ያለፈውን ትውልድ (ሌሎች ይሲቃሉ)

መ፣ አኛማ የሆን ቃል...? እ! (ተማሪን ጠቆሙ)

ወ፣ ህልም ወይም ምኞት

መ፣ ህልም ወይም? (ተማሪዎች) ምኞት ህልም ወይም ምኞት ስንል ምናልባት የነፈምስናንና የወጣትነት እድሜ በምንወስድበት ጊዜ እ! ውጣቱ ምኞት አለው፥ ፍላጎት አለው ህልም አለው:: ለምሳሌ የሀገር ፍቅርን፥ የቤተሰብ ሀላፊነትን ለመመስረት ሌላም ሌላም ነገሮች ለመመስረት ምኞት አለው፥ ፍላጎት አለው:: እዚህ ላይ ይሆን ወጣት ምንድን ነው የምንለው? እዚህ ላይ የትኛውን ምኞት? የትኛውን ህልሙ፣ የትኛውን ፍላጎት ለማሟላት ወይም የትኛውን ትውልድ ለመተካት ነው እዚያ የተስፋ ቡቃያ የተባለው? ሳምሶን? እሽ!

ወ፣ የተከካው ትውልድ

መ፣ የተከካው ትውልድ እሽ!

ወ፣ ወጣትነት

መ፣ ወጣትነት! (የተማሪውን ሁነብ መልሶ ማለት ይመስላል) በወጣትነት ውስጥ ፍላጎት አለ፣ ምኞት አለ ፍቅር አለ የሀገርም ቢሆን የቤተሰብም ሌላም ሊሆውም:: ይሆን ወጣት የተስፋ ቡቃያ ብለነዋል:: ስለዚህ የተስፋ ቡቃያ ነው

ስንል ምን ለማለት ፈልገን ነው? እንደዚህ የምንለው? የተስፋ ቡቃያ ወጣቱ የተስፋ ቡቃያ ነው እንለዋለን ወጣቱን ስለዚህ ምን ለማለት ተፈልጎ ነው? አሁን የተስፋ ቡቃያ ስንል ምን ማለታችን ነው? እሺ!

ሴ.ተ፡ አላማውን ከግብ አያደርስም ማለት ነው::

መ፡ አላማውን ከግብ አላደረሰም:: ግን አላማውን ከግብ ለማድረስ...ኸ?

ሴ.ተ፡ ተስፋ አለው

መ፡ ተስፋ የተጣለበት ወይም የሚጣልበት ወይም እየተዘጋጀ ያለ ትውልድ ማለት ነው:: ጥሩ! ወደ አራተኛው ጥያቄ እንሂድ፥ አራተኛው እ! አምስተኛው አምስተኛው ምንድን ነው የሚለው? በሚከተሉት ዐ.ነገሮች ውስጥ ከስር የተሰመረባቸውን ቃላት ተግባር ግለፅ? እ! ለምሳሌ እዚህ ላይ ወደ ቅፅል ስንመጣ ቅፅል ከስም ይመሰረታል:: ከስም የሚመሰረት ከሆነ ምንድን ነው የምንለው? ስማዊ? ኸ?

ወ.ተ፡ ስማዊ ቅፅል

መ፡ ስማዊ ቅፅል እንለዋለን:: ቅፅል ከግስ የሚመሰረት ከሆነ? ምንድን ነው የምንለው? ቅፅል ከስም የሚመሰረት ከሆነ ምንድን ነው የምንለው? እሺ!

ወ.ተ፡ ስማዊ ቅፅል

መ፡ ከስም የሚመሰረት ከሆነ ስማዊ ቅፅል እንለዋለን:: ለምሳሌ አበበ እልኸኛ ነው የሚለውን ብንወስድ "እልኸኛ" በሚለው ስር ተሰምሮበታል:: አሁን የተሰመረበት ቃል ምንድን ነው የሚባለው?

የማይታወቅ (ወንድ)፡ (የሚሉት አይሰማም)

መ፡ እሺ!

ሴ.ተ፡ ስማዊ ቅፅል

መ፡ ስማዊ ቅፅል እንለዋለን:: ለምንድን ነው ስማዊ ቅፅል ያልነው? ለምን እልኸኛ የሚለውን ስማዊ ቅፅል አልነው? እሺ!

ወ.ተ፡ እልኸኛ የሚለው ቅፅል አበበ የሚለውን ስም የሚገልፅ ስለሆነ::

መ፡ ለምሳሌ ከስም የሚመሰረት ከሆነ ስማዊ ቅፅል እንለዋለን ብለናል:: እልህ የሚለውን እራሱን እንውሰድ እልህ ቃሉ እራሱ ስም ነው? ወይም ግስ ነው? ይሆን መለየት መቻል አለብን? እና ሌላም እንደምሳሌ እንይ፤ ለምሳሌ አበበ ፈሪ ነው እንላለን:: ፈሪ የሚለውን ቃል እንውሰድ ፈሪ ከሚለው ቃል ምን መመስረት ይቻላል? ወይም ፈሪ የሚለው ቃል የተመሰረተው?

የማይታወቅ (ወንድ)፡ ከግስ

መ፡ እጃቸውን እያወጡ ቀጥሉ እሺ!

ወ.ተ፡ ስም ነው

መ፡ ፈሪ የሚለው ቃል ግሱ ምንድን ነው? እሺ!

ተ፡ ፈሪ

መ፡ ፈሪ ነው ግስ እም፡፡ ለምሳሌ ፈሪ የሚለውን ቃል ፈሪ ከሚለው ግስ ማግኘት ይቻላል፡፡ ግሱ ምንድን ነው

ተ፡ ፈራ ነው፡፡ (ያልተጠየቀ)

መ፡ ፈራ ነው፡፡ ስለዚህ አበበ አልገኘ ነው በማለት ፈንታ አበበ ፈሪ ነው ብንል ኖሮ ይህ ፈሪ የሚለው ቃል ምን አይነት ቅፅል ነው የሚሆነው?

ተ፡ ግሳዊ ቅፅል (ያልተጠየቀ)

መ፡ ግሳዊ ቅፅል ነው የሚሆነው፡፡ ስለዚህ በዚህ መልኩ እልህ የሚለውን እንይ ብንል እልህ ምንድን ነው?

ተ፡ ስም ነው፡፡ (ያልተጠየቀ)

መ፡ ስም ነው፡፡ እልህ ስም ነው፡፡ ስለዚህ በዚህ መልኩ ወደ ሁለተኛው በምንሄድበት ጊዜ 'አስለፈች አመለኛ ናት' ይላል፡፡ የተሰመረበት ቃል አመለኛ የሚለው ነው፡፡ ይህ የተሰመረበት ቃል አመለኛ የሚለው ነው፡፡ ይህ የተሰመረበት ቃለ ተግባሩ ምንድን ነው? የተሰመረበት ቃል ተግባሩ ምንድን ነው? እሺ!

ተ፡ አመለኛ ስምን የሚገልፅ ማለት ነው

መ፡ ስለዚህ ምንድን ነው ማለት ነው?

ተ፡ ስማዊ ቅፅል

መ፡ ስማዊ ቅፅል ነው፡፡ እዚህ ላይ አመል የሚለው እራሱ ስም ነው፡፡ ስለዚህ ስማዊ ቅፅል ሆኖአል ማለት ነው፡፡ ወደ "ሀ" ወይም ወደ ሶስተኛው ጥያቄ እንሂድ ማነው የሚያነብልኝ? እሺ!

ሌ፡ የኮሪያን ጦረተኛ የለውም

መ፡ የኮሪያን ጦረተኛ...እ? (ተማሪዎች በቡድን) የለውም የለውም የተሰመረበት ምን የሚለው ነው?

ሌ፡ ጦረተኛ የሚለው ላይ ነው

መ፡ እሺ፣ ተግባሩ?

ሌ፡ ተግባሩ ስማዊ ሀረግ ነው

መ፡ ስማዊ... እ?

ሌ፡ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡

መ፡ ስማዊ ሀረግ ነው፡፡ እ! ለዛሬ ጥያቄ ነው?

ተ፡ (ይጠይቃል አይሰማም)

መ፡ እዚህ ላይ የተሰመረበት ጦረተኛ የሚለው ላይ ብቻ አይደለም፡፡ የተሰመረው የኮሪያን ጦረተኛ የሚለው ላይ ነው፡፡ አንድ ላይ ነው የተሰመረው፡፡ ስለዚህ ይህ እራሱ ሀረጉ እንደምን ሆኖ ነው የገባው፡፡

ተማሪዎች (በቡድን)፡ ስማዊ ሀረግ

መ፡ አንድ ላይ ስማዩ? እ! ሀረግ ሆኖ ነው የገባው:: እና ይህን ለመግለፅ ነው:: እሺ! ለዛሬ እዚህ ላይ እናቆማለን:: ሰዓት ስላለቀ በሚቀጥለው ጊዜ የሚቀሩትን ጥያቄዎችና መልመጃዎች እንሰራለን:: ጥያቄ ከሌላችሁ እንግዲህ እዚህ ላይ እናቆማለን::

አባሪ 2

### በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
### የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
### የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል
### የድህረ-ምረቃ መርሀ-ግብር
### ለተማሪዎች የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ

የተከበራችሁ ተማሪዎች፡-

ይህ መጠይቅ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሁኔታ ለመመርመር ለታቀደ ጥናት መረጃ ለማግኘት የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ በመጨረሻ በአማርኛ ቋንቋ መማሪያ ክፍል ውስጥ በመማር ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት የሚያስችሉ ሀሳቦችንና ተቆማዎችን እንደሚያመነጭ ይጠበቃል። ጥናቱ ውጤታማ እንዲሆንም የተማሪዎች ተሳትፎ እጅግ አስፈላጊ ነው። እናንተም መጠይቁን በመሙላት ትብብር እንድታደርጉልኝ በትህትና እጠይቃለሁ።

መጠይቁን በመሙላት ለምታደርጉልኝም ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

ማሳሰቢያ

1. በመጠይቁ ላይ ስም መጻፍ አያስፈልግም
2. መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው

ክፍል አንድ

ከዚህ በታች የተቀመጡትን ባዶ ቦታዎች በመሙላት ለተጠየቁት መረጃዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ስጪ

1. ፆታ ------------    3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ------------
2. እድሜ ------------

ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ ናቸው ብለህ/ሽ የምትገምቻቸው/ቻቸው መልሶች በመለየት ይህን "√" ምልክት አስቀምጥ/ጪ

1. የአማርኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ በሚያስተምሩበት ጊዜ በአብዛኛው ጥያቄ የሚጠይቁት
   ሀ. ወንዶቹ    ለ. ሴቶቹ    ሐ. ሁለቱም በእኩል ደረጃ

2. መምህሩ ተያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች ትዕዛዞችን ለማዘዝ ሲፈልጉ በተደጋጋሚ ስም የሚጠሩት

ሀ. የወንዶችን

ለ. የሴቶችን

ሐ. የሁለቱንም በእኩል ደረጃ

መልስህ/ሽ "የወንዶችን" ወይም "የሴቶችን" ከሆነ ለምን ይመስልሃል/ሻል

..............................................................................................................

..............................................................................................................

..............................................................................................................

3. መምህሩ ተያቄ በሚጠይቁበት ጊዜ መልስ ለመስጠት ስትፈልግ /ጊ ምን ታደርጋለህ/ሽ?

ሀ. እጄን አወጣለሁ

ለ. እጄን ማውጣት ስለምፈራ አልመልስም

ሐ. መምህሩ ሲጠይቁኝ ብቻ እመልሳለሁ

4. መልስ ለመስጠት በምትፈልግበት/ጊበት ጊዜ መምህሩ በንግግርህ/ሽ መሀል ጣልቃ በመግባት ንግግርህ/ሽን ያቋርጣሉ?

ሀ. አዎ ለ.አያቋርጡኝም

መልስህ/ሽ አዎን ከሆነ ለምን ይመስልሀል?

..............................................................................................................

..............................................................................................................

..............................................................................................................

## ክፍል ሶስት

ለሚከተሉት ጥያቄዎች ያለህ/ሽን አመለካከት ደረጃ በትክክል ያመለክታል የምትለው/ይውን በስተቀኝ ከተሰጡት አማራጮች መካከል አንዱን በመምረጥ ይህን ምልክት አስፍር/ሪ

| | | በጣም ከፍተኛ | ከፍተኛ | መካከለኛ | ዝቅተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በእንግሊዝኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ ያለህ ተሳትፎ መጠን | | | | | |
| 2 | በእንግሊዝኛ ቋንቋ ክፍለ ጊዜ በመግባባት ማስተማሪያ ዘዴ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት የምታደርገው/ጊው ሙከራ | | | | | |
| 3 | በምትናገርበት ጊዜ ሌሎች ሲመለከቱህ/ሽ የመናገር ፍላጎትህ/ሽ | | | | | |
| 4 | ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት በምትፈልግበት/ጊበት ጊዜ በነፃነት ያለቀላቅል በግል የሚሰጥህ/ሽ | | | | | |
| 5 | ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሽን ስታወጣ/ጪ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ እንድትመልስ/ሺ የሚሰጥህ/ሽ እድል | | | | | |
| 6 | ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅህ/ሽን ብታወጣ/ጪም ባታወጣ/ጪም እንድትመልስ/ሺ መምህሩ የሚሰጥህ/ሽ እድል | | | | | |
| 7 | መልስ ስትሰጥ/ጪ በትዕግስት/ዥ እንደገና እንድትሞክር/ሪ መምህሩ የሚሰጥህ/ሽ እድል | | | | | |
| 8 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ሀሳብህ/ሽን ለሌሎች እንድትገልጽ/ጪ የሚያደርጉልህ/ሽ ማበረታቻ | | | | | |
| 9 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ጥያቄ ለመጠየቅም ሆነ ሌሎች ትምህርትን አስመልክቶ ሀሳብህ/ሽን በነፃነት የመናገር እድል | | | | | |
| 10 | በመግባባት ማስተማሪያ ዘዴ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ጋር ያለህ/ሽ ቅርበት | | | | | |
| 11 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ ለጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስትሰጥ/ጪ የሚሰጥህ/ሽ ማበረታቻ/ሙገሳ | | | | | |
| 12 | የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህርህ/ሽ መልስ ስትሰጥ/ጪ በትዕግስት/ዥ የሚያዳምጥህ/ሽ ... ( ) | | | | | |
| 13 | ለጥያቄዎች በራስህ/ሽ ፍላጎት መልስ የመስጠት ዝንባሌህ/ሽ | | | | | |
| 14 | ያለህ/ሽን ጥያቄ ለመጠየቅ የምታደርገው/ጊው ድፍረት | | | | | |

15. በመምህሩ/በሌላ ተማሪ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ እንድትሰጥ/ጪ ተጠይቀህ/ሽ የተሳሳተ ምላሽ ብተሰጥ/ጪ መምህሩ ሊያደርጉ ይችላሉ ብለህ/ሽ የምታስበውን/ቢውን በቅደም ተከተል ፃፍ/ፊ::

ሀ. ______________________

ለ. ______________________

ሐ. ______________________

መ. ______________________

ሰ. ______________________

አባሪ 3

### በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
### የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
### የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ-ፅሁፍ ክፍል
### የድህረ-ምረቃ መርሀ-ግብር
### ለመምህራን የተዘጋጀ የፅሁፍ መጠይቅ

ውድ መምህር፡- ይህ መጠይቅ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍለ ጊዜ የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ሁኔታ ለመመርመር ለታቀደ ጥናት መረጃ ለማግኘት የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ በመጨረሻ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት መማሪያ ክፍል ውስጥ በመማር-ማስተማሩ ሂደት የተማሪዎችን ተሳትፎ ለማጎልበት የሚያስችሉ ሀሳቦችንና ጥቆማዎችን እንደሚያመነጭ ይጠበቃል። ጥናቱ ውጤታማ የሚሆነውም በሙያው ላይ የተሰማሩ መምህራን ተሳትፎ ሲያደርጉ መሆኑ ስለታመነበት እርስዎም ይህንን መጠይቅ በመሙላት በጥናቱ እንዲሳተፉ በትህትና እጠይቃለሁ።

<u>ማሳሰቢያ</u>፡ በመጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም መጠይቁን በመሙላት ለሚያደርጉት ትብብር በቅድሚያ አመሰግናለሁ።

### ክፍል አንድ

<u>የሚከተሉትን ጥያቄዎች ካነበቡ በኋላ ከቀረቡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ ነው የሚሉትን ያስምሩበት። ባዶ ቦታ ሲኖር የራስዎን አስተያየት ይስጡበት</u>

1. እርስዎ በሚያስተምሩበት ክፍል ለሚጠየቁ ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጃቸውን በተደጋጋሚ የሚያወጡት

   ሀ. ወንዶቹ ለ. ሴቶቹ ሐ. ሁለቱም እኩል

2. በክፍል ውስጥ ያልገባቸውን ጥያቄ በተደጋጋሚ የሚጠይቁት

   ሀ. ወንዶቹ ለ. ሴቶቹ ሐ. ሁለቱም እኩል

3. ለጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ በአብዛኛው የሚሰጡት

   ሀ. ወንዶቹ ለ. ሴቶቹ ሐ. ሁለቱም እኩል

4. እጃቸውን ሳያወጡ በመምህሩ አነሳሽነት ለጥያቄዎች መልስ የሚሰጡት

   ሀ. ወንዶቹ ለ. ሴቶቹ ሐ. ሁለቱም እኩል

5. ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ብዙ ጊዜ እድል የሚያገኙት

   ሀ. ወንዶቹ ለ. ሴቶቹ ሐ. ሁለቱም እኩል

   መልስዎ "ወንዶቹ" ወይም "ሴቶቹ" ከሆነ ለምን ይመስለዎታል?

   ________________________________________

   ________________________________________

   ________________________________________

6. በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በመማር-ማስተማሩ ሂደት የተሻለ ተሳትፎ ያላቸው

ሀ. ወንዶቹ ለ. ሴቶቹ ሐ. ሁለቱም እኩል

7. በአጠቃላይ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት የመማር-ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ ተሳትፎ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል ልዩነት አለ ወይስ የለም?

ሀ. አዎ ለ. ይለም ሐ. ለመወሰን ያስቸግራል

መልስዎ "አዎ" ከሆነ የአስተዋሉት ልዩነት ምንድን ነው?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

የልዩነቱ መንስኤ ምን ይመስለዎታል?

________________________________________________

________________________________________________

________________________________________________

## ክፍል ሁለት

ከዚህ በታች የቀረበው ጥያቄ እንብበው ከተሰጡት ዝርዝሮች መካከል መልስ ይሆናሉ የሚሏቸውን በሙሉ ፊደላቸውን በመክበብ፣ ተጨማሪ የሚሉት ካለም በተሰጠው ክፍት ቦታ ላይ በመፃፍ ይመልሱ።

5. የሴት ተማሪዎች የክፍል ውስጥ ተሳትፎ ከወንዶች ያነሰ የሆኑባቸው ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

   ሀ. መምህራን ወንዶችና ሴቶች ተማሪዎችን እኩል ስለሚያሳትፍ (ለሴቶች ተማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ)

   ለ. በክፍል ውስጥ የመምህር-ተማሪ ተራክቦ ላይ ወንዶች ከሴቶች የበለጠ ተሳታፊዎች በመሆናቸው

   ሐ. ሴቶች "ብሳሳት ይስቁብኛል" በሚል የሚኖራቸው ፍርሃት ከፍተኛ በመሆኑና ዝምታን ስለሚመርጡ።

   መ. ሴቶች በራስ የመተማመን ችሎታቸውም ሆነ ለራሳቸው የሚሰጡት ግምት ዝቅተኛ በመሆኑ

   ሰ. በክፍል ውስጥ ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች እኩል ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እድል ስለማያገኙ

   ሸ. ሴቶች ተማሪዎች አይነአፋር በመሆናቸውና ለመሳተፍ ስለማይነሳሱ

   ቀ. በትምህርት ችሎታ ሴቶች ከወንዶች ያነሱ በመሆናቸው

   በ. ሴቶች ተማሪዎች ከወንዶች እኩል ትምህርቱን ለመከታተል ስለማይችሉ

ሌላ ካለ ይገለጽ ________________________________________

________________________________________

________________________________________

## የተማሪዎችን ተሳትፎ ለመመርመር የተዘጋጀ

### የምልከታ ቻርት(Observation Checklist)

ምልከታው የተደረገበት ምድብ/section/________________

ምልከታው የተደረገበት ቀን______________

ምልከታው የተደረገበት ሰዓት____________ ያለቀበት____________

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው የዕለቱ ትምህርት ርዕስ______________

| ተ.ቁ | ተሳትፎዎች | ድግግሞሽ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምድብ አንድ | | ምድብ ሁለት | | ምድብ ሶስት | |
| | | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት |
| 1 | ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት እጅ ማውጣት | | | | | | |
| 2 | ለጥያቄዎች በተደጋጋሚ መልስ መስጠት | | | | | | |
| 3 | ትክክለኛ መልስ በተደጋጋሚ መስጠት | | | | | | |
| 4 | ጥያቄ መጠየቅ | | | | | | |
| 5 | በፈቃደኝነት መልስ መስጠት | | | | | | |
| 6 | በመምህሩ አነሳሽነት መልስ መስጠት | | | | | | |

## የመምህሩን ትኩረት(attention) እና ቃላዊ ምጋቢ ምላሽ (verbal feedback) ለመመርመር የተዘጋጀ የምልከታ ቻርት(Observation Checklist)

ምልከታው የተደረገበት ምድብ/section/ ____________

ምልከታው የተደረገበት ቀን ____________

ምልከታው የተደረገበት ሰዓት ____________ ያለቀበት ____________

በምልከታው ወቅት ይሰጥ የነበረው የዕለቱ ትምህርት ርዕስ ____________

| ተ.ቁ | ተላውጦዎች | ድግግሞሽ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምድብ አንድ | | ምድብ ሁለት | | ምድብ ሶስት | |
| | | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት | ወንድ | ሴት |
| 1 | ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ እጅ ላወጡ ተማሪዎች መምህሩ የሚሰጡት እድል | | | | | | |
| 2 | ለጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ እጅ ላላወጡ ተማሪዎች መምህሩ የሚሰጡት እድል | | | | | | |
| 3 | ትክክለኛ መልስ ለሰጡ የመምህሩ ሙገሳ | | | | | | |
| 4 | የተሳሳተ መልስ ለሰጡ የመምህሩ ግሳጼ (Reprimands) | | | | | | |
| 5 | የተማሪዎችን ስም በተደጋጋሚ መጥራት | | | | | | |
| 6 | የተማሪዎችን መልስ መድገም | | | | | | |

# ማረጋገጫ

እኔ ከዚህ በታች የፈረምኩት፥ ይህ ጥናት የራሴ ስራና በጥናቱም ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ፅሁፎች፥ ምንጮች በሙሉ የጠቀስኩ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ስም [illegible]

ፊርማ

አድራሻ፡- አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፥ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍል
አዲስ አበባ